# የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት

# መተዳደሪያ ደንብ

**(ሕገ-መጅሊስ ቁጥር 1/2011/1440)**

በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ አስተባባሪነት
በመዋቅር ንዑስ-ኮሚቴ የቀረበ ረቂቅ መዋቅርና መተዳደሪያ ደንብ

(ሕገ-መጅሊስ)

**መጋቢት 2011**

**1440ዓ.ሒ**

**2019**

**አዲስአበባ**

## بســـم الله الرحمن الرحيم

"በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በኾነው"

## መግቢያ

በዘውዳዊው ሥርዓተ-መንግስት ዘመን ተጠንስሶ የሀገሪቱን ታሪክ በቀየረው የ1966ቱ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ፈር-ቀዳጅ የተቃውሞ ትዕይንተ-ህዝብ ማግስት በተመሰረተው አብዮታዊ የሴኩላር ሥርዓት መባቻ ላይ መጋቢት 28 ቀን 1967(ረቢዑል አወል 12 ቀን 1395ዓ.ሒ.)የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ከፍተኛ ምክርቤት በሚል ስያሜ በሕዝበ-ሙስሊሙ በይፋ የተመሰረተው መጅሊስ በዘመነ-ውልደቱ የወጠናቸውን ዓላማዎች፣ያነገባቸውን እሴቶች፣የተለማቸውን ግቦችና ያለማቸውን ራዕዮች ከወቅቱ ተጨባጭ ጋር በማጣጣም የአባቶቻችንን አደራ ተረክበን በተሻለ አቅምና አማና ለመፈጸም በማሰብ፤
ይህ በጎ እሳቤ ይሳካ ዘንድ መጅሊስ ሳለፈው ግማሽ ምዕተ-ዓመት የተጓዘባቸውን መስመሮች፣ ያለፈባቸውን ውጣ-ውረዶች እና የተጋረጡበትን ተግዳሮቶች ከህዝበ-ሙስሊሙ አብራክ በወጡ ምሁራን በማስፈተሽ እና በማስጠናት ጠንካራ እናደካማጎኑንአንጥሮ መለየት እና ሰፊውን ሙስሊም በሂደቱ ማሳተፍ ለዘላቂ ሁሉን-አቀፍ መፍትሄ ሁነኛ ዘዴ መሆኑን በማመን፤

በሕገ-መንግስቱ እውቅና የተሰጠውን የእምነት ነጻነት፣ በመንግስት ዘንድ የሃይማኖት እኩልነት እና የሴኩላር ሥርዓት መርሆዎች አፈጻጸም ላይ የተስተዋሉትን ጉልህ ጉድለቶች ለመቀነስና እና ትግበራቸውን ለማሻሻል የወቅቱ የሪፐብሊኩ መንግስት ተጨባጭ እንቅስቃሴዎች ማድረግ መጀመሩን በማበረታታትና የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ እንዲመሰረት ኃላፊነት የተሞላበት እገዛ ማድረጉን በማድነቅ፤የተቋማዊ ለውጥ ኮሚቴውም ከመጅሊስ አመራሮች፣ከአንጋፋ ዓሊሞች፣ ከማህበረሰቡና ከባለ ድርሻ አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የጋራ ተቋሙ (መጅሊስ) ከሀገራዊው ለውጥጋር የተናበበ ተመጣጣኝ አመለካከት፣ ስያሜ፣ አደረጃጀት፣ አወቃቀር እናቁመና እንዲኖረው ለማስቻል ፋታ-የለሽ ያለሰለሰ ጥረት ማድረጉን በአግባቡ በመገንዘብ፤

ይህመንፈሳዊ ድርጅት የሀገራችን የሕግ ማዕቀፎችና አበይት ፖሊሲዎች የያዙትን ትሩፋት በተሟላ  አኳኋን እንዲጠቀምና በሕገመንግስቱ የታመነው ከታሪክ የተወረሰ የተዛባ ግንኙነት ትቶት ያለፈው ሁለገብ ጠባሳን አክስሞ ተግባራዊ እኩልነት፣ሀገራዊትድግና እና ህዝባዊ ብልጽግናለማስገኘት የማህበረሰቡን የትጋትና የጥናት ውጤት ሥራ ላይ ማዋል ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን በማመን፤
የሉዓላዊው እና የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አካል የሆነው ሰፊው ሙስሊም- ማህበረሰብ እንደ ማንኛውም ዜጋ ከሚያስተዳድረው መንግስት እና ሀገር ከሚጋራው ማሕበረሰብ ጋር በተፈጥሯዊ

ቁርኝት የተፈጠረውን ዜግነታዊ ትስስርና ሰብዓዊ ጉድኝት ለማሳለጥ እና ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በሚኖር መስተጋብር በስኬታማ ውክልና ጠንካራና አውራ ሰብሳቢ ተቋም ሆኖ የአስተባባሪነት ሚናውን እንዲወጣ የህዝበ ሙስሊመን አመኔታና ሕገ መንግስታዊ ይሁንታ ማግኘት ቁልፍ መሳሪያ መሆኑን በማጤን፤

አውራ ተቋሙ በህዝባዊ ቅቡልነት እንዲዋጅና የተከታዮቹን አመኔታ እንዲላበስ በኢስላማዊ ፖሊሲ በመመራት በየደረጃው ያለው የማንኛውም የመጅሊስ አገልጋይና አባል መላ ሙስሊምን በሸሃደተይን ገመድ ያለመድሎ የሚያስተሳስር፣ በመሃባ የሚያቅፍ እና በኢስላማዊው መርህ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በውሳኔ ሰጭነት የሚያሳትፍ ተቋማዊ ሥርዓት መዘርጋት መሰረታዊ ፍላጎት መሆኑን በመረዳት፤

ይህንኑ ዓላማ ለማሳካትም ተቋሙ በሃይማኖታዊ ዒልም፣በዓለማዊ ዕውቀት እና በጥልቅ ግንዛቤ የደረጀ፣ለልዕለ ሃያሉ ጌታ የተገዙ እና ለወከሏቸው ሙስሊሞች የታመኑ አገልጋይ ስብዕናዎችን ብቻ እንዲያቅፍ አድርጎ መቅረጽ ወሳኝ መሆኑን በማወቅ፤

በሥራ ላይ የነበሩትን የቀድሞ ሕገ-ደንቦችና መተዳደሪያ ሕግ-ነክ ሰነዶች ተቋማዊ እንደራሴው የሚጠበቅበትን ከባድ አደራ እና ከፍተኛ ሀገራዊ ኃላፊነት በልማታዊ ስሜትና በማይባክን ምጥን ህዝባዊ ሀብት ለመከወን በሚያስችል አኳኋን መደራጀት እንዳለበት በማስታወስ፤

መላው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በሃይማኖታዊ እንደራሴዎቻቸውና በበቁ ዓሊሞቻቸው በኩል አዲሱ መጅሊሳቸው በአላህፈቃድና ችሮታ ይተዳደርበት ዘንድ ይህንን ሕገ-መጅሊስ በቀድሞው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ .. ፣ በሪፐብሊኩ ሕገመንግስት አንቀጽ 27(2) እና ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው ድንበር ዘለል የሰብአዊ መብት የቃልኪዳን ሰነዶች መሰረት እንደ ሀገራችን አቆጣጠር በዛሬው ዕለት ….፤… ቀን 2011(E.C) ወይም … ቀን 1440ዓ.ሒ. በአዲስ አበባ በተደረገ ጉባኤ ….. ድምጽ ፀድቋል።

## ክፍል - ፩ - አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1
### አጭርርዕስ

ይህ ሕገ-መጅሊስ በ1967 የተመሰረተውንና በ1988 እንደገና የተደራጀውን የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ም/ቤት ለማጠናከር እና መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል የወጣ "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ሕገ-መጅሊስ ቁ.1/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2
### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህሕገ-መጅሊስ መሰረት፦

1. "መጅሊስ" ማለት በየደረጃው የሚገኝ "የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ምክር ቤት" መዋቅር የወል መጠሪያ ነው።
2. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት የህዝበ ሙስሊሙ ተመራጭ እንደራሴዎች፣ተሿሚ የመጅሊስ ሃላፊዎች፣ የዑለማ ምክር ቤት አባል አሊሞችና የባለድርሻ ሙስሊም አካላት ተወካዮች በተሰብሳቢ አባልነት አቅፎ በየደረጃው የመጅሊስ መዋቀር የተደራጀ የየእርከኑ ከፍተኛው የስልጣን አካል የሆነ ጉባኤ ነው።
3. "ቋሚ ጉባኤ" ማለት የሙስሊሙ ቀጥተኛ ተመራጭ እንደራሴዎች፣የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ አባላት፣የመስጅድ ዑለማ ንዑስ ጽ/ቤት አባል አሊሞችና የባለድርሻ ሙስሊም አካላት ተወካዮች በተሰብሳቢ አባልነት አቅፎ በአካባቢ መስጅድ ጠቅላላ ጉባኤ የተሰየሙ በታችኛው መጅሊስ ብቻ የተደራጀ ከመስጅድ አካባቢ ነዋሪ ሙስሊሞች ጠቅላላ ጉባኤ ቀጥሎ ከፍተኛው የስልጣን አካል የሆነ ጉባኤ ነው።
4. "የሥራ አመራር ቦርድ" ማለት በዚህ ሕገ-መጅሊስ በተደነገገው አኳኋን ከመጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል ከፍተኛ የሥራ አመራሮችን፣ የአማካሪ ቦርዱን፣ ዋነኛ የሥራ ፈጻሚ ተቋማትን እንዲቆጣጠርና በየምርጫ ዘመኑ በቋሚነት እንዲያገለግል የሚመረጥ በሀገራዊ ደረጃ ዘጠኝ በክልል መዋቅር ደግሞ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላትን ያቀፈ ዋና የቁጥጥር አካል የሆነ ቦርድ ነው።
5. "የአስተዳደር መዋቅር" ማለት ማዕከላዊነትን የሚያሳየውን የብሄራዊው ላዕላይ መዋቅር እና የመጨረሻው እርከን የሆነውን የአካባቢ መስጅድ መዋቅርን ጨምሮ በኢትዮጵያ የፌዴራልና የክልል መንግስታት ሕጎች ለአስተዳደር መዋቅርነት በየአካባቢው እስከ ወረዳ ከተዘረጋው የመዋቅር እርከን ጋር በትይዩ የተደራጀ ሲሆን የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር፣ የዞን ወይም የልዩ ዞን ወይም የክ/ከተማ፣ የወረዳና የልዩ ወረዳ የአስተዳደር እርከኖችን ያካትታል።
6. "ሙስሊም" ማለት በደፈናው (በሙጥለቅ) ኢስላምን በእምነትነት የተቀበለ ወይም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆነ በተለይም የአላህን ብቸኛ አምላክነት ተቀብሎ በነብዩ ሙሐመድ(ሰለሏሁ

ዓለይሒ ወሰለም) የመጨረሻ የአላህ መልእክተኛነትና ነብይነት አምኖ የመሰከረ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

7. "የኢትዮጵያ ሙስሊም ወይም ምዕመን" ማለት የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ወይም ትውልደ-ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም ከኢትዮጵያዊ የተወለደ ወይም ከትውልደ ኢትዮጵያዊ የተወለደ ሙስሊም ሆኖ የመጅሊስ አገልግሎት ከማግኘት አኳያ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖርን ማንኛውንም ሙስሊም ይጨምራል፡፡
8. "ጀመዓ" ማለት ከመስጅድ ጀምሮ በየአስተዳደር መዋቅሩ የሚገኝ ወይም የሚኖር የሙስሊም ማህበረሰብ ነው፡፡
9. "መስጅድ" ማለት በመላ ሀገሪቱ የሚገኝ ቋሚ ኢማም ወይም አሰጋጅና ሙአዚን ያላቸው፣ አምስት ወቅት ሶላት ለሁሉም ሙስሊም ክፍት ሆነው ሶላት ወይም ስግደት የሚከወንበት ኢስላማዊ የአምልኮ ቦታ ሆኖ በመጅሊስ፣ በተቋማጽ፣ በወቅፍ እና በግለሰቦች የሚተዳደሩትን የሚጨምር ሲሆን በዚህ ሕገ-መጅሊስ ለተደነገገው የታችኛው የመስጅድ የመጅሊስ መዋቅር ለማደራጀት ግን በሥራ ቦታዎች፣በምግብ ቤቶች፣ በትምህርት ተቋማት፣በአውሮፕላንና በሌላ የትራንስፖርት ጣቢያዎች፣በእስር ቤቶች፣ በመስሪያቤቶች እና በኢምባሲዎች የሚገኙ መስጅዶችን አያካትትም፡፡
10. "የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ" ማለት በኡማውና በእስልምና ጉዳዮች ዙሪያ ከወረዳ መዋቅር በታች የሚገኝና የሙስሊም ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚደረግበት በአንድ መስጅድ አካባቢ የሚኖሩ ሙስሊሞች ተሰባስበው በጠቅላላ ጉባኤ አባልነት የታቀፉበት የመጅሊስ የመጨረሻውና ለማህበረሰቡ ቅርብ የሆነው የታችኛው እርከን ነው፡፡
11. "የሙስሊሙ ወይም የጀመዓው እንደራሴ" ማለት የአካባቢ መስጅድ የመጅሊስ እርከን የጠቅላላ ጉባኤ አባል ህዝበ-ሙስሊም ወይም አጠቃላይ ጀመዓ ከአባላቱ መካከል እንዲወክላቸው የሚመርጡት የምዕመናን ወኪል ሲሆን በእየእርከኑ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ እየተመረጠ በሀገራዊው መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ አባል የሆነንም ተመራጭ ያካተተ የህዝበ ሙስሊሙ እንደራሴ ወይም ወኪል ነው፡፡
12. "ኢስላማዊ ቦታ ወይም ተቋም" ማለት መስጅድ፣መድረሳ፣የእስልምናጉዳይ የሚከወንበት ጽ/ቤት፣ ቁርአን ቤት፣ የአውቃፍ ተቋማት፣ ኢስላማዊ የምርምር፣ የጥናትና የባህል ማዕከል፣ የገጠር ዛውያ፣ ሃሪማና ኸላዋ፣ እስልምናን መሠረት ያደረገ የልማት ድርጅት ወይም የሲቪክ ማህበር ይዞታ፣ኢስላማዊ እድር፣መረዳጃ እና መሰል ቦታን እና ተቋማትን ያጠቃልላል፡፡
13. "የመጅሊስ ንዑስ ተቋም" ማለት በየደረጃው ባለው የመጅሊስ የአስተዳደር፣የልማትና የተራድኦ መዋቅር የተመሰረቱና የየራሳቸው የተደራጀ አመራርና የመጅሊስ አስተዳደር ያላቸው ተጠሪነታቸው እና ባለቤትነታቸው በየደረጃው ለሚገኝ የአስተዳደር መዋቅር ወይም ለሀገራዊው መጅሊስ የሆኑ መንፈሳዊ ማህበራትና የመረዳጃ ስብስቦች፤ ዘመናዊና ባህላዊ የአዳሪና የተመላላሽ ሃይማኖታዊ የትምህርት ተቋማት፤ የገጠር የቀርዓት ማዕከሎች፤ ዛውያዎች፣ ቋሚ የመንፈሳዊ ስልጠና እና የዒልም ቦታዎች (ኸልዋዎችና ሃሪማዎች)፤ የልማትና የተራድኦ ድርጅቶች፤

ኢስላማዊ የኪነጥበብ፣የመዝናኛና የሚዲያ ተቋማት፤ የዘካ፣የወቅፍ፣ የሂባ እና የወስያ ማዕከሎች፤ እንዲሁም ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን ሌሎች በስሩ የሚገኙ ሃይማኖታዊ አደረጃጀቶችን ይጨምራል፡፡

14. “ፈትዋ” ማለት በህብረተሰቡ ውስጥ ለሚነሱ ሃይማኖታዊ ጥያቄዎች የሃይማኖቱን መሠረታዊ ምንጮች መሰረት በማድረግና ኢስላማዊ አስተምህሮቶችን በግብአትነት በመጠቀም በዓሊም ወይም ዑለማ(የሃይማኖት ሊቃውንት) የሚሰጥ ኢስላማዊ ብይን ነው፡፡
15. “ወቅፍ” ማለት ማንኛውም በጎ አድራጊ ሰው ወይም ተቋም ወይም ድርጅት ንብረቱን ወይም ከንብረቱ የሚገኝን ጥቅም ወይም ፋይዳ በቅድሚያ ተለይተው ለተጠቀሱ ተጠቃሚዎች ወይም የአጠቃቀም ሥርዓቶች ለአገልግሎት እንዲውል ስጦታ የሚደረግበት ኢስላማዊ ሥርዓት ነው፡፡
16. “ዘካት” ማለት ማንኛውም ሙስሊም በህጋዊ መንገድ ካፈራው ከሚንቀሳቀስና ከማይንቀሳቀስ ሀብትና ንብረቱ ላይ በሃይማኖቱ በተደነገገው መጠን፣ሥርዓትና ጊዜ ለሚገባቸው ወገኖች የሚሰጥ የአምልኮ አካል የሆነ የግዴታ ገንዘብ ነው፡፡
17. “ሰደቃ፣ሂባ፣ወሲያ” ማለት ሙስሊሞች በግልም ወይም በጋራ በህይወት ዘመናቸው ወይም ከህልፈታቸው በኋላ ተፈጻሚ የሚሆን ለበጎ አድራጎት እና ለመሳሰሉት ሰብዓዊ ዓላማዎች ድጋፍ የሚያደርጉባቸው ግዴታ ያልሆኑ የተለያዩ ኢስላማዊ የንብረት ልገሳ ወይም የስጦታ ሥርዓቶች ናቸው፡፡
18. "ሪፐብሊክ" ማለትየኢትዮጵያፌዴራላዊዴሞክራሲያዊሪፐፐሊክነው፡፡
19. "ሕገ-መንግስት" ማለት የሪፐብሊኩ ሕገ-መንግስት ነው፡፡
20. "መንግስት" ማለት በግልጽ የሌላ ሀገር ስለመሆኑ ካልተገለጸ በስተቀር እንደ ሁኔታው በሪፐብሊኩ የተቋቋሙት የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መንግስት ማለት ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ መስተዳድሮችና በውጭ ሀገር የሚገኙ የሪፐፐሊኩ ኢምባሲዎችንም ይጨምራል፡፡
21. "ክልል" ማለት በሕገ መንግስቱ የተጠቀሱትና አግባብ ባለው ሕግ ወደ ፊት የሚፈጠሩት የሪፐብሊኩ አባል ክልሎች ሲሆኑ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ መስተዳድሮችንም ይጨምራል፡፡
22. "ተግባር (action)" ወይም "ሥራ" ወይም "ድርጊት" ማለት አንድን ነገር መፈጸምን ወይም ማድረግን (commission) እና ከመፈጸም ወይም ከማድረግ መቆጠብንም (omission) ያካትታል፡፡

## አንቀጽ 3
## ስያሜ እና ዳግም ምስረታ

1. "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት" በአጭር አጠራር "ሀገራዊ መጅሊስ" በኢትዮጵያ እስልምናን እና ሙስሊሙን በሚመለከት በመጅሊስ መዋቅር የተሟላ መንፈሳዊ ስልጣንና ኃላፊነት ያለው የህዝበ ሙስሊሙ የበላይ የሃይማኖት አስተዳደር ተቋም ሆኖ በአዲስ ገፅታ ተደራጅቶ ተቋቁሟል፡፡
2. በሪፐብሊኩ አባል ክልሎችና በየአስተዳደር መዋቅሩ በዚህ ህገ-መጅሊስ መሰረት የተቋቋሙት የአስተዳደር እና የኡለማ መዋቅር ያላቸው የመጅሊስ እርከኖች በሚገኙበት የአስተዳደር ክልል ውስጥ እስልምናን እና ሙስሊሙን በሚመለከት በዚህ ሕገ-መጅሊስ በተደነገገው የስልጣን ክልል ውስጥ የተሟላ መንፈሳዊ ስልጣንና ኃላፊነት ያላቸው ላዕላይ የሃይማኖት አስተዳደር ተቋማት ሆነው ተደራጅተዋል፡፡
3. በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ ሙስሊም ዜጎች በየመኖሪያ አካባቢያቸው በሚገኝ መስጅድ በአባልነት ተመዝግበው የጠቅላይ ጉባኤ አባል የሚሆኑበት የ "አካባቢ መስጅድ ነዋሪ ሙስሊሞች ምክር ቤት" የመጅሊስ የመጨረሻው ታህታይ እርከን ሆኖ በዚህ ህገ-መጅሊስ የተቋቋመ ሲሆን መስጅድ በሌለበት አካባቢ የሚኖሩ ሙስሊሞች ደግሞ በሚኖሩባቸው ቦታዎች "የመስጅድ አልባ ሙስሊም ነዋሪዎች አካባቢያዊ ምክር ቤት" አቻ የመጨረሻ የመጅሊስ ተተኪ ጊዚያዊ እርከን ሆኖ በተመሳሳይ ስልጣን ተቋቁሟል፡፡

## አንቀጽ 4
## የሕግ ሰውነት

1. ሀገራዊው መጅሊስና እስከታችኛው የአካባቢ መስጅድ ድረስ የተደራጀው የአስተዳደር መዋቅር እንዲሁም በመጅሊስ ሥር የታቀፉ ተቋማት እና ንዑስ  ተቋማት በተለይም መስጅዶች፤ የገጠርና የከተማ ኢስላማዊ ማዕከሎች፤ ራሳቸውን ችለው የተቋቋሙ የተመላላሽና የአዳሪ የዒልም(የእውቀት) እና የመንፈሳዊ ሰልጠና ቦታዎች(የደረስነት ዛውያዎች እና ኸልዋዎች)፤ በየእርከኑ የተቋቋሙ የመጅሊስ ጽህፈት ቤቶች እና የእስልምና ጉዳይ ምክር ቤቶች ወይም ጉባኤዎች እና ተመሳሳይ የአስተዳደር መዋቅሮች፤ በመጅሊሱ ሥር የተቋቋሙና የሚቋቋሙ መንፈሳዊ ማህበራት እና ዘመናዊ እና የሚሲዮን የእስልምና ትምህርት ቤቶች ወይም መድረሳዎች እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፤የወቅፍ፣የዘካ፣የወስያና የሂባ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የልማትና የተራድኦ ተቋማት አደረጃጀቶች፤ሃይማኖት ቀመስ ሙዚየሞችና የባህል ማዕከሎች እንዲሁም መሰል በሕግ-ነክ ሰነዶቹ የተደነገጉ አደራጃጀቶች በሪፐብሊኩ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1)፣ 27፣ 31 እና  38(4) ከእነዚሁ የሀገሪቱ የበላይ የሕግ ሰነድ ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥመው በሚተረጎሙት በ1952 በወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ መጽሐፍ ፩ አንቀጽ ፫ ምዕራፍ ፩ ቁጥር 398 እና 399 ድንጋጌዎች፣እንዲሁም በክልልና በፌዴራል መንግስት የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጆች በተለይም በፌዴራሉ አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 17(1)(2) እና የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 110/1992

አንቀጽ 11(7) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መሰረት በም/ቤቱ መዋቅር ስር ሆነው በተቋቋሙበት ደንብ ወይም ህግ ነክ ሰነድ በተሰጣቸው የስልጣን ክልል በተናጠል ራሳቸውን የቻሉ የሕግ ሰውነት ያላቸው አካላት ሆነው ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁመዋል።

2. መጅሊስ የየአስተዳደር መዋቅሩን እና ንዑስ ተቋማቱን በሚመሩሃላፊዎች ወይም ሃላፊዎቹ ደንቡንና ሥርዓቱን ተከትለው በሚወክሏቸው አመራሮችና ነገረ--ፈጆች ተወክለው በሕግ ሰውነቱ ይገለገላሉ፤ በተለይም ይከሳሉ፣ይከሰሳሉ፣ንብረት ያፈራሉ፣ይዋዋላሉ፤ ከሌሎች ሰዎችና ተቋማት ጋር ይጻጻፋሉ፤በዚህ ህገ-መጅሊስ በተሰጣቸው የስልጣን ክልል ውስጥ በህግ ውጤት ያላቸው ሌሎች ተግባራትን (Juridical Act) ይፈጽማሉ።

3. የድርጅቱ ማህተሞችም፣አርማዎች፣ማስታወቂያዎችም ሆኑ የተቋሙ ስም የሚወሳባቸው ማናቸውም ጉዳይና ሰነድ በዚህ ሕገ-መጅሊስ የተደነገገውን የተቋማቸውን መጠሪያ ብቻ ይገለገላሉ።

4. በሪፐብሊኩ እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን የሚገኙት የመጅሊስ መዋቅሮች፣ አባል ተቋማት እና ንዑስ ተቋማት በንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው አኳኋን በዚህ ሕገ-መጅሊስ በተሰጣቸው ስያሜ ብቻ ይጠቀማሉ፤ይገለገላሉ።

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አናቅጽ ድንጋጌዎች መጅሊስ በባለቤትነት ያልያዛቸውን ሌሎች ኢስላማዊ ተቋማት እንዲይዝ ወይም ባለቤት እንዲሆንባቸው ስልጣን አይሰጥም።

## አንቀጽ 5
## የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

1. የቀድሞው "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ም/ቤት" እና "የኡለማ ም/ቤት" ማናቸውም መብትና ግዴታዎች በዚህ ሕገ-መጅሊስ ተተክተው ለተደራጁት "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት" እና ለአቻ "የኢትዮጵያ ኡለማዎች ምክር ቤት" ተላልፏል።

2. የቀድሞው የክልል እና የከተማ መስተዳድር የእስልምና ጉዳይ ከፍተኛ ምክር ቤቶች እና የበታች መዋቅራቸው የነበሩ ማናቸውም ከአንድነት እና አካታችነት የማይጻረሩ መብትና ግዴታዎች በዚህ ሕገ-መጅሊስ እንደገና ለተደራጁ ትይዩ የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር፣ የዞን ወይም የልዩ ዞን ወይም የክፍለ ከተማ እንዲሁም የልዩ ወረዳ ወይም የወረዳ አቻ የመጅሊስ መዋቅሮች ተላልፏል።

3. ከዚህ በፊት በወጡ ሕጎች እና በተደረጉ አሰራሮች ስለ ቀድሞዎቹ የእስልምና ጉዳይ ጉባኤዎች ወይም ምክር ቤቶች የተደነገጉና የተሰጡ መብትና ጥቅሞች እንደ አግባብነቱ በዚህ ሕገ-መጅሊስ በተተኩበት አኳኋን ለአቻና ለትይዩ መዋቅርና ተቋም ተተክተው ያገለግላሉ።

## አንቀጽ 6
## ዓርማ

1. ሀገራዊው መጅሊስ የተቋሙን ዓላማ፣ እሴትና ራዕይ የሚያንጸባርቅ የራሱ ዓርማ ይኖረዋል።
2. ዓርማው የሚከተለው ዝርዝር ይዘት ይኖረዋል፦

ሀ. በክብቀለበትውስጥ ሶስት ሚናራዎችያለው የመስጅድ ምስል።

ለ. የቁርዓን ምስል ኖሮት በመስጅዱ ምስል ክብ አናት ላይ "ቢስሚላሂ አረህማኒ አረሂም" የሚል የተጻፈበት::

ሐ. በቁርአኑ ምስል ግራና ቀኝ የዘንባባ ዝንጣፌ ያለው ነው::

3. የዓርማው ትርጉምም:-

ሀ. ክብ ቀለበቱ ዓለምን የሚያመለክት ሆኖ እስልምና ዓለም አቀፍ ሃይማኖት መሆኑን ይጠቁማል::

ለ. የመስጅድ ሚናራዎች የኢስላም ዋነኛ መነሻናመሠረትመስጅድመሆኑንናበመስጅድና በአምልኮ ቦታዎች የሚደረግ የዒባዳ ተግባርና ክንውን አላህን ብቻ በመገዛት የሚፈጸም መሆኑን ያሳያል::

ሐ. በቁርኣኑ ምስል ላይ "በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ" የሚል ትርጉም ያለው የአረብኛ ጽሑፍ መቀመጡ ኢስላም ለመላው የሰው ዘርና ፍጡራን መለኮታዊ እዝነት መሆኑን በማመላከት ኢስላም ለሁሉን-አቀፍ ፍቅር፣ለሰብአዊ ወንድማማችነትናለአብሮነትያለውንየላቀ ተቀዳሚ ቦታ የሚያሳይ ነው::

መ. ከቁርኣኑ ምስል ግራና ቀኝ የሚታዩ ትይዩ ሁለት የዘንባባ ዝንጣፊዎች የኢስላም ኃይማኖታዊነት በእምነትና በልማት ጣምራሁለገብ ብልጽግና እና ትድግና ላይ አተኩሮ የሚንቀሳቀስ መሆኑን እና አብይ ሚናውና ገጽታው ከሠላም አመንጭነት ተፈጥሯዊ ባህሪው ተነጥሎ እንደማይታይ ያመላክታል::

### አንቀጽ 7
### የዋና መስሪያ ቤትና የክልላዊ እርከን መቀመጫ እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መገኛ

1 የሀገራዊው መጅሊስ ዋና መቀመጫ የሪፐፕሊኩ ዋና መናገሻ ካልተቀየረ በስተቀር አዲስአበባ ሲሆን የከተማ መስተዳድር፤ የክልል፤ የዞን፣ የልዩ ወረዳና የወረዳ መጅሊስ መቀመጫ ደግሞ የየመዋቅሩ አስተዳደር ዋና ከተማ ሲሆን የአካባቢ መስጅድ መጅሊስ ደግሞ የመስጅዱ ቅጥር ግቢ ነው::

2. የመስጅድ አልባ ሙስሊም ነዋሪዎች የአካባቢመጅሊስ የሥራመከወኛ ቦታ በአቅራቢያው ወይም በአካባቢው በሚገኝ ምቹ በሆነ ቢሮ ወይም ጽ/ቤት ወይም ተመሳሳይ ቦታ በጊዜያዊነት ይጠቀማሉ::

3. ሀገራዊ መጅሊሱ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ሁኔታዎች ሲፈቅዱ በዚህሕገ-መጅሊስ በተደነገገው አኳኋን ከሀገርውጪ የዲያስፖራ ኢትዮጵያዊ ሙስሊሞች ቅርንጫፍ የመጅሊስ ጽ/ቤት ሊከፍት ይችላል::

## ክፍል ፪
## መሰረታዊ መርሆዎችና ዓላማዎች

### አንቀጽ 8
### ተቋማዊ ተልዕኮ

መጅሊስ እንደ አሰባሳቢ መሪ ተቋም በኢስላማዊ አስተምህሮት የሚመራ፣በሥነምግባር የታነፀ፣ ከአድሎ የጸዳ እና ችሎታን መሰረት ያደረገ ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የተደራጀ፣

ንቃተ-ህሊናው የዳበረ እና ብቁ ሙስሊም ማህበረሰብ በመፍጠር የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞችን የማስከበር ተልዕኮ አለው።

## አንቀጽ 9
## ተቋማዊ ራዕይ

የመጅሊስ ተቋማዊ ራዕይ ኃላፊነትን የሚሸከም እና አንድነቱን የጠበቀ፤ ኢስላምን የሚኖር፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነቱንያጠነከረ እና በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ልማት የሚሳተፍ ንቁ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ማህበረሰብ በአላህ ፈቃድ ተፈጥሮ ማየት።

## አንቀጽ 10
## አብይ እሴቶች

መጅሊስ ተቋማዊ ተግባራቱን የሚያከናውነው የሚከተሉትን አብይ እሴቶች መሰረት አድርጎ ነው፡-

1. መንፈሳዊነት፡- ከአላህ ምንዳ መፈለግንና ኢስላማዊ ኃላፊነትን መወጣትን ማዕከል በማድረግአገልገሎትመስጠት፤
2. አገልጋይነትና በጎ-ፈቃደኝነት፡- በአገልጋይነት መንፈስና በበጎ-ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ አገልግሎት መስጠት፤
3. እኩልነትና ፍትሃዊነት፡- ሕዝበ ሙስሊሙን በእኩልነትናበፍትሃዊነትመንፈስማገልገል፤
4. ልህቀት፡- በላቀ የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥራን ማከናወን፤
5. ትብብርናወንድማማችነት፡- በኢስላማዊ መተሳሰብ፣ ትብብር እና ወንድማማችነት መንፈስ መሥራት፤
6. ታማኝነት፡- ሕዝበ ሙስሊሙን በጽናትና በታማኝነትማገልገል፤
7. አደራጠባቂነት፡-በአደራ ጠባቂነትና በአማና ስሜት ማገልገል፤
8. አካታችነትና አሳታፊነት፡- ከአግላይነት በፀዳ መልኩ ሁሉንም ሙስሊሞች አካታችነትን፣ አቃፊነትን እና አሳታፊነትን የተላበሰ ተቋማዊ አሰራርን መተግበር፤
9. ግልፅነትና ተጠያቂነት፡- አገልግሎትን በግልፅነትና በተጠያቂነት መንፈስ መሥራት ናቸው።

## አንቀጽ 11
## ተቋማዊ የአሰራር መርሆዎች (Principles)

መጅሊስ የሚከተሉትን አጠቃላይ የአሰራር መርሆዎች መሰረት በማድረግ ተግባራቱን ያከናውናል፡-

1. ቁርኣንና ሀዲስን፤ ኢጅማእና ቂያስን መሰረት አድርጎና ተከትሎ መተግበር፤
2. ከፖለቲካዊ ዓላማ እና ከየትኛውም ወገንተኝነት የጸዳ ሃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ ተግባራትን ማከናወን፤
3. ኢስላማዊ ሥነ-ምግባሮች እና እሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲሰርፁ በአርአያነት መሥራት፣
4. በዚህ ሕገ-መጅሊስ የተጣለበትን መንፈሳዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ሰብዓዊ አገልግሎት ለማህብረሰቡ የመስጠት ኃላፊነት በመወጣት አገልግሎቱን ለሰፊው ህዝብ ለማድረስ ለማህበረሰቡ ቅርበት ላላቸው የታችኛው የመጅሊስ መዋቅር ሰፋ ያለ ኃላፊነትና ሥልጣን መስጠት፤

5. ሙስሊሙ ማህብረሰብ ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር የሚኖረው ግንኙነት በመከባበር እና በአብሮነት መርህ ላይ የተመሰረተ መሆኑን በመቀበል ይህ እሴትም እንዲዳብር ግንባር ቀደም ሚና መወጣት፤
6. ድህነት ቅነሳ፣ የሀገሪቱን ሰላም መጠበቅ ፣ ወንጀል መከላከልና በመሳሰሉት መላውን የሀገራችንን ህብረተሰብ የተባበረ ጥረት በሚጠይቁ መስኮች ሙስሊሙ ማህብረሰብ አርአያነት ያለው ተምሳሌታዊ ፊተኛ ሚና እንዲኖረው ማስቻል እና ማስገንዘብ ሃይማኖታዊ መርህ መሆኑን መቀበል፤
7. በሀገራችን ለዘመናት የዘለቁ ዲናዊ መሰረት የሌላቸውና ጎጂ የሆኑ ባህሎች በሂደት እንዲወገዱ ኢስላማዊ እሴቶችንና መፍትሄዎችን መሠረት ያደረገ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሥራት ሃይማኖታዊ ግዴታው መሆኑን በመቀበል፤
8. ተግባራቱን በግልጽነትና ተጠያቂነት መርህ ላይ ተመስርቶ ማከናወን እና ሙስሊሙ ማህብረሰብ በመረጠው የመጅሊስ አባል ላይ አመኔታ ባጣ ጊዜ ውክልናውን የማንሳት ሉዓላዊ ስልጣን እንዳለው ተገንዝቦ መሥራት::
9. ኢስላማዊ አንድነቱ የማይናወጥ እና እውቀትና ጥልቅ ግንዛቤ በማደርጀትኢስላማዊ እሴቱን ከትውልድ ትውልድ በላቀ ስኬት የሚያሻግር አርቆ አሳቢ ሙስሊም ማህበረሰብ በማስገኘት እሳቤ መንቀሳቀስ::

## አንቀጽ 12
## አብይ ዓላማ እና ተግባር

መጅሊስ እንደ ሃይማኖት አስተዳደር ተቋም የሚከተሉትአብይዓላማዎችና ተግባራትይኖሩታል፡-

1. በሀገሪቱ ሙስሊሞች መካከል ኢስላማዊ ወንድማማችነትን፣መተሳሰብን እና አንድነትን መገንባት የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን፤
2. ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ አገልግሎት መስጠት፣የሐጅ እና ዑምራ ጉዞ አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ከአድሎ የጸዳ እንዲሆን ማድረግ፤
3. ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ኢስላማዊ የትምህርት ተቋማትን እና መድረሳዎችን መገንባት እንዲሁም ተገቢዉን ስርዓተ ትምህርት በመቅረፅ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ማገልገል፤
4. መስጅዶችን መገንባት እና ማስተዳደር፣የዳዕዋ ፕሮግራም እና ስርዓትን ማቋቋም፣መንፈሳዊ አገልጋዮችን (ዳዒዎችን) እና ኢማሞችን ማሰልጠን፣ማብቃትና ማጠናከር፤
5. የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ መብትና ጥቅም እንዲከበር ከመንግስት ጋር በትብብር መሥራት፤
6. እስልምና ሃይማኖት በሀገራችን እንዲስፋፋ የዳዕዋ ሥራ መሥራት፤በህጋዊ መንገድ በዳዕዋ ሥራ የሚሳተፉ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን መደገፍ፤
7. ሀገራችን በምታካሂዳቸው በትምህርት፣ በፋይናንስ፣በማህበራዊ ኑሮ እና በመሳሰሉት ዘርፌ ብዙ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ተሣትፎ ይበልጥ እንዲጠናከር

የእስልምና ሃይማኖትን አስተምህሮት ገንቢ እሴቶች መሠረት ያደረገ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራት፤

8. በሀገራችን የህዝብን የተባበረ ጥረት የሚጠይቅ የተፈጥሮና ሰውሰራሽ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረርሺኝ በሽታ ሲከሰት ሙስሊሙ ህብረተሰብ የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ በአርአያነት ሊጠቀስ የሚችል የማስተባበር ሥራ መሥራት፤
9. በሰላምና በልማት ዙሪያ ከሌሎች የእምነት ተቋማት ጋር በመከባበርና በመተባበር መሥራት፣ ስለግጭት አፈታት ማስተማር፣ሙስሊሞችን በመወከል የማግባባትሥራ መሥራት(Lobby ማድረግ)፣በሙስሊሞችና ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች መካከል ሰላምንና መቻቻል እንዲጠናከር መሥራት፤
10. የእስልምና ቅርሶችን መጠበቅ፣ኢስላማዊጥናትናምርምርማድረግ፤
11. የወጣቶች፣የሴቶች፣የምሁራን፣የነጋዴዎችን የመሳሰሉ ማህበራት እንዲቋቋሙ ማገዝ፣የአቅም ግንባታ ሥራ መሥራት፣ለኢስላማዊ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ድጋፍ መስጠት፣ማስተዳደር፤
12. የሙስሊሙን ማህበረሰብ ሊያገለግል የሚችል የቀብር ቦታ ማዘጋጀትና አገልግሎት መስጠት፤
13. ኢስላማዊ እሴቶችን፣ወጎችን እና ስነ-ምግባሮችን ማስተማር፤
14. ዘካ ማሰባሰብ፣በወጉ ማስተዳደርና ፍትሃዊ ክፍፍል ማድረግ፣ወላጅ አልባ ህፃናትን፣ለችግር ተጋላጭ ልጆችን፣ አረጋውያንን፣ ባላቸው የሞተባቸው ሴቶችን፣አካል ጉዳተኞችንና ልዩ ትኩረት የሚሹ ማህበረሰቦችን መደገፍ፤
15. ኢስላማዊ እሴቶችን መሰረትያደረገ የኢኮኖሚ ስርዓት እንዲመሰረት ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ጥረት በማድረግ ሙስሊሞች በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ በእኩልነት መሳተፋቸውን ማረጋገጥ፤
16. በአምራች ኩባንያዎች ሲጠየቅ ለምግብ ምርቶችና ለአገልግሎቶች የሀላል የምስክር ወረቀት መስጠት፣ለኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲዎች እውቅናና የምስክር ወረቀቶችን መስጠት፤
17. ለህዝብ ግንኙነት ሥራ የሚረዳ ሚዲያ ማቋቋም፣ ሀላል መዝናኛዎች እንዲስፋፉ እገዛ ማድረግ፤
18. ከዓላማዎቹ ጋር አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራትና ተዛማጅ ሥራዎች ማከናወን፡፡

## አንቀጽ 13
## የህዝበ ሙስሊሙ ልዕልና

1. የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ከመንፈሳዊ እና ከሃይማኖታዊ ጉዳያቸው ጋር በተያያዘ በመጅሊስ ላይ የከፍተኛው ስልጣን ባለቤት ናቸው፡፡
2. የሙስሊሞች ከፍተኛ መንፈሳዊ የስልጣን ባለቤትነት በዚህ ሕገ-መጅሊስ በተቀመጠው አኳኋን በታችኛው እርከን በቀጥታና በተዘዋዋሪ በሚሳተፉባቸው ውሳኔዎች በእንደራሴዎቻቸው እና በኡለማቸው በኩል በሚፈጽሟቸው ሥራዎች ይተገበራል፡፡
3. ሀገራዊውጠቅላላ ጉባኤ የምዕመኑ መንፈሳዊ የሥልጣን ባለቤትነት የሚንፀባረቅበት በሀገሪቱ የእስልምና ጉዳይ ላይ ከፍተኛው የሥልጣን ባለቤት ሲሆን የክልል መጅሊስ የየእርከኑ ጠቅላላ

ጉባኤዎች በሀገራዊው መጅሊስ ለብቻ ከተያዙት የሥልጣንክልል ውጭ በሆኑትና ሀገር አቀፍ ይዘት በሌላቸው ክልላዊ የእስልምና ጉዳዮች ላይ የየእርከናቸው የመጨረሻ የሥልጣን ባለቤት ናቸው፡፡

## አንቀጽ 14
## የህዝበ ሙስሊሙ መብት እና ግዴታ

1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ አባል የሚከተሉት መብትና ጥቅሞቹ የተጠበቁና የማይገረሰሱ ናቸው፡-

1.1 በአካባቢውም በሚገኝም ሆነ በሪፐብሊኩ የግዛት ወሰን ክልል በሚገኝማናቸውም መስጂድ የአምልኮ ተግባር እና ሃይማኖታዊ ተግባር መፈጸም፤

1.2 በአካባቢው በሚገኝ በመጅሊስ ሥር ባለ መድረሳ መጠቀም፤

1.3 በተለየያ የመጅሊስ እርከንና መዋቅር የመሳተፍና መስፈርቱን አሟልቶ ሲገኝ የመምረጥና የመመረጥ፣ እንዲሁም ለመጅሊስ መጠናከር የሚረዱ ሃሳቦችን፣ አስተያየቶችን በስብሰባዎች ላይ የመናገር ወይም በጽሑፍ መግለጽ፤

1.4 በአካባቢው በሚሰሩ የመጅሊስ የልማት ተግባራት ላይ ባለው አቅምና ችሎታ መስፈርቱን ሲያሟላ ተቀጥሮ መሥራት፤

1.5 ለመጅሊስ መጠናከር የእውቀት፣ የጉልበት፣ የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፤

1.6 ማንኛውንም ሃይማኖታዊ አገልግሎት ከመጅሊሱ በህግ አግባብ ማግኘት፤

1.7 የመጅሊሱን መታወቂያ ማግኘት፤

1.8 ለሃይማኖታዊ ጥያቄዎች በተገቢው አካል ፈትዋ ማግኘት፤

1.9 የመጅሊስ ዓላማዎች መፈጸማቸውን፣መርሆዎቹ መተግበራቸውን፣ ደንብና ሥርዓቶች መከበራቸውን እና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውንን የመከታተልና መረጃ የማግኘት መብት እና ሌሎች ተዛማጅ መብትቶች አለው፡፡

2. በአንቀጽ 13 የተደነገገውን የህዝብ ልዕልና እንደተጠበቀ ሆኖ መላው ሙስሊም ማህበረሰብ በጋራና በተናጠል የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

2.1. በአባልነት በተመዘገበበት የአካባቢ መስጅድ መጅሊስ የአባልነት ወርሃዊ መዋጮ መክፈል፤

2.2. መጅሊሱ በሁሉም እርከን በሚያደርጋቸውን ሁለገብ እንቅስቃሴዎችና የልማት ሥራዎች ላይ የጉልበት እና የዱዓ እገዛን ጨምሮ በአቅም እና በችሎታው ልክ መርዳትና መደገፍ በተለይ ለልማት ዘመቻ ጥሪዎች እና ለቋሚና ተለዋዋጭ የማህበረሰብ እገዛ መርሃግብሮች ላይ መሳተፍ፤

2.3. አቅም በፈቀደ መጠን መጅሊሱ በሚያዘጋጃቸው ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ትምህርታዊ ገለጻዎችና ስብሰባዎች መሳተፍና ያገኘውን ግንዛቤና መረጃ ላልተገኙት ማስተላለፍ፤

2.4. በሙስሊሙ ማህበረሰብ መካከል ሸሪዓዊ መሠረት ከሌለው ክፍፍልና ውዝግብ ከሚፈጥር ያልተገባ ተግባር መታቀብ፤

2.5. የሙስሊም ወንድሙን ሁለገብ መብትና ጥቅም(ህይወቱን(ደሙን)፣ክብሩንና ንብረቱን) መጠበቅ፤

2.6. ይህንን ሕገ መጅሊስ፣ የኡለማ የአንድነትና የትብብር የቃል ኪዳን ሰነድ እና ሌሎች መመሪያዎችን እንዲሁም በማናቸውም የመጅሊስ አመራር፣ ኡለማና ኢማም በህግ አግባብ የሚሰጡትን ትዕዛዞች ሸሪዓውን እስካልተቃረነ ድረስ ማክበርና ለአፈጻጸማቸውን መተባበር፤

### አንቀጽ 15
### ኢስላማዊ የንጽህና ግምት(Islamic Presumption of Innocence)

1. ማንኛውም ሙስሊም ምዕመንና ጀመዓ ንጹህና በጎ አማኝ ወይም ስብስብ እንደሆነ ይቆጠራል ወይም ይገመታል።
2. ማንኛውምምዕመን ወይም ተቋም ተቃራኒ ማስረጃ ተገኝቶበት እና በኢስላም ሥልጣን በተሰጠውና ስልጣኑ በማያሻማ ሁኔታ በግልጽ በተደነገገ አካል ቀርቦ መልስ የመስጠትና የመደመጥ መብቱ በተጠበቀለት ሥርዓት በአግባቡ ተጣርቶና ተረጋግጦ አግባብ ባለው የኡለማ አካል ሸሪዓውን መሰረት አድርጎ ብይን ካልተሰጠበት በስተቀር በዚህ ሕገ-መጅሊስ በተደነገገው የተክፊር፣ የተብዲዕ እና የተዛማጅ የፍረጃ አስተሳሰቦች እና እኩይ ድርጊቶች ሰለባ ነው ማለት አይቻልም።

### አንቀጽ 16
### የሕግ የበላይነትኢስላማዊ መርህ

በየትኛውም የመጅሊስ መዋቅርና ቅርንጫፍ የሚገኝ ማንኛውም የተቋሙ አባል፣አገልጋይና ምዕመን የሚፈጽሟቸው ሥራዎችና የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች ከኢስላም መሠረታዊ ሕግጋት እና ከዚህ ሕገ-መጅሊስ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ ባጢል እና ውድቅ (Void) ሆኖ ተፈጻሚነትም አይኖረውም።

## ክፍል ፫
## የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 17
### የሕግአተረጓጎምሥርዓትናየፈትዋስልጣን

1. በዚህ ሕገ-መጅሊስ ለኡለማ ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንዲሁም ከሕገመንግስታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ የትርጉም ጥያቄዎችና አለመግባባቶች የፌዴሬሽን ምክርቤትና የሌሎች መንግስታዊ የህግ ተርጓሚ ተቋማት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከኢስላማዊ የመጅሊስ አሰራር ወይም ከሃይማኖት ለበስ አስተዳደራዊ ተግባሩ ጋር በተያያዘ የሕግ ጥሰት ተፈጽሟል የሚል የትርጉም አቤቱታ በምዕመኑ ወይም በመጅሊስ ማናቸውም አባል ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ አቤቱታ ሲቀርብ በአንቀጽ.... በተደነገገው መሰረት የመንፈሳዊ የግልግል ሸንጎ የሕግ ትርጉም እና ብይን ወይም ውሳኔ ይሰጣል።
2. በንዑስአንቀጽ 1 የተጠቀሰው የትርጉም ጥያቄ የሚቀርብበትንና የሚስተናገድበትን ዝርዝርሥነ-ሥርዓት የሀገራዊው መጅሊስ በጠቅላላ ጉባኤ መመሪያ ያወጣል።
3. በንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የሕግ አተረጓጎም ላይ መደበኛ ሕጎችና ውሎች በሚተረጎሙበት የሕግ መርሆና ፍልስፍና ጋር በማጣጣምና በማዋሃድ ለመተርጎም ተገቢውን ጥረት መደረግ አለበት።

4. ከአስተዳደራዊ መጅሊስ ነክ የትርጉም ጥያቄዎችናበመጅሊስ አሠራር ሂደት ውጭለሚነሱ ሃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ ጉዳዮች (መስአላዎች) ላይ ፈትዋ የመስጠት የማስተላለፍ ሥልጣን የኡለማ ምክር ቤት ነው።

### አንቀጽ 18
### የግንኙነት አውታር፣የመግባቢያ ልሳንና የሥራ ቋንቋ

1. ሁሉም የዓለምና የሀገራችን ሕዝቦች፣ ብሔሮችና ጎሳዎች በማንነት፣ በቋንቋም ሆነ በማናቸውም መንፈሳዊ መብትና ጥቅም እኩል ሲሆኑ በዘር፣በቀለምና በሚከተሉት ኢስላማዊ አቋም ልዩነት እና መድሎ መፈጸም የተከለከለ ነው።
2. የሁሉም ሙስሊሞች ልሳናችና ቋንቋዎች በመጅሊስና በሙስሊሙ ማህበረሰብ መካከል በተቻለ መጠን የግንኙነትና የመግባቢያ አውታር ሆነው ያገለግላሉ፤
3. የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት የሥራ ቋንቋ የሪፐብሊኩ መንግስት የሥራ ቋንቋ ነው፤ ለውጭ ሀገር ግንኙነት እንደ አግባብነቱ አረብኛን እና እንግሊዘኛን በጣምራ ወይም በተናጠል ይጠቀማል።
4. የመጅሊስፕሮጀክትፕሮፖዛሎች፣ጥናታዊ ዘገባዎችና የማስተዋወቂያ ሥራዎች ከሁለቱ ዓለም-አቀፍ ቋንቋዎች በተጨማሪ በአፍሪካ ሕብረትና በተባበሩት መንግስታት የሥራ-ቋንቋዎች እና በሌሎች በስፋት ተደራሽ በሆኑ ቋንቋዎች ሊጠቀምና ሀገራዊውን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ሊያሳልጥበት ይችላል።
5. የክልልና የበታች መጅሊስ የሥራ ቋንቋ መዋቅሮቹ የሚገኙበት የመንግስት የአስተዳደር መዋቅር የሚከተለውን የሥራ ቋንቋ የሚገለገሉ ሲሆን በሌላ ክልል ከሚገኝ የመጅሊስ መዋቅር ወይም ከሀገራዊው መጅሊስ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የሪፐብሊኩን መንግስት የሥራ ቋንቋ/ዎች የሚጠቀሙ ሆኖ አረብኛንና እንግሊዘኛን በተጨማሪነት መገልገል ይችላሉ።

### አንቀጽ 19
### የሕገ-መጅሊስ ህትመት፣ስርጭት እና አስገዳጅ ቅጅ

1. መላውምዕመንመብትናግዴታውንእንዲያውቅናከላይእስከታችባለውየመጅሊስመዋቅርወጥሥርዓትበ ማስፈን የተጠያቂነትንና የግልጸኝነት አሰራርን ለማጎልበት እንዲያግዝ ይህ የማዕከላዊ ሕገ-መጅሊስ የአማርኛ ቅጅ በተቻለ መጠን ብዙሀን ሙስሊሞች በሚናገሯቸው ሀገር በቀል ቋንቋዎች እንዲሁም በአረብኛ እና በእንግሊዘኛ ተተርጉሞ እና ታትሞ ለህዝበ-ሙስሊሙ ከህትመት ወጭው ባልበለጠ ዋጋ እየተሸጠ በስፋት መዳረስ አለበት።
2. በዚህሕገ-መጅሊስ የአማርኛ ቅጅ እና በሌሎች ቋንቋ በተዘጋጁ ቅጅዎች መካከል የትርጉም ልዩነትቢያጋጥምየአማርኛውቅጅተቀዳሚነትይኖረዋል።

### አንቀጽ 20
### የመጅሊስ የሥራ ዘመን

1. በሁሉም የመጅሊስእርከን ተመራጭ አካላት ማለትም የጠቅላላ ጉባኤ፣የሥራ አመራርና አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ የአማካሪ ኮሚቴ፣ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ፣ የዘካ አስተዳደር ቦርድና

ሌሎች የቁጥጥር  አካላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ የእንደራሴዎች ምርጫ በየአምስት ዓመቱ አንዴ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የተመራጭ ስብስብ አባል የሆነ ከሁለት የሥራ ዘመን(two consecutive terms) በላይ በተከታታይ ሊመረጥ አይችልም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በሁሉም የመጅሊስእርከኖች የኡለማ ምክር ቤት የሥራዘመንስድስትዓመትሲሆንየኡለማምርጫበየስድስትዓመቱአንዴይደረጋል፡፡
4. የምርጫ ጊዜው ከረመዳን ወይም ከሐጅ ጊዜ ጋር በመገጣጠሙ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ተጨባጭ ከባድ አስገዳጅ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው የሥራ ዘመን ወይም የእንደራሴና የኡለማ ምርጫ በማናቸውም ምክንያት ሊራዘም ወይም ሊሰረዝ አይችልም፡፡
5. የመጅሊስ የበጀት ምደባ ከማናቸውም ወጭዎች በፊት ለምርጫ ጉዳዮች ቅድሚያ መሰጠት አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ 3 በተደነገገው እጅግ አስገዳጅ ምክንያት ቢያንስ ከአንድ ዓመት በፊት ቀድሞ የሚታወቅ ከሆነ ምርጫንማስረዘምየሚቻለው በቅድሚያ ምርጫውን እስከ ሶስት ወር ጊዜ ከታቀደለት ጊዜ አስቀድሞ መፈጸም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 5 መሰረት ምርጫ የሚራዘመው ምክንያቱ ቢያንስ በጠቅላላ ጉባኤው በአራት አምስተኛ ድምጽ ሲደገፍ ሆኖ እጅግ ቢበዛ ከአንድ ዓመት ሳልበለጠ ጊዜ ብቻ ነው፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ማለት፡-

ሀ. የሀገሪቱንና የህዝቦቿን ሰላም ያናጋ ጦርነት ሲኖር፤ ወይም

ለ. ሀገር-አቀፍ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ኖሮ ቢያንስ የሀገሪቱን የቆዳ ሽፋን ሲሶውን የሚሸፍን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታወጀ ሲሆን፤ ወይም

ሐ. ከሪፐፐሊኩ ጠቅላላ ሀገራዊ የፖለቲካ ምርጫ ጋር ሲገጣጠምና በዚህ አንቀጽ ንዑስ 5 መሰረት ማስቀደም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

መ. ምርጫውን በታቀደው ጊዜ ማድረግ የማያስችል ሀገራዊ ሕግ ከወጣ ብቻ ነው፡፡

ሠ. ሌሎች ተመሳሳይ ከባድ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ፤

## አንቀጽ 21
## የመጅሊስ መዋቅራዊ አቋም

የሙስሊሞች ምክር ቤት ወይም የመጅሊስ መዋቅር ከወረዳ በታች ከአካባቢ መስጅድ ጀምሮ እስከ ማዕከል በሚደርስ የላዕላይና የታህታይ የተዋረድ መዋቅር የሚደራጅ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ በየቀጠናው የሚመሰረተውን የዲያስፖራ ማህበረሰብ መጅሊስ ቅርንጫፍን ጨምሮ እንደ ሚከተለው ተዋቅሯል፡-

1. “የመስጅድ አካባቢ”ወይም “የመስጅድ አልባ” ሙስሊም ነዋሪዎች መጅሊስ፤

2. የወረዳ ወይም የልዩ ወረዳ መጅሊስ፤

3. የዞን ወይም የልዩ ዞን ወይም የክ/ከተማ እና የዲያስፖራ ቅርንጫፍ መጅሊስ፤

4. የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር መጅሊስ እና

5. ጠቅላይ ምክር ቤት ናቸው፡፡

## አንቀጽ 22
## የክልል መጅሊስ አባላት እና የተዋረድ ስያሜ

1. በጠቅላይ ምክር ቤት ሥር የሚገኙት የክልል መዋቅሮች ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነትያላቸውሆነውከማዕከላዊውላዕላይተቋምጋርበሚጣጣምስያሜ የተደራጁ ሲሆን በሪፐፐሊኩ ሕገ-መንግስት ወይም በሀገሪቱ የህግ ማዕቀፍ የክልላዊ መንግስታት ብዛትና አወቃቀር ካልተለወጠ በስተቀር አባል የክልል መጅሊሶች፡-

ሀ. የኦሮሚያ ክልል ሙስሊሞች ምክር ቤት፣

ለ. የአማራ ክልል ሙስሊሞች ምክር ቤት፣

ሐ. የሶማሌ ክልል ሙስሊሞች ምክር ቤት፣

መ. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልልሙስሊሞችምክር ቤት፣

ሠ. የአፋር ክልል ሙስሊሞች ምክር ቤት፣

ረ. የቤኒሻንጉል ጉምዝክልልሙስሊሞችምክር ቤት፣

ሸ. የትግራይ ክልል ሙስሊሞች ምክር ቤት፣

ቀ. የሐረሪ ክልል ሙስሊሞች ምክር ቤት፣

በ. የጋምቤላ ክልል ሙስሊሞችምክር ቤት፣

ተ. የአዲስ አበባ ከተማ ሙስሊሞች ምክር ቤት እና

ቸ. የድሬዳዋ ከተማ ሙስሊሞች ምክር ቤት ሆነው በዚህ ሕገ መጅሊስ በተደነገገው አኳኋን እንደገና ተደራጅተዋል፡፡

2. ከክልል በታች ያሉት የዞን፤የልዩ ወረዳ፣ የወረዳና የአካባቢ መስጅድ እርከኖች እንደ ቅደም ተከተላቸው ክልሎቹበተጠሩበትአኳኋን የመጀሊስ መዋቅሩ ወይም እርከኑ የሚገኙበት ዞን፣ልዩ ዞን፣ ወረዳ፣ ልዩ ወረዳናየመስጅድን ወይም የመስጅድ አልባ አካባቢን ስም በማስቀደምና ሙስሊሞች የሚለውን በማስከተል የሚጠሩበት ሲሆን የዲያስፖራ ቅንጫፍም በሀገራዊው መጅሊስ ስር የሚደራጅ በመሆኑ እንደ ስፋቱና እና እንደ ግዝፈቱ የተደራጀበትን ሀገር ወይም ክፍለ-አህጉር ወይም አህጉር በቀጠና መጠሪያነት የሚጠቀም ሆኖ የሚከተለውን አስገዳጅ የአጠራር ቅርጽ ይይዛሉ፡-

ሀ. የ ….. ዞን /ልዩ ዞን(ክ/ከተማ)/ወረዳ/ልዩ ወረዳ/ሙስሊሞችምክር ቤት፤

ለ. በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሀገራዊ ምክር ቤት የ ….. ቀጠና የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ሙስሊሞች ንዑስ ምክር ቤት፤

ሐ. የ …… መስጅድ አካባቢ/አካባቢ መስጅድ አልባሙስሊም ነዋሪዎችምክር ቤት፤

## አንቀጽ 23
## አቻ ልዩ መዋቅሮች

1. በዚህሕገ-መጅሊስስ ለክልል መጅሊስ የተደነገገውሁሉ ለአዲስአበባ እና ለድሬዳዋ መስተዳደር መጅሊሶችም ያገለግላል።
2. በዚህሕገ-መጅሊስስለዞንመጅሊስየተደነገገውሁሉለአዲስአበባ እና ድሬዳዋመስተዳደር የክፍለ ከተማ መጅሊሶች ያገለግላል።
3. መስጅድበሌለበት አካባቢ የሚኖሩ ሙስሊሞችየቀበሌውንወይም የአካባቢውን የመንደር መጠሪያበመጠቀም የመስጅድ መዋቅሩን የሚተካ የመስጅድ አልባ ሙስሊም ነዋሪዎች ምክር ቤት የሚደራጅ ሲሆን በዚህ ሕገ-መጅሊስ ስለአካባቢ መጅሊስ የተነገረው ሁሉ ለዚሁ መስጅድ አልባ መዋቅርም ያገለግላል።

## አንቀጽ 24
## የዲያስፖራ ቅርንጫፍ መጅሊስ

1. ዲያስፖራኢትዮጵያውያንሙስሊሞችበብዛትበሚገኙባቸው የባህር ማዶ ሀገራት እንደሁኔታዎቹ ምቹነት ሀገርን ወይም ክፊለ-አህጉርን ወይም አህጉርን በከባቢያዊ ቀጠናነትበመጠቀም በዞንመጅሊስስልጣንናኃላፊነትልክወይም ደረጃአቅምበፈቀደመጠንበተመሳሳይየሕግሰውነት እና ይዞታ እንደ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሆኖ ማቋቋም የሚቻል ሲሆን የቀጠናው ተጠሪ የብሄራዊው መጅሊስ የጠቅላላ ጉባኤ አባል ይሆናል።
2. የሚቋቋምበት ሀገር ህግ የተለየአጠራር፣አደረጃጀትና አመራር እንዲኖር ካላስገደደ በስተቀር ስለ ለዞን መጅሊስ የተደነገገው ሁሉ እንደአስፈላጊነቱ ለዲያስፖራ ቅርንጫፍም ያገለግላል።
3. የዲያስፖራ ቅርንጫፍ ተቋማት በምዕመኑ ብዛት ልክ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ወይም ቆንጽላ ጽ/ቤት ከአንድ በላይ በሚገኝባቸው እና በዛ ያለ ሙስሊም ኢትዮጵያዊ በሚኖርባቸው ሀገሮች ከባለ ድርሻ አካላትና ከኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ተቋማትጋር በመቀናጀትና በመተባበር በወረዳ መጅሊስ የኃላፊነትና የስልጣን ደረጃ በየግዛቱ(States) ወይም በየከተማው ለዋናው ቅርንጫፍ መጅሊስ ተጠሪ የሆኑ ንዑስ ቅርንጫፎች በሀገራዊው መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ ፈቃድና ይሁንታ ሊከፈቱ ይችላሉ።
4. የዲያስፖራ ቅርንጫፍ መጅሊስ በሚገኙበት ቀጠና ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎች ወይም የመንግስት ወኪሎች ጋር በሚኖራቸው የሥራ ግንኙነት መተባበርንና መደጋገፍን መሰረት ያደረገ ሕገመንግስታዊ መስተጋብር ይፈጥራሉ።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አናቅጽ የተደነገገው የዲያስፖራ መጅሊስ ተግባራዊ ሲደረግ በሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤ በባለድርሻ አባልነትና በሥራ ፈጻሚ መዋቅሩ የተመለከተው አደረጃጀትበዚህ ድንጋጌ አደረጃጀት ይተካል።

## አንቀጽ 25
## የጠቅላላ ጉባኤዎች የሥልጣን ተዋረድ

1) ሀገራዊውጠቅላላጉባኤየመጅሊስከፍተኛው መንፈሳዊ የህግአውጭአካልነው፡፡
2) የክልል መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ የሀገር አቀፉን መጅሊስ ሕገመጅሊስ ባልጣሰ መልኩ በክልሉ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን መተዳደሪያ ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን አለው፡፡
3) የዞን ወይም የልዩ ዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ የሀገር አቀፉንና የክልሉን መጅሊስ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ ባልጣሰ መልኩ በዞኑ ተፈጻሚ የሚሆን መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡
4) የወረዳ የልዩ ወረዳ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ በዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡትን መመሪያዎች በወረዳው ተፈጻሚ የሚሆንበትን የአፈጻጸም እቅድ የማውጣት ስልጣን አለው፡፡
5) የመስጅድ ጠቅላላ ጉባኤእና ቋሚ ጉባኤ በወረዳ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ እቅዶችና ትዕዛዞችን በመስጅዳቸው ተፈጻሚ የማድረግ ስልጣን ያላቸው ሆኖ አጠቃላይ የበላይ መመሪያዎችን ባልጣሰ መልኩ በመስጅዱ አስተዳደር ኮሚቴ ምርጫ፣ በኢማም አሿሿምና በሙአዚን ምደባ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ሰጭ አካላት ናቸው፡፡
6) የየእርከኑ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤዎች አንዱ ለሌላው ተጠሪ አይደለም፡፡

## ክፍል ፬ አራት
## የጠቅላይ ምክር ቤቱ ማዕከላዊ አደረጃጀት

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

## አንቀጽ 26
## የአስተዳደር መዋቅር አደረጃጀት

የጠቅላይ ም/ቤቱ ማዕከላዊ የአስተዳደር መዋቅርየሚከተሉትን አብይ አደረጃጀቶች ያቀፈ ነው፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤ፤
2. ኡለማ ም/ቤት
3. የሙፍቲዎች ጉባኤ
4. የሥራ አመራር ቦርድ፤
5. የአማካሪ ቦርድ፤
6. የኦዲት እና ኢንስፔክሽን፤
7. የዘካ አስተዳደር ቦርድ፤

ሀ. የእቅድና ስታቲክስ ክፍል

ለ. የዘካ ሰባሳቢ ክፍል

ሐ. የዘካ ስርጭት ክፍል

8. መንፈሳዊ የግልግል ሸንጎ

9. የዋና ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤትና  ሥራ አስኪያጅ

10.ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጆች

10.1. የትምህርት፣ የኢስለማዊ ቅርሶችና ተቋማት አስተዳደር ምክትል ዋናሥራ አስኪያጅ፤

10.2. የበጎ አድራጎት እና ማህበራዊ አገልግሎት ምክትል ዋናሥራ አስኪያጅ፤

10.3. የአስተዳደር እና ልማት ምክትል ዋናሥራ አስኪያጅ

11.የህግ አገልግሎት

12.የህዝብ ግንኙነት እና ሚዲያ ዳይሬክቶሬት

13.የክልል እና ዲያስፖራ ማደራጃ ዳይሬክቶሬት

14.የአወልያ ተቋማት እና የኢትዮጰያ ሙስሊሞች የልማት ኤጀንሲ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

15.የሐጅ እና ኡምራ ዳይሬክቶሬት፤

16.የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት

17.የወጣቶች ዳይሬክቶሬት

18. በምክትል ዋና ሥራ አስኪያጆች ስር የሚታቀፉ የሥራ ክፍሎች እና ዳይሬክቶሬቶች

18.1. የመንፈሳዊ ተቋማት ዳይሬክቶሬት

18.2. የትምህርትና የእስላማዊ ቅርሶች ዳይሬክቶሬት

ሀ. የእስላማዊ ቅርሶች እና ሙዚየም አስተዳደር

ለ. የጥናት ስርጭትና ህትመት አስተዳደር

ሐ. የቤተ-መጸሃፍትና መረጃዎች አስተዳደር

መ. የትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር

18.3. የማህበረሰብ ተሳትፎና እድገት ዳይሬክቶሬት

ሀ. የማህበራትና አደረጃጀት

ለ. የማህበረሰብ አቅም ግንባታ

ሐ. የበጎ ፈቃደኞች ማስተባበሪያ

መ. የወጣቶች ጉዳይ አስተዳደር

18.4. የበጎ አድራጎት እና ማህበራዊ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ሀ. የመዝናኛ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር

ለ. የተቋማት ግንባታ ዲዛይንና ጥራት ቁጥጥር

ሐ. የልማትና የተራድኦ ድርጅቶች አስተዳደር

መ. የድንገተኛ አደጋ እርዳታ ማስተባበሪያ

18.5. የአስተዳደር እና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት

ሀ. የሰው ሃብት ልማት አስተዳደር

ለ. የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር

ሐ. የንብረት አስተዳደር

መ. የእቅድና ፖሊሲ ጥናት ጽ/ቤት

ሠ. ጠቅላላ አገልግሎት

18.6. የገቢ ማበልጸጊያ ዳይሬክቶሬት

ሀ. የወቅፍ፣ ወስያና ሂባ አስተዳደር

ለ. ኢንቨስትመንትና ፕሮጀክት አስተዳደር

ሐ. የአባላት ክፍያ አስተዳደር

18.7. የህዝብ ግንኙነት እና ሚዲያ ዳይሬክቶሬት

ሀ. የሚዲያ ክፍል

ለ. የህትመት ትርጉምና ስርጭት ክፍል

ሐ. ሀገር አቀፍ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል

መ. ዓለም አቀፍ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል

18.8. የክልል እና ዲያስፖራ ማደራጃ ዳይሬክቶሬት

### አንቀጽ 27
### የሀገር አቀፍ ኡለማ ምክር ቤት አደረጃጀት

የጠቅላይ ምክር ቤቱ ማዕከላዊ የኡለማ ምክር ቤት መዋቅር የሚከተለው አብይ አደረጃጀት አለው፡

1. ሀገራዊ የኡለማ ምክር ቤት
2. የሙፍቲዎች ጉባኤ

2.1. ዋና ሙፍቲ

2.2. የምርምርና የፈታዋ ክፍል

3. የኡለማ አስተዳደር ጽ/ቤት

3.1. የዳዕዋ፣ ኢርሻድና ተርቢያ ክፍል

3.1.1. የዳዕዋና ኢርሻድ

3.1.2. የተርቢያ ክፍል

3.2. የተዕሊምና የሀለቃ ማስተባበሪያ

3.3. የስርዓተ-ትምህርት፣ የመጽሃፍ ዝግጅትና የብቃት ማረጋገጫ ክፍል

3.3.1. የስርዓተ-ትምህርትና የመጽሃፍ ዝግጅት

3.3.2. የብቃት ማረጋገጫ

3.4. የሸሪዓ ፍርድ ቤት ቃዲዎች ምልመላና ስልጠና ክፍል

3.5. የክልልና የዲስፖራ ኡለማ ማስተባበሪያ

3.6. የዳዒዎችና ኢማሞች ስልጠናና አስተዳደር

3.7. የሃላል ምርቶችና አገልግሎቶች ማረጋገጫ ክፍል

## ምዕራፍ ሁለት
## የአስተዳደር መዋቅር ዝርዝር አደረጃጀት

### ንዑስ-ምዕራፍ አንድ
### የኢ/እ/ጉ/ጠ/ም ቤት ጠቅላላ ጉባኤ

#### አንቀጽ 28
#### *የጠቅላላ ጉባኤ አመሰራረት*

ሀገራዊ ጠቅላላ ጉባዔ ከየክልሉ የተውጣጡና የተላኩ ተመራጭ እንደ ራሴዎችን፣ የኡለማ ምክር ቤት አባላትንና የባለድርሻ ሙስሊም አካላት ተወካዮችን ያካተተ የመጅሊስ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሲሆን በድምሩ 140 አባላትን በጉባኤ አባልነት የሚያቅፍ ሆኖ የአባላት ተዋፅኦውም፡-

1. ከየክልሉ የተውጣጡ ተመራጭ የህዝበ-ሙስሊሙ እንደራሴዎች በድምሩ 55 ሆኖ ተዋጽኦውም፡-

1.1. አዲስ አበባና ድሬዳዋን ጨምሮ የሁሉም ክልል መጅሊስ ሦስት የሥራ አመራር አባላት ማለትም ሊቀመንበር፣ምክትል ሊቀመንበር እና ዋና ጸሓፊ በድምሩ 33 አባላት፤

1.2. በሀገራችን አቆጣጠር በ1999 የተደረገውን ሀገር አቀፍ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤትን በግብአትነት በተጠቀመው መሰረት በየክልሉ ባለው የህዝበ ሙስሊም ብዛት መሰረት ለእያንዳንዱ አንድ ሚሊዮን ህዝበ-ሙስሊም ተጨማሪ አንድ ተወካይ አባል በማከል በአጠቃላይ ተጨማሪ 22 አባላት ከፍተኛ ሕዝበ ሙስሊም ከሚገኝባቸው አምስት ክልሎች የሚጨመሩ ሲሆን ተዋጽኦውም፡-

ሀ. ከኦሮሚያ ክልል ተጨማሪ 12 አባላት

ለ. ከሶማሌ ክልል ተጨማሪ 4 አባላት

ሐ. ከአማራ ክልል ተጨማሪ 3 አባላት

መ. ከደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ተጨማሪ 2 አባላት እና

ሠ. ከአፋር ተጨማሪ 1 አባላት ናቸው፡፡

1.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1.2. የተጠቀሰው ተጨማሪ አባል የሚመለመለው በክልሉ አብዛኛውን ህዝበ-ሙስሊም ካበረከቱ ዞኖች ተመራጭ እንደራሴዎች መካከል ነው፡፡

2. በጠቅላላው ያለ ሕዝብ ምርጫ የሚመጡ 63 መቀመጫዎች ድርሻ የዑለማ ሆኖ ከሀገር አቀፍ ዑለማዎች ምክር ቤት 35 አባላት፣ የተቀሩት ደግሞ አዲስ አበባና ድሬዳዋን ጨምሮ የሁሉም ክልል የዑለማ ምክር ቤት ዋናና ምክትሉን ማለትም እያንዳንዱ ክልል ሁለት ሁለት የዑለማ ምክር ቤት መሪዎች በድምሩ 22 አባላት፣ ስድስት አባላት ደግሞ ከታዋቂ የገጠር የኢልም ማእከላት በቀጥታ ይሳባሉ፡፡

3. የልዩ ልዩ ባለ ድርሻ አካላት ድርሻ 22 መቀመጫ ሆኖ ተዋጽኦውም እንደሚከተለው ነው፡-

3.1 በፌደራል መንግስቱ ከተመዘገቡ እና ከአንድ ክልል በላይ ከሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ የሙስሊሞች የልማት ድርጅቶች ህብረት (ጥምረት) 2 ተወካይ አባላት፣

3.2 ከፌደራል ደረጃ ከተመዘገቡ ኢስላማዊ ማህበራትና ተቋማት 2 ተወካይ አባላት፣

3.3 ከምሁራን ህብረት (ጥምረት) 2 ተወካይ አባላት፤

3.4 ከሙስሊም ተማሪዎች ሕብረት-ትስስር (ኔትዎርክ) 2 ተወካይ አባላት፤

3.5 ከሙስሊሙ የንግድ ማህበረሰብ ህብረት (ጥምረት) 2 ተወካይ አባላት፤

3.6 ከሙስሊም ወጣቶች ማህበራት ህብረት (ጥምረት) 2 ተወካይ አባላት፤

3.7 ከሙስሊም ሴቶች ማህበራት ህብረት (ጥምረት) 4 ተወካይ አባላት፤

3.8 ከሙስሊም የሚዲያ እና ኪነ-ጥበብ ተቋማት 2 ተወካይ አባላት፤

3.9 ከዱዓቶች ማህበር 2 ተወካይ አባላት፤

3.10 ከዲያስፖራ ሙስሊሞች ትስስር (ኔትዎርክ) 2 ተወካይ አባላትን የያዘ ነው፤

## አንቀጽ 29
## የጠቅላላ ጉባዔ አባልነት መስፈርት

ከየክልሉ በማናቸውም ደረጃ ለሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤ አባልነት የሚላኩ የሙስሊሞች እንደራሴ ተመራጮች የሚከተለውን ካላሟሉ በስተቀር በጉባኤው ለአባልነት መወዳደርም ሆነ መታቀፍ አይችሉም፡-

1. ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ሆኖ በተላከበት ክልል ነዋሪ የነበረ (ከነዋሪነት ውጭ የክልሉ ብሄር ወይም ብሄረሰብ አባል መሆን አይጠበቅበትም)፤
2. ህዝበ-ሙስሊሙን ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፤
3. በሚኖርበት የአካባቢ መስጅድ መጅሊስ የአባልነት መዋጮ የከፈለ፤
4. ቢያንስ ከመስጅድ እስከ ዞን ባለው መዋቅር ተመራጭ የሆነ፤
5. ለኢስላምና ለሙስሊሞች ታማኝ የሆነና በተቅዋ (አላህን በመፍራት) የታነጸ፤
6. በየትኛውም የመጅሊስ እርከን ላይ በኃላፊነት ተቀምጦ በስነምግባር ችግር ያልተሰናበተ ወይም በሙስሊሙ ማህበረሰብ የበረከተ ተጨባጭ ቅሬታ ቀርቦበት ከፍተኛ የዲሲፕሊን እርምጃ ያልተወሰደበት፤
7. የሞያ ብቃት ወይም ክህሎት ወይም የዒልም/የዲን እውቀት ያለው፤
8. በመልካም ስነምግባራቸውና በማህበረሰብ ዲናዊ(ሀይማኖታዊ) አገልግሎት/ኺድሚያ የታወቀ፤
9. ዑለማን ሳይጨምር ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ ቋሚ ገቢ ያለው፤
10. ዕድሜው ቢያንስ 35 ዓመት የሆነ፤
11. መሰረታዊ ሃይማኖታዊ ተግባራትን በአግባቡ የሚፈጽም፤
12. የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲና የመንግስት የፖለቲካ ተሿሚ ያልሆነ ( ሹመቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ያልሆነ ወይንም አባል ከሆነ በኂላ የፖለቲካ ወይም የመንግስት ባለስልጣን ከሆነ የጠቅላላ ጉባዔ አባልነቱን ይለቃል)፤
13. በዑለማ ምክር ቤት አባልነቱ ምክንያት የጠቅላላ ጉባኤ አባል የሆነ ዓሊም በተመሳሳይ ጊዜ አባልነቱን ካልተወ በስተቀር የመጅሊስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ወይም የጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ መሾም አይችልም።

## አንቀጽ 30
## የጠቅላይ ም/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን እና ተግባር

ሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባር ይኖረዋል፦

1. ሉዓላዊ ምዕመናን ከፍተኛውን ሃይማኖታዊ ሥልጣናቸውን በእንደራሴዎቻቸው፣በዓሊሞቻቸው እና በባለድርሻ ሙስሊም አካላቶቻቸው በኩል የሚተገብሩበት የእስልምና ጉዳዮችን በተመለከተ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ህዝበ ሙስሊሙን ለማገልገል ይሰራል። በመሆኑም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሙስሊሙን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ውሳኔ ያሳልፋል።
2. የብሄራዊ መጅሊሱን የሥራ አመራር ቦርድ እና የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴን ከአባላቱ መካከል እንዲሁም የዘካ አስተዳደር ቦርድ አባላትን ደግሞ በዚህ ህገ-መጅሊስ መሰረት ከአባላቱ ውጭ ይሾማል፣ ይቆጣጠራል፣ይሽራል፣ ሪፖርት እየሰማ እና እያጣራ አስፈላጊውን ይወስናል፤
3. ሕገ-መጅሊሱን በአንቀጽ ….. … እና …. በተደነገገው አኳኋን የማሻሻያ ሀሳብ ያመነጫል፤ ያሻሽላል ይለውጣል፤
4. በሥራ አመራር ቦርድና በሀገራዊው ዑለማ ምክር ቤት ተረቀው የሚቀርቡለትን የመጅሊስ የምርጫ መመሪያ፣ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች የህገ-መጅሊሱ ማስፈጸሚያ ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል፣ ይሽራል፣ ያሻሽላል።
5. የዑለማዎች ምክር ቤት በየክልሉ መቋቋሙን ያረጋግጣል።
6. በሥራ አመራር ቦርድ አቅራቢነት የመጅሊሱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል።
7. በሥራ አመራር ቦርድ እና በሀገራዊው የዑለማዎች ምክር ቤት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የየተቋማቸውን የበጀት ዓመት የሥራ እቅድ፣የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና ዓመታዊ በጀት ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፣ ያጸድቃል፣ የሥራ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ መመሪያ ይሰጣል፤
8. የውጪ ኦዲትና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሪፖርትን መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል።
9. በሥራአመራር ቦርድ ተጠንተው የሚቀርቡ የተለያዩ የሥራ ፕሮጀክቶችንና የልማት ትልሞችን መርምሮ አስፈላጊን ውሳኔ ይሰጣል።
10. የተቋሙ ዓላማዎች በተግባር ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
11. የኡለማ ምክር ቤት አባላትን ጨምሮ የሥነ-ምግባር ግድፈትና ጥፋት በሚፈጽሙ አባላት ላይ የመጨረሻውን አስተዳደራዊና እስከስንብት የሚደርስ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲሁም ለህግ ክፍል እና ለመንፈሳዊ ሸንጎ መቅረብ ያለባቸውን ጉዳዮች በመለየት ተገቢውን ይወስናል፤
12. የጠቅላላ ጉባዔው አባል በሞት ወይም በዕድሜ ወይም በመልቀቂያ ወይም በስንብትና በማናቸዉም ምክንያት ጠቅላላ ጉባዔውን ከለቀቀ በተሰናበቱት ምትክ የሥራ ሽግሽግ ደርጋል፤ በተጓደሉ አባላት ቦታ በዚህ ህገ-መጅሊስ በተደነገገው አኳኋን እንዲተኩ ያደርጋል።

13. መብትና ጥቅሞቹ የተጠበቁለት አንድ ወጥ አገልግሎት ለማህበረሰቡ ለመስጠት እንዲቻል በክልል መጅሊስ የሚወጡ ስትራቴጂዎች፣ደንቦችና መመሪያዎች የየአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጨምረው በፌዴራል ደረጃ ከወጡ የመጅሊስ ስትራቴጂዎች፣ደንቦችና መመሪያዎች ተቃርኖ የሌላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣በኦዲትና ኢንስፔክሽን የተቃርኖ ሪፖርት ሲቀርብለትም መርምሮ ይወስናል።

14. የክልል መጅሊሶች እነዚህን ደንብና መመሪያዎች አክብረው ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ስህተቶች እንዲታረሙ ያደርጋል።

15. ከሀገራዊው መጅሊስ የምስረታ ዓላማ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል።

## አንቀጽ 31
## የሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ በወርሃ ….. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚካሄድ ሲሆን ስብሰባውን ማድረግ የማይቻልበት ከባድ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በተያዘለት ጊዜ መፈጸም አለበት።

1.1. ከባድ ሁኔታው መኖሩ በሥራ አመራር ቦርድ እና በጠቅላላ ጉባኤው አመራሮች የጋራ ስብሰባ እስከ ሶስት ወር ለሚደርስ ጊዜ ለአንዴ ብቻ ሊያራዝሙ ይችላሉ።

1.2. ከባድ ሁኔታ የተባለው በአንቀጽ 20(8) ከተደነገገው የምርጫ ማስረዘሚያ ምክንያት መመዘኛ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

2. በጉባኤው ስብሰባ ከግማሽ በላይ የድምጽ ተሳታፊ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።

3. ጉባኤው በዋና ሙፍቲው ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ ዋና ሙፍቲ በሌሉበት ወይም ጉባኤውን መምራት በማይችሉበት ጊዜ የጠቅላላ ጉባኤው ሙፍቲ ምክትል ሰብሳቢ የጠቅላላ ጉባኤውን ይመራል።ምክትል ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ የጉባኤው ዋና ጸሃፊ የሰብሳቢነት ሚናውን ተክቶ ይሰራል።

4. ሁሉም የጉባኤው ውሳኔዎች የሚፈጸሙት በግልጽ ሆኖ የሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ ለዋና ሙፍቲ ምርጫ ካልሆነ በስተቀር አይፈቀድም።

5. የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት አጀንዳው በአግባቡ በውይይት ከተብላላ በኋላ ሆኖ በዚህ ሕገ-መጅሊስ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የአብላጫ ድምጽ መደበኛ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ በቂ ነው።

6. በውሳኔዎች እኩል ድምጽ በሚኖርበት ጊዜ የጉባኤው ሰብሳቢ ያለበት ወገን መለያ ይሆናል።

7. በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ወቅት ለውይይት የቀረበው አጀንዳ ከሙፍቲዎች ጉባኤ ወይም ከኡለማ ምክር ቤት ጋር የተያያዘ ከሆነ ጠቅላላ ጉባኤው የሚመራውበምክትል ሰብሳቢው ነው።

8. ሁሉምዓይነትስብሰባዎችናውሳኔዎች፣ ምርጫዎችናየምርጫሂደቶችኢስላማዊ አደብንና መርህን በተከተለ አኳኋን መመራትአለበት።

## አንቀጽ 32
## የጠቅላላ ጉባኤ ድንገተኛ ስብሰባ

1. ጠቅላላ ጉባኤው አስቸኳይና አጣዳፊ ድንገተኛ ጉዳይ ሲከሰትና ልዩ ጉባኤ በመጥራት ይሰበሰባል፡፡
2. የአስቸኳይ ጉባኤ ለመጥራት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች አጣዳፊና በቂ ምክንያት ናቸው የሚባለው፡-

ሀ. መደበኛ ጉባኤው እስኪደረግ ቢጠበቅ በተቋሙ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚደርስ ሲሆን፣ ወይም

ለ. ዋና ሙፍቲው በኡለማ ምክር ቤቱ ሲታገዱ ወይም መልቀቂያ አቅርበው ሲሰናበቱ፣ ወይም

ሐ. ከግማሽ በላይ የሥራ አመራር ቦርድ ወይም የዘካ አስተዳደር ቦርድ አባላት ሲለቁ፣ወይም

መ. አጣዳፊ ሀገራዊ ክስተት ሲፈጠርና በክስተቱ ምክንያት ውሳኔ ማሳለፍ አስፈላጊ እና ጉዳዩ ከሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ ስልጣን በላይ ሆኖ ሲገኝ፤

ረ. ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸው ተዛማጅ ከባድ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፡፡

3. በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ምክንያት መከሰቱ ተረጋግጦ በዋና ሙፍቲው ወይም በአራት የሙፍቲዎች ጉባኤ አባላት ወይም በስድስት የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ወይም በአንድ አምስተኛ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ወይም በአንድ ሶስተኛ የኡለማ ምክር ቤት አባላት ወይም የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ በአብላጫ አባላት ድንገተኛ ጉባኤው እንዲጠራ ከተደገፈና በፊርማቸው አረጋግጠው ለሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ እና ለጠቅላላ ጉባኤ አመራሮች በጣምራ ካሳወቁ ጉዳዩ የደረሰው አካል በጋራ ድንገተኛ ስብሰባው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚደረግበትን ቀን ወስኖ ወዲያውኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ይሁንና ድንገተኛ ስብሰባ እንዲጠራ የፈለጉት የጠቅላላ ጉባኤ አንድ አምስተኛ አባላት ከሆኑ ጥያቄውን የሚያቀርቡት ለጠቅላላ ጉባኤው አመራር አባላት ብቻ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ቅድመ ሁኔታው ሲሟላ የሥራ አስፈጻሚ ቦርዱና የጠቅላላ ጉባኤው አመራር ከስብሰባው በፊት መደረግ ያለበትን የጊዜያዊነት ባህሪ ያላቸውን ምክንያታዊ የጥንቃቄ እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

## ንዑስ-ምዕራፍ ሁለት
## የሥራ አመራር ቦርድ እና የአማካሪ ቦርድ

### አንቀጽ 33
### የሥራ አመራር ቦርድ አመሰራረት

1. የመጅሊስ የሥራ አመራር ቦርድን ሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤ ከአባላቱ መካከል መርጦ የሚሾመው ዘጠኝ አባላት ያሉት አካል ሲሆን ለኡለማ ምክር ቤት የተሰጠውን ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዉጭ የመጅሊስ አስተዳደርንና ሙስሊሞችን በሚመለከቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ከጠቅላላ ጉባዔ ቀጥሎ ሁለተኛው የስልጣን አካል ነው፡፡
2. ለሥራ አመራር ቦርድ አባልነት በአንቀጽ 34 የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ አባላት እስካሉ ድረስከዘጠኙ የቦርድ አባላት ዉስጥ ቢያንስ አምስቱ በ1999 የህዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት ከፍተኛ ሕዝበ ሙስሊም ቁጥር ከሚገኝባቸው ክልሎች ማለትም ከኦሮሚያ ክልል፣ ከሶማሌ ክልል፣ ከአማራ ክልል፣ከደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እና ከአፋር ክልል ከተወከሉ የጠቅላላ ጉባኤ አባላትመካከል ሊመረጡ ይገባል፡፡

3. ከቦርድ አባላቱ ቢያንስ ሰባቱ(7) ከጠቅላላ ጉባዔው የእንደራሴ እና የኡለማ አባላት መካከል መመረጥ ያለባቸው ሲሆን ከባለድርሻ ሙስሊም አካላት ከሆኑት የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ የሚመረጡት ከ2 መብለጥ የለበትም። ይሁንና በዚህ ሕገ-መጅሊስ ስለመመዘኛ የተደነገጉት ቢኖርም ቢያንስ አንድ የኡለማ ምክር ቤት አባል በቦርዱ ውስጥ መካተት አለበት።
4. ቦርዱን ስብሰባውን በየወሩ ቢያንስ አንዴ የሚያደርግ ሲሆን ወርሃዊ ደሞዝ ወይም አበል ይኖራቸዋል።
5. የመጅሊስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅያለ ድምፅየቦርዱፀሐፊበመሆንያገለግላል፤
6. ዋና ሙፍቲው፣ ሁሉምምክትልጠቅላይ ሥራ አስኪያጆች፣ ዳይሬክተሮችየጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ እና ማናቸውም ለጉዳዩ ያስፈልጋል የተባለ ሰው በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ በአስረጅነት ሲጋበዝ ወይም ሲጠየቁ መገኘት አለባቸው።

### አንቀጽ 34
### ለሥራአመራር ቦርድ አባልነት መስፈርት፣

የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በችሎታቸዉና በሙያዊ ብቃታቸዉ የታወቁና ለመጅሊሱ አመራር የተሻለ አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ ሆነው የሚከተለው ማሟላት አለባቸው፡-

1. መሰረታዊ የዲን ዕውቀት ያለው
2. በእስልምና ሃይማኖት ግዴታ የተደረጉ ትእዛዛትን ተግባራዊ የሚያደርግ እና በግልጽከሚታወቁ ኃጢአቶችየጸዳ፣
3. የመስጊድ ም/ቤት አባል የሆነና መብትና ግዴታዎቹን የተወጣ፣
4. እደሜው 40 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነው፤
5. በሃይማኖታዊ አልያም በመደበኛ ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው አልያም የመጀመሪያ ዲግሪና የስምንት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው፤
6. የፌዴራል መንግስቱን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ሆኖ ቢያንስ ዓረብኛ ወያም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር፣መጻፍና ማንበብ የሚችል፤
7. ሕዝበ ሙስሊሙን ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፤
8. ቢያንስ በወር አንዴ ለሚደረገው ስብሰባ መገኘት የሚችል፤
9. ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት ቢያንስ የአሥራ አምስቱን የእጩነት ድጋፍ ያገኘ፤
10. በየትኛዉም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የመንግስት የፖለቲካ ሹመኛ ያልሆነ ወይም ሹመኛ ቢሆንም ስልጣኑን ለመልቀቅ ፈቃደኛ የሆነ፤
11. ለኢትዮጵያሙስሊምማህበረሰብ የሚቆረቆርና ራዕይያለው፣

### አንቀጽ 35
### ከሥራ አመራር ቦርድ አባልነት የሚያሰናብቱ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም የቦርዱ አባል ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ከቦርዱ አባልነት በጠቅላላ ጉባዔው በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰናበት ይችላል፡-

1.1. ሥራውን በአግባቡ ከመወጣት የሚያቅብ ማናቸውም የጤናችግር ካለበት፤

1.2. ከሥነ-ምግባር ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ባለው ወንጀልጥፋተኛ መሆኑ አግባብ ባለው አካል ከተረጋገጠ

1.3. የመጅሊስን መልካም ስምና ዝና በሚያጎድፍ ተግባር መሰማራቱ ታውቆ ጠቅላላ ጉባዔው ጥፋተኛነቱን ከታመነበት፤

1.4. መሰረታዊ ኢስላማዊ የሥነ ምግባር ህግጋትንከጣሰ፤

1.5. ኃላፊነቱን በብቃት መወጣት ካልቻለ፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የቦርዱ አባላት በሚከተሉት ምክንያቶች በክብር ሊሰናበቱ ይችላሉ፤

2.1. ለቦርዱ ወይም ለጠቅላላ ጉባኤው መልቀቂያ አቅርበው በገዛ ፈቃዳቸው ሲለቁ፤

2.2. ዕድሜአቸው ከ70 ዓመት በላይ ሆኖ በጡረታ ከተሰናበቱ፤

2.3. ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ፣

2.4. ጠቅላላ ጉባዔው የቦርድ አባሉ በሥራ ጫናና በመሳሳሉት ምክንያት ሚናውን አይወጣም ብሎ ሲያስብና በሌላ ማናቸውም ምክንያት የክብር ስንብት ውሳኔ ሲያሳልፍ፤

## አንቀጽ 36
## የሥራ አመራር ቦርድ ስልጣንና ተግባር

1. የሥራ አመራር ቦርዱ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ሆኖ የመጅሊሱን ስትራቴጂክ ሥራዎች የሚመራና የሚያስተባብር አካል ሲሆን በተለይ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1.1. በጠቅላላ ጉባዔው የሚፀድቁ ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎችና ውሳኔዎች አርቅቆ ያቀርባል።

1.2. በጠቅላላ ጉባዔው የፀደቁ ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎችና ውሳኔዎች በተዋረድ ባሉ የመጅሊስ አካላት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

1.3. ከኡለማ ምክር ቤት ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፣የጋራ ስልጣኖችን በህብረት ይተገብራል፣ ስልጣኑ ያልሆነን ወደ ተገቢው ተቋም ይመራል።

1.4. የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ፣ የፋይናንስና የበጀት አጠቃቀም፣ የሰራተኛ አስተዳደር፣ የንብረት አስተዳደር የአፈጻጸም መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችን ያወጣል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

1.5. የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያደምጣል፣ ይገመግማል፣ ልዩ ልዩ ውሳኔ ያሳልፋል፤

1.6. የጠቅላላ ጉባዔውን መደበኛ፣ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች ከጠቅላላ ጉባኤው አመራር ጋር ይጠራል፤

1.7. ለቦርዱ ተጠሪ ለሆነላቸው አካላት የዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያሳልፋል፤

1.8. ግልጽነት ያለው የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞች መምረጫ መስፈርቶችን ከዑለማ ምክር ቤት ጋር ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

1.9. የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁን ጽ/ቤት፣የዘርፎቹንና የዳይሬክቶሬቶችን አስተዳደራዊ መዋቅሮች በሙያተኛ በማስጠናት ሥራ ላይ ያውላል፣ያሻሽላል፣ተገቢው በጀት እንዲመደብላቸው ያስደርጋል።

1.10. በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የመጅሊስን ዓመታዊ ተሰብሳቢ ገቢ፣ የሥራ እቅድና በጀት ይመረምራል፣ ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

1.11. ከሌሎች እምነቶች ተከታዮች ተመሳሳይ ተቋማት ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር የአብሮነትን ባህል በሚያበለጽጉ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ይሰራል፤

1.12. አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ኃይማኖታዊ ጉባዔዎችና ስብሰባዎች ላይ የሀገሪቱን ሙስሊም ማህበረሰብ በመወከል ይሳተፋል፣ የልዑካን ቡድን ያደራጃል፤

1.13. በሀገራዊ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ የወጡና የተሻሻሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን የማስፈጸሙ ሥልጣን የክልልና የከተሞች መጅሊሶች መሆኑን ይከታተላል፤

1.14. የሙስሊሞችን ሃይማኖታዊና ሰብአዊ የመብት ጥያቄዎች አግባብ ላላቸው መንግሥታዊ አካላት በማቅረብ መፍትሄ እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል፤

1.15. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁን እና ምክትል ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁን አወዳድሮና መልምሎ በመቅጠር ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት ያደርጋል።

1.16. የሥራ ክፍል አመራሮችን፣ዳይሬክተሮችን፣ ኃላፊዎችንና ምክትሎቻቸውን በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ መልማይነት እና አቅራቢነት ይቀጥራል።

1.17. ለዘካአስተዳደር ተቋም፣ለልማትኤጀንሲእናበመጅሊስ ስር ላሉ ሌሎች ኢስላማዊተቋማት የቦርድ አመራሮችን ይመድባል፣ የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤

1.18. የአማካሪዎች ቦርድን ያቋቁማል፣ አባላትን ይሰይማል፣ የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤

1.19. ሙስሊሞች በየዓመቱ የሚከፍሉትን የመዋጮ መጠን ከክልሎች ጋር በመመካከር ይወስናል፣ ለአሰባሰቡ ስልት ይነድፋል፤

1.20. የመጅሊስን ሥራዎች በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያስችሉ አስተዳደራዊናሌሎች የበታች ውስጣዊ መዋቅሮችን ያደራጃል፤

1.21. በቦርዱ በሚወጣ የፋይናንስ እና የንብረት አስተዳደር ዝርዝር መመሪያ መሰረት የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁና የምክትሎቹን ከመጅሊስ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘና ከገንዘብና ንብረት አስተዳደር እንዲሁም ከባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኙ ጉዳዮችን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ውሳኔ ይሰጣል።

1.22. ከጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

2. የሥራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሃፊ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፡-

የሰብሳቢው ስልጣንና ተግባር

2.1 ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ቦርዱና ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል

2.2 የፌደራል ጠቅላይ ምክር ቤቱ አስፈጻሚ ሀይላት ሥራዎችን በአግባቡ መስራታቸውን በበላይነት ይከታተላል፤ ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት ያደርጋል፤

2.3 . የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፤

2.4 ምክትል ሊቀመንበሩንና ጸሐፊውን አሱን ወክለው እንዲሰሩ ማድረግ ይችላል፤

2.5 በስራ አመራር ቦርዱና በውስጥ ደንቡ የሚወሰነውን ሊሎች ሥራዎች ያከናውናል፤

የምክትል ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

3.1. የቦርዱን ሰብሳቢ ያግዛል፤

3.2. ሰብሳቢው በማይኖርበት ሰዓት ተክቶ ይሰራል፤

3.3. በሰብሳቢውና በስራ አመራር ቦርዱ የሚመራለትን ሥራ ያከናውናል፤

3.4. ሰብሳቢውና ጸሐፊው በማይኖሩበት ጊዜ ከሥራ አመራር ቦርድ መካከል አንዱን ይወክላል፤

የጸሐፊ ስልጣንና ተግባር

4.1. የሥራ አመራር ቦርዱ ዋና ጸሐፊ በመሆን ይሰራል፤

4.2. ስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፤

4.3. ቃለ ጉባኤ እንዲያዙ ያደርጋል፤

4.4. የጠቅላይ ም/ ቤቱን ስራዎች አስመልክቶ ለጠቅላላው ጉባኤ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ያደራጃል፣ በአስፈጻሚ አካላት ሪፖርት መዘጋጀቱን ይከታተላል፤ በስራ አመራር ቦርዱም ሲጸድቅ ለጉባዔው ያቀርባል፤

4.5. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ከጠቅላላ ጉባኤው አመራሮች ጋር በቅንጅት ያስተባብራል።

## አንቀጽ 37
## የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባዎችና ምልዓተ ጉባኤ

1. የሥራ አመራር ቦርዱ በየወሩ ቢያንስ አንዴ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል።
2. በቦርዱ ስብሰባ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የሰብሳቢው ድምጽም በእኩል ድምጽ ወቅት የመለያ ይሆናል።
4. ሁሉም የጉባኤው ውሳኔዎች የሚፈጸሙት በግልጽ ሆኖ የሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ አይፈቀድም።
5. የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት አጀንዳው በውይይት ከተብላላ በኂላ በአብላጫ ድምጽ ነው።
6. ሁሉም ዓይነት የቦርዱ ስብሰባዎችናውሳኔዎች፣ ምርጫዎችናየምርጫሂደቶችኢስላማዊ አደብን እና መርህን ባዋሃደ ስርዓት መመራትአለበት።

## አንቀጽ 38
## የአማካሪ ቦርድ

1. የአማካሪ ቦርዱ በቀጥታ በጠቅላላ ጉባኤው ወይም በውክልና በሥራ አመራር ቦርዱ ከተለያዩ የሙያ መስክ በተውጣጡ ከ7 እስከ 11 የሆኑ ልዩ ልዩ ምሁራን አባላትን በማቀፍ የሚዋቀር የባለሙያዎች ስብስብ ሲሆን የጠቅላላ ጉባኤውን፣ የሥራአመራር ቦርዱንና የኡለማ ምክር ቤትን ባስፈለገ ጊዜ የሚያማክር የልዩ አዋቂዎች(ፕሮፌሽናሎች) ስብስብ ሲሆን ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ነው።
2. የስብስቡ ሙያዊ ስብጥር የሃይማኖት ሊቃውንት(ሙያተኛን) ጨምሮ የተለያዩ የማህበራዊና የተፈጥሮ ሳይንስ ሙያተኞችን ተዋጽኦ ያካተተና ለአንገብጋቢ መስኮች ቅድሚያ የሰጠ ሆኖ በስሩ የተለያዩ ንዑስ የሙያ ዘርፎችን ማዋቀር ይችላል።
3. የአማካሪ ሙያተኞች ያለ ደሞዝ የሚያገለግሉ የበጎ ፈቃደኞች ስብስብ ሆኖ በተቋሙ ጠያቂነት ለሥራው በተገኙበትና ለውይይት በታደሙበት ቀንና ጊዜ ልክ በቁርጥ ክፍያ ቀመር አበል ይከፈላቸዋል።
4. የሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ ምክንያታዊ መነሻ ሲኖረው የአማካሪ ቦርድ አባላት መካከል የሙያተኛ ለውጥ በማድረግ ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያደርጋል።

## ንዑስ-ምዕራፍ ሶስት
## የኦዲት እና ኢንስፔክሽን አገልግሎት

### አንቀጽ 39
### የኦዲት እና ኢንስፔክሽን አባላት አመሰራረት

1. የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ ጉባኤው ከአባላቱ መካከል መርጦ የሚሾማቸው አምስት አባላትን ያቀፈ የመጅሊስ የቁጥጥር አካል ነው።
2. የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ የሥራ ዘመን የጠቅላላ ጉባዔው የሥራ ዘመን ነው።
3. ኮሚቴው ቢያንስ በሶስት ወር አንዴ የሚሰበሰብ ሆኖከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፣በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ያሳልፋል።

### በአንቀጽ 40

### የኦዲትና የኢኒስፔክሽን አገልግሎት

1. የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የኦዲትና ኢኒስፔክሽን አገልግሎት ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ነው።
2. አገልግሎቱ በሀገራዊ መጅሊስ መዋቅር ውስጥ የሚከተሉት ስልጣንና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   2.1. የመጅሊስን አጠቃላይ የሥራና የአገልግሎት ሂደት በመመርመር ከሚገኘው የኦዲትና ኢኒስፔክሽን ውጤት በመነሳት ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፤
   2.2. የሂሳብና የንብረት አያያዝ በአግባቡ መሆኑን ይከታተላል፤
3. በሥራ አመራር ቦርድ የሚወሰኑ ጉዳዮችን ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

4. በሚቀርበው ሪፖርት መሰረት የሚመለከታቸው አካላት የመፍትሄና የእርምት እርምጃዎች መውሰዳቸውን ይከታተላል፡፡
5. ለሥራ አመራር ጉባኤው በየሶስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
6. ሥራውን በአግባቡ ለመሥራት የሚያስችል መዋቅር በማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ ያፀድቃል፡፡ ዝርዝር የሥራ አፈፃፀም መመሪያም ያወጣል፡፡

## አንቀጽ 41

## የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ስልጣንና ተግባር

የኦዲትና ኢንስፔክሽን አገልግሎት የሚከተሉትንተግባራትያከናውናል፡-

1. የመጅሊስ የገንዘብ አወጣጥ እና የንብረት አያያዝ ሥርዓት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡
2. የመጅሊስ ፖሊሲዎች፣ደንቦች፣መመሪያዎች፣አሰራሮች በሥራ አመራር ቦርድ፣ በዑለማ ምክር ቤት ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ የሥራ አመራር ቦርድንና የዑለማ ምክር ቤቱን ያሳስባል፣
3. የመጅሊስ የገንዘብና የንብረት እንቅስቃሴዎች መርህን ተከትሎ በውስጥና በውጪ ኦዲተሮች መመርመራቸውን ይከታተላል፣ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ የሥራ አመራር ቦርድንና የዑለማ ምክር ቤቱን ያስገነዝባል፤በሥራ ሂደቱ ላረጋገጣቸው ችግሮች መፍትሄ ያመላክታል፡፡
4. በሥራው ሂደት ያረጋገጣቸውን ጥፋቶች እና የጥፋት ፈጻሚዎችን በዲሲፕሊን ወይም በህግ እንዲጠየቁ ለሚመለከታቸው የተቋሙ አካላት ያሳውቃል፡፡
5. መጅሊስ ህግና ስርዓትን ተከትሎ በመሥራት የሙስሊሙን ማህበረሰብ መብትና ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የሞራል ልዕልና ያለው ተቋም እንዲሆን ኮሚቴ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡
6. የኦዲትና ኢንስፔክሽን የግኝት ሪፖርቱን ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡ በሪፖርቱ ውስጥ ላነሳቸው ችግሮች የመፍትሄ ሃሳቦችን ማካተት ይጠበቅበታል፡፡
7. የታቀዱ ሥራዎች አፈጻጸም በተሻለ ጥራትና ውጤት መከናወናቸውን በመከታተል አስተያየቱን ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ይለግሳል፡፡
8. ሌሎች ከጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ንዑስ-ምዕራፍ አራት
## ዋና ሙፍቲ፣ የሥራ ፈጻሚ አካላት እና ልዩ ልዩ ክፍሎች

## አንቀጽ 42
## ዋና ሙፍቲ

1. ዋና ሙፍቲ በኡለማ ምክር ቤት አቅራቢነት በሀገራዊው ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መንፈሳዊ መሪ ሲሆኑ ተጠሪነታቸው ለጠቅላላ ጉባዔው እና ለዑለማዎች ምክር ቤት

በጣምራ ሆኖ የጠቅላይ ም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ እና የኡለማ ምክር ቤት ሰብሳቢ እንዲሁም የሙፍቲዎች ጉባኤ ዋና ሙፍቲ ሆነው ይሰራሉ።

2. ሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤው ዋና ሙፍቲውን የሚመርጠው የኡለማ ምክር ቤቱ በቅድሚያ ከመረጣቸው የሙፍቲዎች ጉባኤ አባላት መካከል ነው።
3. የዋና ሙፍቲው የሚመረጠው የኡለማ ምክር ቤቱ የሚያሳውቃቸው ሁሉም የሙፍቲዎች ጉባኤ አባላት በዕጩነት ለ ሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤ ከቀረቡ በኋላ በሚስጥር በሚሰጥ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ነው።
4. የኡለማ ምክር ቤቱ የሙፍቲዎች ጉባኤ አባላትን ከመምረጡ በፊት ጉዳዩን የሚያስፈጽም ..... አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ ከሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤው የእንደራሴ አባላት መካከል መርጦ ያቋቁማል።
5. ዋና ሙፍቲው የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነትና ስልጣን ይኖራቸዋል፦

5.1. የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መንፈሳዊ መሪ ናቸው፡፡

5.2. የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ወክለው በማናቸውም ቦታ መልዕክት ያስተላልፋሉ፤

5.3. የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባ ይመራሉ፤

5.4. የዑለማዎች ምክር ቤትንና የሙፍቲዎችን ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራሉ።

5.5. በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ከሙፍቲዎች ጉባኤ አባላት ጋር ብያኔ(ፈትዋ) ይሰጣል።

5.6. ዋና ሥራ አስኪያጁ ከፋይናንስ ሀላፊው ጋር በጣምራ ፊርማ ወጪ እንዲያደርግ በሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤ ከሚያወጣው የገንዘብ ገደብ ጣሪያ በላይ ያለውን ዋና ሙፍቲው እያዩ ወጪ እንዲደረግ ያጸድቃሉ።

5.7. በጠቅላላ ጉባዔና ከዑለማዎች ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 43
## ዋና ሥራ አስኪያጅ

1. የብሄራዊው መጅሊስ ዋና ሥራ አስኪያጅ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አስተዳደራዊ መሪ ነው።
2. ዋና ሥራ አስኪያጁ የሚመለመለው እና የሚቀጠረውበሥራአመራር ቦርዱ ሆኖ ቦርዱ ቀጥሎ ለሚደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ያደርጋል።
3. ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት የሚመለመል ዕጩ ለቦታው ከመወዳደሩ በፊት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፦

3.1. ሙስሊም የሆነ፤

3.2. እድሜው ቢያንስ አርባ ዓመት የሆነው፤

3.3. ሀይማኖቱን የሚተገብር፤

3.4. በአስተዳደር፣በአመራርና ተዛማጅ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪና አሥራ አምስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለዉ ሆኖ ከዚህ ውስጥ ለስምንት ዓመት በሀላፊነት የሠራ፤

3.5. ከሥነ-ምግባር ብልሹነት ጋር በተያያዘ በማንኛውም ሁኔታ ጥፋተኛ ያልተባለ፤

3.6. በጀመዓነት ከሚሰግድበት መስጊድ የአባልነት ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፤

3.7. መጅሊስን ለመምራት ፈቃደኛ የሆነ እና ስለተቋሙ ያለውን ራዕይ በጽሑፍ ማቅረብ የሚችል፤

3.8. የፌደራል መንግስቱን የሥራ ቋንቋ እና እንግሊዘኛ የሚችል ሆኖ ዓረብኛን በተጨማሪነት የሚችል የተሻለ ይመረጣል።

4. የዋና ሥራአስኪያጁ ስልጣንና ኃላፊነት ፦

4.1. እንደ ተቋም አስተዳደራዊ መሪ በሀገራዊው መጅሊስ መዋቅር ውስጥ በስልጣን ክልሉ አስተዳደራዊ ትእዛዝ ያስተላልፋል።

4.2. የሀገራዊመጅሊስን የእለት-ተዕለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣ በበላይነት ይመራል፤

4.3. መጅሊስን በህጋዊ ሰውነት ይወክላል፤ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል፣ውል ይዋዋላል፣ ውክልና ይሰጣል፤

4.4. የሥራ አመራር ቦርድ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣

4.5. በስልጣን ክልሉ መግለጫ ይሰጣል ወይም ሌሎችን ይወክላል፣

4.6. በገንዘብና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ወጪዎችን ያዛል፣ የመጅሊስን ሂሳብ በፊርማቸው ለማንቀሳቀስ ስልጣን ከተሰጣቸው ኃላፊዎች ጋር በመሆን የባንክ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣

4.7. በጠቅላላ ጉባዔ፣ በሥራ አስፈጻሚ ቦርድ፣ በዑለማዎች ምክር ቤትና በሥራ አመራር ኮሚቴው ውሳኔ መሰረት በተዘጋጁ ደብዳቤዎችና ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች አስተዳደር ነክ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል፣

4.8. ከጠቅላላ ጉባዔና ከሥራ አስፈጻሚ ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

5. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉትን ጥፋቶች ከፈጸመ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት በቂ ናቸው፦

5.1. የህገ-መጅሊሱን መሰረታዊ ድንጋጌዎች ጥሶ ሲገኝ፤

5.2. የቅጥር ውሉን መሰረታዊ ድንጋጌ ጥሶ ሲገኝ፤

5.3. ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ በሆነ ሥራ ተሰማርቶ ሲገኝ፤

5.4. በግልና በማህበራዊ ኑሮው ለመጅሊሱ ክብር የማይመጥን አድራጎት ፈጽሞ ሲገኝ፤

5.5. ለሥራአመራር ቦርዱ ተገቢ ትዕዛዝ እምቢተኛ ሲሆን፤

5.6. የተቋሙን መብትና ጥቅም በሚጎዳ ተግባር ላይ ሲሰማራ፤

5.7. የእስልምና ሃይማኖንቱን ሲተው፤

5.8. ተመሳሳይነት ባህሪ ያላቸው ጥፋቶች ሲፈጽም፤

## አንቀጽ 44
## የትምህርት፣ የኢስላማዊ ተቋማት እና ቅርሶች አስተዳደር ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ

1. የትምህርቶች፣የኢስላማዊ ተቋማት እና ቅርሶች አስተዳደርምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በሥራ አመራር ቦርዱ መልማይነት ተወዳደሮ የሚሾም ሲሆን ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ነው።
2. ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ ከኢስላማዊ ቅርስ፣ከዳዕዋና ጋር የተቆራኙ መንፈሳዊ ጉዳዮችንና በስሩ የተዋቀሩ ዳይሬክቶሬቶችን የሚያስተባብር ሆኖበተለይም የሚከተሉትን የዘርፉን ዋና ዋና ተግባሮች ያከናውናል፡-

2.1. በመጅሊስ መዋቅር ስር የተደራጁና የሚያቋቁማቸውን መደበኛና ኢስላማዊ የትምህርት ተቋማትን ያስተዳድራል፤ የካሪክለሙን አፈጻጸም ይከታተላል፤

2.2. ወቅቱን ጠብቆ የዘርፉን ዓመታዊ የሥራ፣ የሰው ኃይልና የበጀት እቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2.3. በሥራ ላይ ያሉትን መስጅዶች፣ የቁርኣን ት/ቤቶች፣ መድረሳዎችናኸልዋዎች ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን የማጠናከሪያ ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፤ እነዚህ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ተገቢውን ጥናት በማካሄድ እንዲቋቋሙ ጥረት ያደርጋል፤

2.4. የቁርኣን፣ የሐዲስና ሌሎች ኢስላማዊ መጽሐፍት ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ሲገኙም በዑለማዎች ከታዩ በኋላ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

2.5. ሀገራዊ ኢስላማዊ ሙዚየሞችን ያደራጃል፣ያስተዳደራል፤ለህዝብ ግልጋሎት ክፍት ያደርጋል፤

2.6. ሀገር በቀል የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ኢስላማዊና ሙስሊም ተኮር ቅርሶችን ይንከባከባል፤ይጠብቃል፤

2.7. ሃይማኖት ቀመስ እና ሀገር ተኮር የታሪክ መረጃ የሆኑ ቅርሶች እንዲሰበሰቡ ጥረት ያደርጋል፤ተገቢውን ጥናት ያደርጋል፤ የድሮ መዛግብት ይጠብቃል፣ ያሰራጫል፣ ያሳትማል፤

2.8. ኢስላማዊና ሙስሊማዊ የሚደሰሱና የማይዳሰሱ ሀገር በቀል ቅርሶች በተባበሩት መንግስታት የባህል፣የሳይንስና የሥነ ጥበብ ማዕከል(ዩኔስኮ)በዓለም አቀፍ ቅርስነት እንዲመዘገብ ያስደርጋል፤

2.9. ከቅርስ አስተዳደር የሚገኝን ገቢውን ለተሻለ የቅርስ ጥበቃ አላማ ያውላል፤ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ለይቶ ያውቃል፣ ይመዘግባል፣ ጥናት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣ ለህዝብ ያሳውቃል፣ ቅርሶች በሚሰበሰቡበት ወቅት ጉዳት እንዳይደርስባቸውና ነባር ገጽታቸው እንዳይለወጥ ተገቢው ጥንቃቄ መደረጉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2.10. በጥናት ላይ ተመስርቶ ኢስላማዊ ት/ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ በኡለማ ምክር ቤት የተዘጋጀውን የትምህርት ካሪኩለም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

2.11. ወጣቶች በተለይም የአካል ጉዳተኞች ነጻ የዘመናዊ ትምህርት እና የዲን ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ስፖንሰር ያፈላልጋል፣ ሲገኝም አስፈላጊውን የመምረጫ መስፈርት በማዘጋጀት ለክልሎች/ለከተማ አስተዳደሮች የኮታ ድልድል ያደርጋል፣ መስፈርቱን የሚያሟሉና የክልላቸውን

መጅሊስ የድጋፍ ደብዳቤ የያዙ እጩዎች ብቻ የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ አድሎአዊና ህገ ወጥ አሰራርን ያስወግዳል፤

2.12. ዘርፉን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የማሻሻያ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ለሚመለከታቸው የአቅም ግንባታ ስልጠና ያከናውናል፤

2.13. የሙስሊሙ ማህበረሰብ የኑሮና የባህል ነፀብራቅ የሆኑ የወግ እቃዎችና የዕደ-ጥበባት ፈጠራ ውጤቶችንያበረታታል፣ ይመዘግባል፤ የጥናት ግብዓት ያደርጋል፤

2.14. ኢስላማዊ የጥናትና የባህል ማዕከል እንዲቋቋምና እንዲጠናከር ጥረት ደርጋል፣ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ቅርሶች ሕዝብ እንዲጎበኛቸውና እንዲያውቃቸው ሙዚየሞችን በየአካባቢው በማቋቋም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ማዕከሉ የራሱን የገቢ ምንጭ ለማጎልበት ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

2.15. የሙስሊሙን ታሪክ በተመለከተ በጽሁፍ የሰፈሩ ሰነዶች እንዲሰበሰቡና እንዲደራጁ ያደርጋል፣ የሙስሊሙ ታሪክ በባለሙያዎች እንዲጠኑ ጥረት ያደርጋል፣ የጥናት ውጤቶቹንም ለተጠቃሚዎች ይፋ ያደርጋል፤

2.16. የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ታሪክ ነክና ቅርስ ተኮር ኮንፈረንስ፣ ምርክሾፕና የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀትኢስላማዊ ቅርስና ታሪክ ለሀገሪቱ የቱሪዝም ልማት ግብዓት የሚሆኑበትን መንገድ ማጥናትና ሥራ ላይ እንዲውል ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ያከናውናል፤

2.17. ዘርፉን በተመለከተ ለሚቀርቡ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፤

2.18. የሥራውን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርት ወቅቱን ጠብቆ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ያቀርባል፤

2.19. ከለጋሽ ድርጅቶች እና ከበጎ አድራጊዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ አዳዲስ መስጅዶች የሚገነቡበትንና ነባሮች የሚጠናከሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ያስተባብራል፤ለሰብአዊ ልማትም ይሰራል፤

2.20. ከዋና ሥራ አስኪያጁ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 45
## የአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ

1. የአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በሥራ አመራር ቦርዱ መልማይነት ተወዳደሮ የሚሾም ሆኖተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ፣
2. ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ ከአስተዳደር፣ ከፋይናንስ፣ ከሀብት ስርጭት፣ ከዕርዳታና ገቢ ከሚያስገኙ ወቅፎች ጋር የተቆራኙ ጉዳዮችንና በስሩ የተደራጁ ዳሬክቶሬቶችንና የሥራ ክፍሎችን ያስተባብራል። ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ በተለይም የሚከተሉትን የዘርፉን ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል፦

2.1. የዘርፉን ዓመታዊ የሥራ፣ የሰው ኃይልና የበጀት እቅድ ወቅቱን ጠብቆ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2.2. ዘርፉን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የማሻሻያ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ የአቅም ግንባታ ስልጠና ያከናውናል፤

2.3. የክልሎች መጅሊሶች በዓመታዊ የሥራ እቅዳቸው ውስጥ ሙስሊሙን ማህበረሰብ በማደራጀትና ከአባላት መዋጮ በመሰብሰብ እንዲጠናከሩ ለማድረግ ስልት ይቀይሳል፣ ለአፈጻጸሙ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፤

2.4. ለመስጅዶችና ለሙስሊሙ ማህበረሰብ በወቅፍ የተሰጡ ወይም የሚሰጡ ገቢ የሚያስገኙ ንብረቶች በአግባቡ ተጠብቀው ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2.5. የፕሮጀክት ጥናቶች በባለሙያዎች እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ሲፈቀድ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የፕሮጀክቶች ክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ ስርዓት እንዲጠናከር ጥረት ያደርጋል፤

2.6. የልማት ጉዳይን በተመለከተ ከበላይ አመራር ጋር በመመካከር ከዓለም አቀፍ ተቋሞች፣ ከአቻ ማህበራት፣ ከክልልና ከፌዴራል የመንግስት አካላት እንዲሁም ከግለሰቦች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣ ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት ጥረት ደርጋል፤

2.7. የመጅሊስን ልዩ ልዩ የልማትና የእርዳታ ተቋማት ያቋቁማል፣ ይመራል፣የእርዳታ ቁሳቁሶችን ያሰባስባል እንዲከማቹና እንዲደራጁ ያደርጋል፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የእለት ደራሽ እርዳታዎች በወቅቱ እንዲደርሱ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤

2.8. የሙስሊሙ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር እርዳታና ድጋፍ እንዲገኝ ስርዓት ይዘረጋል፣ የመሰብሰቡን ተግባር ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ከኢስላማዊ እርዳታ ሰጪና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር የትብብር ግንኙነት ያደርጋል፣ የጋራ መድረክ ይፈጥራል፣ በትብብር ይሰራል፤

2.9. የክልል መጅሊሶች በእርዳታና ልማት ዘርፍ ለሚያከናውኑት ሥራዎች አቅማቸውን መገንባት፣ አቅጣጫ ማሳየት፣ የጋራ የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀት፣ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ማዋል፤

2.10. ዘርፉን በተመለከተ ለሚቀርቡ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፤

2.11. የሥራውን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርት ወቅቱን ጠብቆ ለዋናው ሥራ አስኪያጁ

2.12. በስሩ የተደራጁ የሥራ ክፍሎችን ያስተባብራል፤ይቆጣጠራል፤

2.13. ከዋናሥራ አስኪያጁ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

### አንቀጽ 46
### የማህበራዊ አገልግሎት፣የበጎ አድራጎትናልማት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ

1. የማህበራዊ አገልግሎት፣ የበጎ አድራጎትና ልማትምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ በሥራ አመራር ቦርዱ መልማይነት ተወዳደሮ የሚሾም ሆኖተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ነው።
2. ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ ከበጎ አድራጎት፣ከማህበረሰባዊ ልማትና ከማህበራዊ ደህንነት ጋር የተቆራኙ ጉዳዮችንና በስሩ የተደራጁ ዳሬክቶሬቶችንና የሥራ ክፍሎችን የሚያስተዳድርና የሚቆጣጠር ሆኖ በተለይም የሚከተሉትን የዘርፉን ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል፡-

2.1. የዘርፉን ዓመታዊ የሥራ፣ የሰው ኃይልና የበጀት እቅድ ወቅቱን ጠብቆ አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2.2. ዋና ሥራ አስኪያጁ የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣

## አንቀጽ 47
## የዋና ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት

1. የዋና ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ኃላፊ በዋና ሥራ አስኪያጁተመልምሎ የሚሾምሆኖ ተጠሪነቱም ለዋና ሥራ አስኪያጁ ነው።
2. የዋና ሥራአስኪያጅ ጽህፈት ቤት ኃላፊ በተለይም የሚከተሉትን የዘርፉን ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል፡-

2.1. ወደ ዋና ሥራ አስኪያጁ ጽ/ቤት የሚመጡ እንግዶችን ያስተናግዳል፤

2.2. በመጅሊስ ኃላፊዎች የሚጻፉ ደብዳቤዎችን ለሚመለከታቸው ያደርሳል፣ ውጤቱን ይከታተላል፤

2.3. ከልዩ ልዩ መስሪያ ቤቶች ወይም የመጅሊስ ጽ/ቤቶች ለሚመጡ እንግዶች ከኃላፊዎች ጋር እንዲገናኙ ፕሮግራም ይይዛሉ፣ ያስፈጽማል፤

2.4. የሀገራዊው መጅሊስ አካላትን እቅዶችና በጀት በአግባቡ መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

2.5. መያዝ የሚገባቸው አጀንዳዎችን በማዘጋጀት ለዋና ሥራ አስኪያጁ ያቀርባሉ፤

2.6. ቃለ ጉባዔዎችን ያደራጃል፣ ውሳኔዎችን ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፣ የውሳኔዎችን አፈጻጸም ይከታተላል፤

2.7. በዋና ሥራ አስኪያጁ የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 48
## የሕግ አገልግሎት

1. የህግ አገልግሎት ክፍል ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁሲሆን የጠቅላይ ምክር ቤቱ ዋና የሕግ አማካሪ ክፍል ነው።
2. የህግ አገልግሎቱ የሚከተሉትን ዋና ተግባራት ያከናውናል፡-

2.1. ሀገራዊመጅሊሱን በህግ ጉዳይ ያማክራል፣ውሎችን፣የክርክር ጽሁፎችናና አቤቱታዎችን ጨምሮ ማናቸውንም ሕግ-ነክ ሰነዶችን ያረቃል፤ያዘጋጃል፤ሲከሱም ሆነ ሲከሰሱ በዳኝነት እና በከፊል የዳኝነት አካላት እንዲሁም በአስተዳደር ተቋማት ተቋሞቹንና ንዑስ ተቋሞቹን ወክሎ ይሟገታል፣ ነገረ ፈጅ ይመድባል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በዋና ሥራ አስኪያጁ ሲታመንበት ጠበቃ ይመድባል።

2.2. በመላ ሀገሪቱ በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግስታት በወጡ እና በሚወጡ ማናቸውም ሕጎች እና ፖሊሲዎች እንዲሁም መንግስታዊ ውሳኔዎች፣ አሰራሮችና የሌሎች አካላት አድራጎቶች የሕዝበ ሙስሊሙን ጥቅሞችን ስለማስከበራቸው ይከታተላል፤ ጥናት ያደርጋል፤ ሃሳብና አስተያየቱን ይለግሳል፣ የምዕመኑን ጥቅም የሚጎዳና የህግ ማዕቀፉን የሚጥስ ማናቸውም ድንጋጌ፤ፖሊሲ፣ ውሳኔና አሰራር ሲገኝም በማናቸውም ጊዜ ከበላይ አመራሩ ጋር በመቀናጀትና በመመካከር የሚስተካከሉበትን መንገድ ይጥራል፣ ይወተውታል፤ ያስተባብራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በዋና ሥራ አስኪያጁ ሲታመንበት ወደ ህግ እና ሕገ-መንግስት ተርጓሚ አካላት በመውሰድ ያሳርማል፤

2.3. በህግ ጉዳይ በየትኛውም እርከን ለሚገኙ የመጅሊስ አስተዳደር እና ለኡለማ ምክር ቤት አመራሮችና አባላት ሥልጠና ይሰጣል፤

2.4. የሀገራዊ መጅሊስ የህግ ጉዳዮችን ይከታተላል፣የውሳኔ ሃሳብ ለጠየቀው የሥራ ክፍል ወይም ለበላይ አመራር ይሰጣል፤

2.5. በሀገር-አቀፍ ህግ-ነክ ጉዳዮች እና በህግ ማዕቀፉ ክፍተቶች ላይ ጥናት ያደርጋል፣አስፈሊጊ የሆኑ የአድቮኬሲ ተግባራትን ለዋና ሥራ አስኪያጁ እያስፈቀደ ያከናውናል፤ የመፍትሔ ሃሳብ ያመነጫል፣ ለሚመለከተው አካል በተቋሙ አመራር በኩል ያደርሳል፤

2.6. የተቋሙን ሕገ-መጅሊስ እና ሌሎች ደንብና መመሪያዎች ትክክለኛ ግልባጭ ስለመሆናቸው እያረጋገጠ በማሳተም ለምዕመኑና ለሚመለከታቸው ተቋማት ተደራሽ ያደርጋል፣ በህግ --ነክ ሰነዶቹ ዙሪያም የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብርም ያከናውናል፤

2.7. ለመጅሊስ አሰራር የሚረዱ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና የውስጥ አሰራር ስርዓቶችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመቀናጀትና በመተባበር ቴክኒካዊ የሰነድ ማርቀቅ ሥራውን ያግዛል፤

2.8. ለዕጩ ዳኞች/ቃዲዎች ከሹመት በፊትና በኋላ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፤

2.9. በተመሳሳይ መልኩ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በተሰጣቸው የስልጣን ክልል የሚመሩበት የሸሪዓ ህግጋት መጽሃፍ ስነዳ(ኮዲፊኬሽን) ሥራን ከኡለማ ምክር ቤት ጋር በመቀናጀት በአመራሮቹ የሚሰጠውን አቅጣጫ በመተግበር ቴክኒካዊ ሥራውን በማስተባበር ያረቃል፣ በኡለማ ምክር ቤት ሲጸድቅም በሸሪዓ ፍርድ ቤቶቹ ሥራ ላይ ስለመዋላቸው ይከታተላል፤ ሃሳብና አስተያየቶችንም በኡለማ ምክር ቤት በኩል ለፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ እንዲደርሰውና ስህተቶች እንዲታረሙ ያግዛል፤ አፈጻጸሙን እየተከታተለም ለኡለማ ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤

2.10. የሀገራዊ መጅሊስ ተቀጣሪ ሰራተኞችና ሹመኞችን የሥነምግባር ጉድለት በሚመለከት ሪፖርት ሲቀርብለት ለጠየቀው አካል ህግ ነክ የውሳኔ ሃሳብ እና ምክር ያቀርባል፤

2.11. መላው መጅሊስና ንዑስ ተቋማቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚኖራቸው ጉድኝት መብትና ጥቅም አለመጎዳቱን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

2.12. የመስጅዶች ቅጥር ጊቢና ዙሪያ ገባ ከባእድና ኢሞራላዊ ሥራዎችና ከአፈንጋጭ ንግድና ሸቀጦች ጸድቶ ለአምልኮ ሰላምና ደህንነት ተስማሚ ከባቢ መኖራቸውን በመከታተል ለሚመለከት አስተዳደር ያሳውቃል፣ እገዛ ሲጠየቅ የሕግ ድጋፍ ይሰጣል።

2.13. በጎ ፈቃደኛ የህግ ሙያተኞች ከበጎ ፈቃድ ሥራ ክፍል ጋር በመተባበር ለማህበረሰቡ የሚያግዙበት ሁኔታ ያመቻቻል።

2.14. ሌሎችበዋና ሥራ አስኪያጅ ተለይተው የሚሰጡትን ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 49
## የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት

1. የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሲሆን በሴት ዳይሬክተር ይመራል።
2. በሁሉም እርከን የሚገኘው የመጅሊስ መዋቅር በሴቶች የሚመራ የሴቶች ጉዳይ ልዩ ጽ/ቤት ማዋቀር ያለበት ሲሆን በበጀትም ሆነ በሌላ ማናቸውም ምክንያት ይህንን የሥራ ክፍል ማጠፍ አይቻልም።
3. የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ሹመት በዋና ሥራ አስኪያጁ መልማይነትና አቅራቢነት በሥራአመራር ቦርዱ የሚጸድቅ ሆኖ ኃላፊነታቸውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገውን የሥራ ክፍሉን ሥራ በበላይነት መምራት ሲሆን ቦርዱ ለዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ሹመት የቅጥር መመዘኛ ያወጣል።
4. ዳይሬክቶሬቱ የሚከተሉትን ዋና ተግባራትን ያከናውናል፦

4.1. ሴቶች በኢስላም ያላቸውን መብትና ሥፍራ ለሕብረተሰቡና በተለይም ለሴቶች ግንዛቤ ማስጨበጥ፤

4.2. ከዑለማ ምክር ቤቶች ጋር በጋራ በመሥራት ሙስሊም ሴት ዱዓቶችና ዓሊሞች ማፍራት በሚቻልበት መንገድ ላይ በትኩረት መሥራት፤

4.3. የሙስሊም ሴቶችን ጥቅሞችና መብቶችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር፤የሀገሪቱ የሕግ ማዕቀፍና የመጅሊስ ሥርዓትባስቀመጠውአግባብ ከሚመለከተው የመጅሊስና የመንግሥት አካላት ጋር መሥራት፤

4.4. ሙስሊም ሴቶች በሀገሪቱ የሃይማኖታዊ፣ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው እድሎች እንዲመቻቹላቸው አስፈላጊ ሥራዎችን መሥራት፤

4.5. ሙስሊም ሴቶች በሃይማኖታቸው ምክንያት በትምህርት ተቋማት አልያም በሥራ ላይ አልያም በማንኛውም ሥፍራ የሚገጥሟቸውን የመብት ጥሰቶችን መመዝገብ፤ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋጋር አልያም ጉዳዩን ወደ ሕግ በመውሰድ መፍትሄ እንዲያገኙ መሥራት፤

4.6. ሙስሊም ሴቶች ላይ የሚደርሱባቸውን ጾታዊና ሃይማኖታዊ ትንኮሳዎችንም ሆነ ጥቃቶችን አስመልክቶ ከተጠቂ ሴቶች ዝርዝር መረጃዎችን መሰብሰብ፤ማደራጀት፤በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንዲታወቁ ማድረግ፤እንደየአስፈላጊነቱ ጉዳዩን ወደ ሕግ በመውሰድ መፍትሄ ማስገኘት፤

4.7. ሙስሊም ሴቶች የሀገሪቱ ሕጎች በሚፈቅደው መሠረት እንደፍላጎታቸውና እንደ ችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

4.8. በመንግስት አካላት የሚረቀቁና የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ሕጎች፣የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲሁም የመንግስት ውሳኔዎችና አሰራሮች የሙስሊም ሴቶችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ እንዲተገበሩ የማሳወቅና የመወትወት ሥራዎችን ማከናወን፤

4.9. በሙስሊም ሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችንና ጥቃቶችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹና ጥቃቶቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የዉይይት መድረክ ማዘጋጀት፤መፍትሄዎችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ፤

4.10. ሙስሊም ሴቶችን አስመልክቶ ጽ/ቤቱ የሚሰራቸውን እቅዶች በማዘጋጀት በድርጅቱ አመራሮች በኩል ማስጸደቅ፤ የሥራቸውንም ሪፖርት ማድረግ፤

4.11. የሴቶችን ችግሮች የሚፈቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን በመለየት ለተግባራዊነቱ ከሚመለከተው አካል ጋር መንቀሳቀስ፤

4.12. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሙስሊም ሴቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ተደራጅተው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲያቃልሉ ከባለድርሻ አካላት ድጋፍ በማፈላለግ የገንዘብ፣የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ። የሴቶችን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያግዙ ጉልበት፣ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አነስተኛ መሣሪያና ቁሳቁሶች የሚገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣መፍጠር፤

4.13. ኢስላማዊ መርህንና ሕገመጅሊስን ባልጣሰ መልኩ የሴቶችን መብት ለማስከበር ከተቋቋሙ የሴቶች አልያም ሌሎች ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መሥራት፤

4.14. ሙስሊም ሴቶች ልምድ እንዲለዋወጡና በማህበረሰቡ ዉስጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ መሥራት፤

4.15. የሙስሊም ሴቶች ድርጅቶችን ለማቋቋምና ለማጠናከር የሚከናወኑ የአቅም ግንባታና የሥልጠና ሥራዎችን ማስተባበር፣ማገዝና የምክር አገልግሎት መስጠት፤

4.16. ሙስሊም ሴቶችን በመወከል ሴቶችን በሚመለከቱ መድረኮች መገኘት፤በእስልምና ጉዳይ ዉስጥና በመላ ሀገሪቱ የሴቶችን ድምጽና ፍላጎት ማሰማት፤

4.17. ሙስሊም ሴቶች በማህበረሰቡ ዉስጥ የሚገጥሟቸውን ችግሮች እንዲቀረፉ መሥራት፤

4.18. ሴቶች በትምህርት፣በስልጠና እና በክህሎት እንዲጎለብቱ መሥራት፤በበላይነት ማቀናጀት፤

4.19. ሴቶች ልምድ እንዲለዋወጡና በማህበረሰቡ ዉስጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ መትጋት፤

4.20. ኢስላምን የተረዳና የሚኖር በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ንቁ ተሳታፊ የሆኑና አርኣያ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት፤

4.21. ሴቶች የተለያዩ የህይወት ክህሎቶችን ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ አስሶ ጾታዊ ትንኮሳዎች ሴቶች ላይ እንዳይደርስ መሥራትና ለተጠቂ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግና የድርጊቱ ፈጻሚዎች አስተማሪ ቅጣት እንዲቀበሉ መሥራት፤

4.22. የሴቶች በሀገር ግንባታ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፤

4.23. በሀገሪቱ ሴቶችን በሚመለከቱ መድረኮች ሙስሊም ሴቶችን በመወከል በተለያዩ መድረኮች መሳተፍና የሙስሊም ሴቶችን ድምጽ ማስተጋባት፤

4.24. ሴቶችን በሚመለከቱ የህይወት ጉዳዮች ከዑለማ ምክር ቤትና ከሚመለከተው አካላት ጋር በጥምረት መሥራት፤

4.25. የሀገሪቱ የህግ እና የፖሊሲ ማዕቀፍ ለሙስሊም ሴቶች ምቹና መብትና ጥቅማቸውን የማይጣረስ መሆኑን ከህግና ከሌሎች የሥራ ክፍሎች ጋር በመቀናጀት መሥራት፤ እና

4.26. በዋና ሥራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡ ኃላፊነቶችንና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችንና ተግባራትን ማከናወን ናቸው፡፡

## አንቀጽ 50
## የወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት

1. ሙስሊም ወጣቶች በመጅሊስ ሌሎች ክፍሎችና እንቅስቃሴዎች ሁሉ የመሳተፍ ሙሉ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ያላቸውን እምቅ አቅም ለራሳቸው፣ለህዝበ ሙስሊሙና ለሀገሪቷ ማበርከት ይችሉ ዘንድ ከተናጠል እንቅስቃሴ ይልቅ በየዝንባሌያቸውና በየፍላጎቶቻቸው ሲደራጁ በመሆኑና ወጣቶች ከእስካሁኑ የላቀ ሚና እንዲወጡ የተደራጀ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ የወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በሁሉም የመጅሊስ መዋቅሮች ይቋቋማል፡፡
2. ዳይሬክቶሬቱ እድሜያቸው ከ15 እስከ 39 የሆኑ ወጣት ወንድና ሴቶች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን እድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ታዳጊ ወጣት እንዲሁም ከ18 እስከ 39 ደግሞ ወጣት በሚል በሁለት ዘርፍ በመላ ሀገሪቱ ይደራጃሉ፡፡
3. ታዳጊ ወጣቶች በዳይሬክቶሬቱ ስብስቦች፣አደረጃጀቶችና ክንውኖች ያለ ድምጽ በአባልነት የመሳተፍ መብት ያላቸው ሲሆንከምርጫ ተሳትፎ በስተቀር ለወጣት የተጠቀሰው መብትና ግዴታ ያካታቸዋል፡፡
4. ዳይሬክቶሬቱ ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሲሆን በበታች የተዋረድ መዋቅሮችም ተመሳሳይ አደረጃጀት የሚኖረው ሆኖ የሚከተሉት ዋነኛ ሥልጣንና  ተግባራት ይኖሩታል፦

4.1. ሙስሊም ወጣቶች በሙያቸው፣ በሃይማኖታዊና በልማት እንደ ዝንባሌያቸውና ፍላጎቶቻቸው ዙሪያ ተደራጅተው የራሳቸውን፣ የሕዝበ ሙስሊሙን እንዲሁም የሀገራቸውን ችግሮች መፍታት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ በፈለጉት መንገድ እንዲደራጁና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ያግዛል፡፡ የተደራጁትን የወጣቶችን ስብስቦችን በማህበርነት፣ በክበብነትና በሊግነት ይመዘግባል፣ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ እንቅስቃሴያቸውን ይቆጣጠራል፤

4.2. ወጣቱ ከደካማ የሥራ ባህልና አጉል ሱሶች እንዲላቀቅና አምራች ዜጋ መሆን እንዲችል አስፈላጊውን ተግባራት መፈጸም፤

4.3. ወጣት ሙስሊሞች በሃይማኖታቸው ምክንያት የሚደርሱባቸውን አድሎዎች፣ መሰናክሎችና የህግ ጥሰቶችን በመለየት እንዲስተካከሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሠራል፤

4.4. በሙስሊም ወጣቶች መካከል የመቻቻልና ልዩነትነን በጥበብ የመያዝ እንዲሁም ሰላማዊ የዉይይት ባህል እንዲጎለብት ኢስላምና ሙስሊሙን በሚመለከቱ የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ለወጣቱ የዉይይት መድረኮችን፣ ሥልጠናዎችንና ኮንፈረንሶችን ያዘጋጃል፤

4.5. ሙስሊም ወጣቶች ያሉባቸውን ችግሮችና ጥያቄዎችን በጥናት በመለየት ምላሽ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል። ያስደርጋል። የጥናቱን ዉጤት ለወጣቱ ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤ በጥናቱ ላይ በመሞርከዝ መፍትሄ ይሻል፤

4.6. ሙስሊም ወጣቶች ከቤተሰብ ጥገኝነት በመላቀቅ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥራ ፈጠራ፣የሞያና የብቃት ማሳደጊያ ስልጠናዎችን ያመቻቻል። ያስተባብራል። እንደ አስፈላጊነቱ የራሱን ማዕከላት ይከፍታል፤

4.7. ሙስሊም ወጣቶች ዲናቸውን በወጉ እንዲማሩና ተተኪ ዓሊሞች እንዲሆኑ ከዑለማ ምክር ቤትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መሥራት። ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ የትምህርትና የቂርዓት መድረኮችን ማዘጋጀት፣ ማስተባበር፤

4.8. ሙስሊም ወጣቶች በ ዘመነኛ ትምህርት የላቁና ተወዳዳሪዎች እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ በጎ ፈቃደኛ ሙስሊሞችን በማስተባበር የማጠናከሪያ ትምህርቶችን በየደረጃው ማዘጋጀት። ዉጤታማ የሆኑ ወጣቶችን በመሸለም የሌሎች ተማሪዎችን ተነሳሽነትን ማሳደግ፤

4.9. ከትምህርት ክፍል ጋር በመቀናጀት የወጣቶች የንባብ ባህል እንዲዳብር በመስጊዶች ዙሪያ ሃይማታዊና የአካዳሚ መጽሐፍትን በአንድነት የያዙ ቤተመጽሐፍት እንዲደራጁ ማድረግና የወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

4.10. አቅም በፈቀደ መጠን ለሙስሊም ወጣቶች የሚመቹ የመዝናኛ ሥፍራዎች እንዲቋቋሙ ከመንግሥት፣ከባለሀብቶችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መሥራት፤

4.11. ወጣት ምዕመናን የአመራር ክህሎት በማዳበር ብቁ የዲንና የሀገር ተረካቢ ዜጎች እንዲሆኑ ለማስቻል የተግባርና የንድፈ ሃሳብ የአመራር ሥልጠናዎችን መስጠት፣ማመቻቸት።

4.12. ሙስሊም ወጣቶች በተግባር ተጽእኖ ፈጣሪ ሆነው ነጥረው እንዳይወጡ እና የአመራር አቅማቸውን እንዳያሳድጉ እንቅፋት የሚሆኑ መመሪያዎች፣ ደንቦችና አሰራሮች እንዲሻሻሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል።

4.13. በእርከኑ ያለን መጅሊስንና ሙስሊም ወጣቶችን በመወከል ወጣቶችን በሚመለከቱ መድረኮች ሁሉ ይሳተፋል። ከሦስተኛ ወገን ጋርም ዓላማውን መሠረትና ህገመጅሊሱን መሠረት በማድረግ ይሠራል። ይዋዋላል።

4.14. ወጣቶችን በስነምግባር የታነጹ ዜጎች ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል።

4.15. ሙስሊም ወጣቶች የአመለካከት ልዩነትና ቡድንተኝነትን፣ ጎሰኝነትን፣ አልያም ማንኛውም የልዩነት አጥሮችን ተሻግረው አብረው እንዲሰሩ፣በአንድነትና ህብረት በጋራ በመቆም ለህዝባቸው፣ለእምነታቸውና ለሀገራቸው የየበኩላቸውን መወጣት እንዲችሉ አስፈላጊውን ተግባራት ሁሉ ያከናውናል።ልዩነት ሲፈጠርምያቀራርባል። በወጣቶች መካል የሚፈጠሩ ችግሮችንም በሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይፈታል።

4.16. የሙስሊም ወጣቶችን መብትና ጥቅሞችን የሚነኩ መመሪያዎች፣ደንቦችና መንግሥታዊ ፖሊሲዎች ካሉ እንዲሻሻሉ ይሠራል። አዳዲስም እንዲስተካከሉ ከሚመለከተው አካል ጋርም ተባብሮ ይሠራል።

4.17. በወጣቶች ዘንድ የበጎ ፈቃደኝነት ተግባራት ባህል እንዲስፋፋ በመሥራትአገርንና ወገንን የሚያገለግሉ ወጣቶች ይፈጥራል።

4.18. ወጣቶችን መሚመለከት በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲና መመሪያዎችን ያጠናል። ከሙስሊሙ ተጠቃሚነት አንጻር በመገምገም ለሚመለከታቸው አካላት አስተያየቱን ይሰጣል።የማሳመንና የማግባባት ሥራዎችን ይሠራል።

4.19. ወጣቶችን ንቃተ ሕሊና የሚያሳድግበት፣ትስሥራቸውን የሚያጎለብትበት እንዲሁም ልምድና ተመክሮ የሚለዋወጡት የራሱንሚዲያ ያቋቁማል።

4.20. ወጣቶች ዓሊሞችን፣የመጅሊስ አስተዳደሮችን፣ ኢማሞችንና የመስጊድ ኮሚቴዎችን በአጠቃላይ የሙስሊም አመራርና ባለድርሻ አካላትን በማክበርና የነርሱ አጋዥ ሃይል እንዲሆኗቸው ድልድይ ሆኖ ይሰራል።

## አንቀጽ 51

## የክልል ጉዳዮች እና የዲያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

የክልል እና ዲያስፖራ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለፌደራል መጅሊስ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆነ የፌደራል መጅሊስ መዋቅር ሲሆን በዋናነትም ያለምንም የክልልና የቦታ ገደብ በሀገር ዉስጥና በዉጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን እርስ በርሳቸውና ከመጅሊስ ጋር ትብብር፣ ህብረትንንና የልምድ መለዋወጥን እና መደጋገፍን ለማሳለጥ የተቋቋመ ክፍል ነው። ይህ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በሥሩ የዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እና የክልል ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በተሰኙ ሁለት ክፍሎች የተዋቀረ ነው።

የክልል ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የቀጠና ጽ/ቤቶቹን የመቆጣጠርና የማስተባበር ሀላፊነት የሚወጣ ሲሆን የሚከተሉትን ተግባርና ሀላፊነቶችን ይኖሩታል።

1. የቀጠናው አከባቢ ሙስሊሞችና የመጅሊስ መዋቅሮች አስተዳደራዊ የክልል ድንበሮች፣ የቋንቋ፣ የብሄር፣ የአከባቢና ሌሎች ልዩነቶች ሳይገድቧቸው በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የተጠናከረ ኢስላማዊ አንድነት፣ወንድማማችነት፣ ትብብር፣ መተዋወቅ እና መተጋገዝ እንዲያጎሎብቱ እንዲሁም የጋራ እሴቶቻቸውን በአከባቢው ለማጠናከር የሚያስችሉ ተግባራትን መሥራት።
2. ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሹ አከባቢዎችን ከአካባቢው የመጅሊስ መዋቅር ጋር በመቀናጀት በአከባቢው የሚኖሩ ሙስሊሞችን ማህበረ-ኢኮኖሚ (socio economic) በማጥናትና በሚደረሰው ትንታኔ ላይ በመመስረት በቀጠናዉ አግባብነት ያለዉ ኢስላማዊ ትምህርትና ዳዕዋ እንዲስፋፋ እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስትራቴጂዎችን በመዘርጋት የአከባቢው መጅሊሶችና ሌሎች ኢስላማዊ ተቋማት ለህዝባቸው የተሻለ መስራት እንዲችሉ ማገዝ።

3. የሀጅና ዑምራ አገልግሎትን ጨምሮ የቀጠናዉ ሙስሊሞች ከፌደራል መጅሊስ ማግኘት የሚገባቸውንና የቀጣና ጽ/ቤት እንዲያስፈጽም ሥልጣን የተሰጣቸውን ሌሎች አገልግሎቶችን ለአከባቢው ሙስሊሞች በአቅራቢያቸው በሚገኘው የቀጠና ጽ/ቤቱ መስጠት፡፡
4. በቀጠናዉ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞችን የጋራ ጥቅሞችን የበለጠ ለማስጠበቅ የሚረዱ ስራዎችን የአከባቢው መጅሊሶች በጋራ አቅደው እንዲሰሩ ማገዝ፡፡
5. በቀጠናው በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች ሀብትን በጋራ ለመጠቀም (Resource Sharing) እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
6. በቀጠናው ሊፈጠሩ የሚችሉትን ግጭቶችን በመፍታት ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ጥረት ማድረግ፤
7. ከዘካ አስተዳደር ተቋም ጋር በመቀናጀት የዘካ አስተዳደር ተቋም ሀላፊነት የሆኑትን በቀጠናው ዘካ የሚገባቸውን የቀጠናውን ሙስሊሞች ሁኔታ በማጥናት በቀጠናው የዘካ አስተዳደር ተቋምን ተግባራት እንዲሳኩ ማገዝ፡፡
8. ሙስሊሞች በቁጥር አናሳ በሆኑባቸዉና ልዩ ትኩረት የሚሹ አከባቢዎች የአቅም ግንባታ፣ የድጋፍና አካባቢዎቹ ከፌደራል መጅሊስ ወይም ከሌሎች ክልል መጅሊሶች ማግኘት የሚፈልጓቸውን ድጋፎችን ማስተባበር፡፡
9. የክልል እና ዲያስፖራ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ወይም በሥሩ ያሉት የቀጠና ጽ/ቤቶች እንዲፈጽሟቸው በሀገራዊ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጧቸውን ሌሎች ኃላፊነቶችን መወጣት፡፡

**አንቀጽ 52**

**የክልልና የዲያስፖራ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት አደረጃጀት**

**አንቀጽ 52.1**

**የክልል ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት አደረጃጀት**

በክልል ጉዳዮቸ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ሥር የሚከተሉት አምስት ቀጠናዊ የማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ይደራጃሉ፡፡


1. ***የሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፡-*** ይህ ቀጠና ጽ/ቤት የትግራይ ክልል፣ከሰሜን ሸዋ ዞን በስተቀር ሁሉንም የአማራ ክልሎችን እና የአፋር ክልል ዞኖችን በሙሉ ያካልላል፡፡ ዋና ጽ/ቤቱም እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር የሚችል ሆኖ ለአሁኑ ለቀጠናው አማካይ ስፍራ ላይ በምትገኘው በወልድያ ከተማ ይሆናል፡፡

2. ***የደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና ማስተባበሪ ጽ/ቤት፡-*** ይህ ቀጠና ከደቡብ ክልል ሀላባ፣ሀዲያ፣ ሲዳማ፣ ወላይታ እና ጌድዮ ዞኖችን፤ ከኦሮሚያ ክልል የባሌ፤ የአርሲ፣የምዕራብ አርሲ፣ የቦረና እና ጉጂ ዞኖችን እንዲሁም ከሶማሌ ክልል የሊበን ዞን ያጠቃልላል፡፡ ዋና ጽ/ቤቱም እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር የሚችል ሆኖ ለአሁኑ ለቀጠናው አማካይ ስፍራ ላይ በምትገኘው በሻሸመኔ ከተማ ይሆናል፡፡

3. ***የምስራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና ማስተባበሪ ጽ/ቤት፡-*** ይህ ቀጠና ከኦሮሚያ ክልል የምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖችን፤ ከሶማሌ ክልል ከሊበን ዞን በስተቀር ሁሉንም ዞኖች፤ የሀረሪ ክልላዊ መንግስት ዞኖችን በሙሉ እና የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደርን ያጠቃልላል።ዋና ጽ/ቤቱም እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር የሚችል ሆኖ ለአሁኑ ለቀጠናው አማካይ ስፍራ ላይ በምትገኘው በድሬደዋ ከተማ ይሆናል።

4. ***የምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና ማስተባበሪ ጽ/ቤት፡-*** ይህ ቀጠና ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፤ ምስራቅ ወለጋ፤ ምዕራብ ወለጋ፤ ጅማ ዞንን፣ ጅማ ከተማ ልዩ ዞንን እና ቡኖ በደሌ፣ ኢሉ አባ ቦራ ዞን፣ ከደቡብ ክልል ቤንች ማጂ፣ ከፋና ሸካ ዞኖችን፤ ቤኒ ሻንጉል ክልልን እና የጋምቤላ ክልልን በሙሉ ያጠቃልላል።ዋና ጽ/ቤቱም እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር የሚችል ሆኖ ለአሁኑ ለቀጠናው አማካይ ስፍራ ላይ በምትገኘው በበደሌ ከተማ ይሆናል።

5. ***የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና ማስተባበሪ ጽ/ቤት፡-*** ይህ ቀጠና በኦሮሚያ ክልል የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን፤ ቡራዩና ሰበታ ከተማን፣አዳማ ከተማ ልዩ ዞንን፣ ምስራቅ ሸዋ፤ ምዕራብ ሸዋ፤ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞንን፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞንን፣ ከደቡብ ክልል የጉራጌ እና ስልጤ ዞኖች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ያጠቃልላል።ዋና ጽ/ቤቱም እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር የሚችል ሆኖ ለአሁኑ ለቀጠናው አማካይ ስፍራ ላይ በምትገኘው በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል።




አንቀጽ 52.2

የዳያስፖራ ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊነትና አደረጃጀት

የዳያስፖራ ጉዳዮች ጽ/ቤት በአንቀጽ 24 ስለ ዳያስፖራ መጅሊስ የተደነገገውን መሰረት በማድረግ ጥናት ተደርጎ ሲቀርብለት ጠቅላይ ምክር ቤቱ የዳያስፖራ ጉዳዮች ጽ/ቤትን አደረጃጀትና ኃላፊነት ይወስናል።

## ንዑስ-ምዕራፍ አምስት

## የዘካ አስተዳደር

### አንቀጽ 53
### የዘካ አስተዳደር ቦርድ

1. የዘካ አስተዳደር ቦርድ በወረዳ እና በሀገራዊ የመጅሊስ መዋቅር ብቻ የሚደራጀውን የዘካ አሰተዳደር ተቋምየሚቆጣጠር ሲሆን ተጠሪነቱ ለተደራጁበት እርከን ጠቅላላ ጉባኤ የሆነ ስብስብ ነው፡፡
2. የዘካ አስተዳደር ቦርድ በሥራአመራርቦርድ አቅራቢነትበጠቅላላ ጉባኤው ይደራጃል፡፡
3. የቦርዱ አባላት ዘጠኝ(9) ሲሆኑ የስብጥሩ ተዋጽኦም፡-
   3.1. ከዘካ ሰጭ ዋነኛ ባለሃብቶች 3 አባላት፤
   3.2. ከኡለማ ምክር ቤት 2 አባላት፤
   3.3. ከታዋቂ ዳኢዎች(ሰባኪዎች) 2 አባላት፤
   3.4. የሂሳብ አዋቂን ጨምሮ ከምሁራን 2፤
4. የዘካ አስተዳደር ቦርድ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አሉት፡-
   4.1. የዘካ ስብሰባ፣ አስተዳደር እና ሥርጭት ሽሪዓውን በተከተለ አኳኋንና ሕገ-መጅሊሱ በዘረጋው አሰራር መሰረት በዘካ አስተዳደር ተቋም መከናወኑን መከታተልና መቆጣጠር፤
   4.2. በአንቀጽ 51(2) በተደነገገው አኳኋን የዘካ ስርጭት የ60/40 ምጣኔን መሰረት በማድረግ ወረዳና የሀገራዊ የዘካ ስርጭት ክፍፍል መደረጉን ማረጋገጥ፤
   4.3. የዘካ አስተዳደር ተቋም የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን መመልመል፣መቅጠርና በህግ ማሰናበት፤
   4.4. ተጠሪ ለሆኑለት ጠቅላላ ጉባኤ ዓመታዊ የሥራ እቅድ እና የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብና በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ማከናወን፤
   4.5. የዘካ አስተዳደር ተቋምን ዓመታዊ በጀት አዘጋጅቶ ለየጉባኤው ማቅረብና ሲጸድቅለት መተግበር፡፡
   4.6. ለዘካ ሰጭዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራትና ማነቃቃት፤
   4.7. ለዘካ ሰጭዎች ባላቸው ህብትና ንብረት ላይ ተመስርቶ ሲጠየቁ ስለ ፊቂሃዊ የዘካ አሰጣጥ ስሌት የምክር አገልግሎት መስጠት እና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

### አንቀጽ 54
### የዘካ አስተዳደር ቦርዱ ስብሰባዎች

1. የዘካ አስተዳደር ቦርዱ በየወሩ ቢያንስ አንዴ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል፡፡
2. በቦርዱ ስብሰባ ከግማሽ በላይ ወይም አምስት አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ የሚሆን ሲሆን ቢያንስ አንዱ ከኡለማ አባላት መሆን አለበት፡፡
3. ቦርዱ ሰብሳቢውን ከኡለማ አባላቱ መካከል ይመርጣል፣ የሰብሳቢው ድምጽም በእኩል ድምጽ ወቅት መለያ ይሆናል፡፡

4. ሁሉም የጉባኤው ውሳኔዎች የሚፈጸሙት በግልጽ ሆኖ የሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ አይፈቀድም፡፡
5. የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፋት በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡
6. ሁሉም ዓይነት የቦርዱ ስብሰባዎችና ውሳኔዎች፣ ምርጫዎችና የምርጫ ሂደቶች ኢስላማዊ አደብን፣ መርህን በተከተለ አኳኋን መደረግ አለበት፡፡
7. የቦርዱ አባላት ያለ ደሞዝ የሚያገለግሉ የበጎ ፈቃደኞች ስብስብ ሆኖ በትርፍ ጊዜ የክፍያ ቀመር ለሥራው በተገኙበትና ለውይይት በታደሙበት ጊዜ ልክ በቁርጥ ክፍያ ቀመር አበል መክፈል ይቻላል፡፡

## አንቀጽ 55
## የዘካ አስተዳደር ተቋም

1. የዘካ አስተዳደርተቋም ተጠሪነቱለዘካ አስተዳደርቦርድ የሆነ በሀገራዊው እና በወረዳ መጅሊስ ብቻ የሚቋቋም ዘካ ሰብሳቢና አከፋፋይ ተቋም ሲሆን ስልጣንና ተግባራቱም የሚከተሉት ናቸው፡-
   1.1. ኢስላማዊ ደንብና ሥርዓትን በተከተለ አኳኋን ከዘካ ሰጭዎች በውክልና ለሚገባቸው ሰዎች እንዲደርስለት የሚሰጠውን የዘካ ሀብትና ንብረት ተረክቦ ለሚገባቸው ዘካ ተቀባዮች ማድረስ፤
   1.2. ዘካ ሰጭዎች ሲጠይቁ ስለአጠቃላይ የዘካ አፈጻጸም እና ዘካቸው ስለዋለበት ሁኔታ ማብራሪያ መስጠት(በተለይ በቅድመ ሁኔታ ዘካ የሰጡ ሰዎችን ሸርጣቸው ስለመፈጸሙ ማስረዳት)፤
   1.3. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና የአፈጻጸም ሪፖርት ለዘካ አስተዳደር ቦርድ ማቅረብና በሚሰጠው አቅጣጫና አመራር መሰረት ውሳኔውን መተግበር፤
2. ዘካ ሰጭዎች ለስርጭቱ ያስቀመጡት የአፈጻጸም ተገቢ ቅድመ ሁኔታ(ሸርጥ) ካልኖረ በስተቀር ከየትኛውም ወረዳ የሚሰበሰብ ዘካ ቢያንስ ስድሳ በመቶው ዘካው ለተሰበሰበበት አካባቢ ዘካ ተቀባዮች መዋል ያለበት ሲሆን ቀሪው አርባ በመቶ ለሀገራዊው የዘካ አስተዳደር ተቋም በመላክ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለዘካ ተቀባዮች ይከፋፈላል፡፡
3. የዘካ ስርጭት በተቻለ መጠን ድህነትን ለዘለቄታው በሚፈታ አኳኋንና ዘካ ተቀባዮችን የሥራ ባህል በማላበስ ወደ ዘካ ሰጭነት በሚያሸጋግር ዘዴ በምክር ታግዞ መተግበር አለበት፡፡
4. የዘካ አስተዳደር ተቋሙ ለሚሰራቸው ሥራዎች ዘመናዊ የሂሳብና የመዝገብ አያያዝ ሳይንሳዊ ሥርዓቶችን መተግበርና ዓመታዊ ኦዲት ማድረግ ያለበት ሲሆን ለየትኛውም የገንዘብ እንቅስቃሴዎች የገቢ እና የወጭ ደረሰኝመስጠት አለበት፤
5. ተቋሙ በንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰውን ለመተግበር ያመቸው ዘንድ በዘርፉ ሙያተኞች ሊያደራጅ ይገባል፡፡
6. ብሄራዊው የዘካ አስተዳደር ተቋም ከየወረዳው የሚሰበስበውን የአርባ በመቶ ዘካ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጥናት ለተለዩየዘካ ተቀባይ አካባቢዎች እንደ አስፈላጊነቱ ይውላል፡፡
7. የኡለማ ምክር ቤቱ በሚያወጣው የዘካ ፖሊሲና መመሪያመሰረት በወረዳና በሀገራዊ ደረጃ ይፈጸማል፡፡

## ንዑስ-ምዕራፍ ስድስት
## መንፈሳዊ የግልግል ሸንጎ

## አንቀጽ 56
## የሸንጎው አባላት እና ተጠሪነት

1. ሸንጎው በሀገራዊውእና በክልል ጠቅላላ ጉባኤዎች በሀገራዊውና በክልል እርከን ብቻ የሚደራጅ የሕገ-መጅሊስ፣የሥነ-ሥርዓትና የምዕመናን ጉዳዮች አማራጭ የግጭት መፍቻ የግልግል ተቋም ሲሆን የሙፍቲዎች ጉባኤ እና የኡለማ ጽ/ቤት አባል ካልሆኑ የኡለማምክርቤትሶስት፣ በማህበረሰባዊአገልጋይነታቸው ከታወቁ የሀገርሽማግሌ አንድአባል፤ከሕግምሁራን ሁለትአባላት እና በጠቅላላ ጉባኤአስፈላጊነቱ የታመነበት አንድ ሌላ አባል ያቀፈ የሰባት አባላት ስብስብ ሲሆን ጠቅላላ ጉባኤው ካመነበትና የሥራ ጫና ከተፈጠረ ተጨማሪ ስብስብ በተመሳሳይ ተዋጽኦና ስብጥር ሊጨምር ይችላል።
2. ሁሉም አባላቱ በተቻለ መጠን በቀደመ ሥራቸው በገለልተኝነትና በሚዛናዊነት የሚታወቁ ሆነው በእርቅ፣ በግልግልና በዳኝነት ተኮር ሥራዎችና በማህበራዊ አበርክቶዎች ልምድ ያላቸውሆኖ ዕድሜያቸው ቢያንስ 40 ዓመት የሞላቸው ሆኖ ሰብሳቢው ከኡለማ ምክር ቤትከታቀፉትአባላት መካከል ይመርጣሉ።
3. ሸንጎው ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ ሥራውን ለማከናወን የሚያስችለውን ጽ/ቤትና የሰው ሃይል ያደራጃል።
4. በሸሪዓ ፍርድ ቤት ቃዲዎች ምልመላና ስልጠና ክፍል እንዲሁም ከህግ አገልግሎት ክፍል ጋር በመቀናጀት ሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤው የግልግል ሸንጎው የዕለት ተዕለት የግጭት አፈታት የግልግል ሥራው የሚመራበትን የግልግል ሥነሥርዓት መመሪያ ሸንጎው ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት ማውጣት አለበት።
5. ማናቸውም የሸንጎው አባል የሥነሥርኣት ጉድለት ወይም ጉልህ የአቅም ውስንነት ወይም ኃላፊነትን በብቃት ለመወጣት የማያስችል ሌላ ማናቸውም ምክንያት መኖሩ ሲታመን በኡለማ ምክር ቤት ጠያቂነት በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ሊሰናበት የሚችል ሲሆን የጉባኤው ስብሰባ እስኪደርስ አባሉን ማቆየት ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ሲታመን የሸንጎው አባላት አቤቱታ ከቀረበበት አባል ውጭ የሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ እስከ ቀጣዩ የጉባኤው ስብሰባ ከሥራ ሊያግደው ይችላል።

## አንቀጽ 57
## የሸንጎው ስልጣንና እና ተግባር

1. የሸንጎው አባላት ለሸሪዓው፣ ለህገ-መጅሊሱና ለህሊናቸው ብቻ ታማኝ ሆነው በስልጣን ክልላቸው በቀረቡላቸው ጉዳዮች ተወያይተው ፅኑ (አስገዳጅ) ውሳኔ ያሳልፋሉ።
2. በስልጣን ክልላቸው ሸንጎው የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች በሁሉም የመጅሊስ እርከን አመራሮች፣ ሰራተኞች፣አባላትና ውሳኔው በሚመለከተው ምዕመን መፈጸም አለበት።
3. የግልግል ሸንጎው በሶስት ርዕሰ-ጉዳዮች ማለትም በሕገ-መጅሊስ አተረጓጎም፣ በሥነ-ሥርዓታዊ ጥሰቶችና በምዕመናን መካከል በሚነሱ መጅሊስ ተኮር አለመግባባቶች ላይ መርምሮና በማስረጃ አጣርቶ የግልግል ውሳኔ ይሰጣል፤

4. በሙስሊሙ ማህበረሰብ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በፈቃድ ላይ የተመሰረተ የእርቅ ሥራ ይሰራል፤

5. በሚከተሉት ጉዳዮች እንደ ጉዳዩ ባህሪ በሕገ-መጅሊስ ተርጓሚነት ወይም በሥነ ሥርኣት አስከባሪነት ወይም በአስታራቂ ገላጋይነት ያያል፦

   5.1. በየትኛውም መዋቅርና ደረጃ የሚገኝን ማናቸውም የመጅሊስ አባል፣ አመራርና አገልጋይ አድራጎቶች ወይም ውሳኔዎች ህገ-መጅሊሱን ይቃረናል የሚል ሥነ-ሥርዓቱን ተከትሎና የበታች አስተዳደር አካላትን መፍትሄ አሟጥጦ የሚቀርብን ጥያቄ ያያል፤

   5.2. የትርጉም ጥያቄ በሀገራዊ ጉዳይ በቀጥታ በክልል ጉዳዮች ደግሞ በይግባኝ የሚከተሉትን ጉሥነ-ሥርዓቱን ተከትሎና የበታች አስተዳደር አካላትን መፍትሄ አሟጥጦ የሚቀርብን ዳዮች ያያል፤

   5.3. በማናቸውም የሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም የኡለማ ምክር ቤት ወይም የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ወይም የአማካሪ ቦርድ ወይም የዘካ አስተዳደር ቦርድ አባል የሥነ ምግባር እና የሥነ ሥርዓት ጥሰቶች ሲፈጸሙና ጠቅላላ ጉባኤው በማናቸውም ምክንያት ወይም በዚህ ሕገ-መጅሊስ ጉዳዩን በዲሲፕሊን እንዲያይ ስልጣን የተሰጠው አካል ጉዳዩ በሸንጎው እንዲታይ ሲወስን አቤት ባዩንና አቤቱታ የቀረበበትን አባል በማድመጥ ሥነ-ሥርዓታዊ የግልግል ውሳኔ ይሰጣል፤

   5.4. በየትኛው የሪፐብሊኩ የግዛት ወሰን በሚገኙ ሙስሊሞች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሌሎች ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ሳይፈቱ ቀርቶ ወደ ሀገራዊ ጉዳት የመሻገር አዝማሚያ የታየባቸውን ጉዳዮች በገላጋይነት ማስታረቅ፤

   5.5. ከሪፐፕሊኩ ከእርቀ-ሰላም እና የወሰን ኮሚሽን እንዲሁም ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሀገራዊ ግጭቶች ሲኖሩ በአፋጣኝ በሚፈቱበት ዙሪያ በቅርበት መሥራትና በጥናትና ምርምሮች የእስልምናንና የሙስሊሞችን ተሞክሮ ማካፈል፤

   5.6. በዚህ ምዕራፍ ስለ ሸንጎው ሥልጣንና ተግባር የተደነገጉት አናቅጽ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ አግባብ ባለው ሕግ ለሌላ አካል የተሰጠን የዳኝነት ሥልጣን አይነካም፤

6. በማንኛውም የመጅሊስ እርከን በምርጫ፣ በምድባም ሆነ በቅጥር በተለያየ ኃላፊነት፣አባልነትና የሥራ የሚቀላቀል ማናቸውም ሰው በቅድሚያ በዚህ ሕገ-መጅሊስ ለመመራትና የመንፈሳዊ ሸንጎውን ውሳኔ ለማክበር ስምምነቱን በጽሁፍ መግለጽ ያለበት ሲሆን የቅጥርና የምደባ ውሎች ይህንኑ የሚገልጽ ድንጋጌ ማካተት አለበት።

7. ሸንጎው ለመጀመሪያ ጊዜ በሚያያቸው ቀጥታ ጉዳዮች ላይቅር የተሰኘ ወገን የግልግል ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ ለሚኖረው ጠቅላላ ጉባኤውሳኔው እንዲከለስለትይግባኝ መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን ጠቅላላ ጉባኤው በጉዳዩ ባህሪ ላይ የሚመለከት ቋሚ ኮሚቴ በማደራጀት ጉዳዩን በመገምገም የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

## ምዕራፍ ሶስት
## የሀገራዊ መጅሊስ የኡለማ መዋቅር ዝርዝር አደረጃጀት

## ንዑስ-ምዕራፍ አንድ
## ሀገራዊ የኡለማ ምክር ቤት

### አንቀጽ 57
### የኡለማ የአንድነት እና የትብብር መተዳደሪያ የቃል ኪዳን ሰነድ አስገዳጅነት

1. የኡለማ የአንድነት እና የትብብር የቃል ኪዳን ሰነድ የዚህ ሕገ-መጅሊስ አካል የሆነና በመላው የመጅሊስ መዋቅር እና በመዋቅሩ በሚሳተፍ ማናቸውም ኡለማና ሙስሊም ዘንድ አስገዳጅ ሕገ-ደንብ ነው።
2. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች ከዚሁ የኡለማ የአንድነት እና የትብብር የቃል ኪዳን ሰነድ ጋር ተጣጥሞ መተርጎም አለበት።

### አንቀጽ 58
### የሀገራዊ ኡለማ ምክር ቤት አመሰራረት

1. የሀገራዊ ዑለማ ምክር ቤት ሃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ ተግባራትን የሚመራና የሚያስተባብር ከሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤው ቀጥሎ የመጅሊስ ላዕላይ ተቋም ነው።
2. የዑለማ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ነው።
3. የዑለማ ምክር ቤት አባላት ቁጥር 35 ሆኖ ተዋፅኦውም እንደሚከተለው ነው፡-

   3.1 ለሕዝበ ሙስሊሙ አንድነት ሲተጉ የነበሩት ሙፍቲ ሀጅ ዑመር እድሪስና ዶ/ር ጄይላን ከድር

   3.2 በሙፍቲ ሀጅ ዑመር እድሪስና ዶ/ር ጄይላን ከድር አስተባባሪነት ከእያንዳንዱ ክልል ከሁለቱ ዋና አስተሳሰቦች በአንቀጽ 58 ለሀገራዊ ዑለማዎች ምክር ቤት ለአባልነት የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ አንዳንድ የበቁ ዓሊሞችን በመምረጥ ማለትም ከየክልሉ ሁለት ሁለት ዓሊሞችን በድምሩ 22 ዓሊሞች

   3.3 የእያንዳንዱ የክልል የክልሉ መሪ ሙፍቲ ሆነው የሚመረጡ አንዳንድ ዓሊሞች በድምሩ11 አባላት፤
4. ሀገራዊው ዋና ሙፍቲው የኡለማ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ይሆናል፣
5. የዑለማ ምክር ቤቱ ከአባላቱ መካከል የራሱን ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሃፊ ይመርጣል፣

### አንቀጽ 59
### ለሀገራዊዑለማዎች ምክር ቤት የአባልነት መስፈርት

የሀገራዊ ኡለማ ምክር ቤት አባል የሚሆኑ ሰዎች የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡-

1. ዕድሜው ከአርባ ዓመት ያላነሰ፤

2. በኢስላማዊ ትምህርት ከታወቀ ኢስላማዊ ዩኒቨርስቲ ወይም ኮሌጅ ቢያንስ ሁለተኛ(የማስተርስ) ዲግሪ ያለው ወይም በሀገር በቀል የቁርኣትና የዒልም ማዕድ ተመጣጣኝ እውቀት ያለው ሆኖ ከአራቱ መዝሀቦች ቢያንስ አንዱን አጠቃሎ ያወቀና የተማረ(የተዓለመ)፤
3. የቁርኣን ተፍሲር ያጠናቀቀ፣ የአረብኛ ቋንቋ ክህሎት ያለው፣ኩቱቡ ሲትታን ያጠናቀቀና ከአስር ዓመት በላይ በማቅራት ላይ የሚገኝ፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የተመጣጣኝነት መመዘኛ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው የዓሊሞች ስብስብ መለኪያ ያወጣሉ።
5. በማናቸውም ቦታና ሥራ ከሥነ-ምግባር ጋር በተያያዘአቤቱታ ወይም ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ያልተባለ፤

## አንቀጽ 60
## ከሀገራዊው የዑለማ ምክር ቤት አባልነት የሚያሰናብቱ ሁኔታዎች

1. ማንኛውምየዑለማ ምክር ቤት አባልከሚከተሉትምክንያቶች በአንዱ በኡለማ ምክር ቤት ጠያቂነትበጠቅላላጉባኤ በሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰናበት ይችላል፡-
   1.1. ከደንብ መተላለፍ በላይ በሆነ በወንጀልጥፋተኛ መሆኑ በውሳኔ ከተረጋገጠ፤
   1.2. ለተሰማራበት ተምሳሌታዊ የኡለማ ሃላፊነት ተቃራኒ በሆነ ቦታና ሥራ ላይ ሲገኝና መጥፎ አርአያነቱ ለምክር ቤቱ ስምና ዝና የማይመጥንና ክብሩን የሚያጎድፍ ሲሆን፤
   1.3. ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ጉልህ የእውቀትና የአፈጻጸም ጉድለት ሲስተዋልበት፤
   1.4. እንዲሁም ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ከባድ ጥፋቶች መፈጸማቸው ሲረጋገጥ እና
   1.5. በኡለማ ምክር ቤቱ የሥነ ምግባር ደንብ የተደነገጉ ሌሎች ጥፋቶችን ፈጽሞ ሲገኝ፤
2. የንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የዑለማ ምክር ቤት አባል ከሚከተሉት ምክንቶች በአንዱ በክብር ከአባልነት ሊሰናበቱ ይችላል፡-
   2.1. የስድስት ዓመት የሥራ ዘመናቸው ሲጠናቀቅና በዑለሞች መካከል ብቻ በሚደረገው በቀጣዩ የዑለሞች ምርጫ ሳይመረጡ ሲቀሩ።
   2.2. ለዋና ሙፍቲው የመልቀቂያ ጥያቄ በጽሁፍ ሲያቀርቡ፤
   2.3. ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩና
   2.4. መደበኛ ሥራን ቢያንስ ለመንፈቅ ዓመት በአግባቡ ለማከናወን የማያስችል ማናቸውም ህመም ሲኖርበት፤
   2.5. የኡለማ ምክር ቤቱ ወይም ጠቅላላ ጉባኤው አቤቱታ የቀረበበት አባል የዲሲፕሊን ጥፋት ቢፈጽሙም በክብር እንዲሰናበቱ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን።
3. በክብር ለሚሰናበቱ የኡለማአባላት ተገቢው የምስጋና የኡማ አገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
4. በተሰናባች ዓሊም ቦታ ተገቢውን ሥርዓት ተከትሎ የዑለማ ምክር ቤትተተኪ አባል ይሰይማል።

5. ተሰናባቹ ዋና ሙፍቲው በሚሆኑበት ጊዜ ተተኪውን የሚሾመው ዋና ሙፍቲውን ከጅምሩ የመምረጥ ስልጣን ያለው አካል ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 61
## የሀገራዊዑለማ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የዑለማ ምክር ቤት በተለይ በዒልም ነክ ጉዳዮች ድምጽን በድምፅ በአባላቱ ሙሉ ድምፅ የመሻር መብት ኖሮት ተጠሪነቱ ለሀገራዊው ጠቅላይ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ ነው፡፡
2. በኡለማ መተዳደሪያ የቃል ኪዳን ሰነድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኡለማ ምክር ቤቱ የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራትን ያከናውናል፦
   2.1. ለሃይማኖታዊ ጥያቄዎች ተገቢውን ኢስላማዊ ህግና ደንብ ተከትሎ ብይን(ፈትዋ) ይሰጣል፤
   2.2. ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር የትምህርትና ዳዕዋ አገልግሎት አሰጣጥና የዳዒዎች የስምሪት ስርዓት፣ ደንብና መመሪያ ያዘጋጃል፤ተግባራዊ ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
   2.3. ብቃትና የላቀ ሥነ-ምግባር ያላቸው የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞችን በህግ መሰረት በመመልመል ለፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በማቅረብ እንዲሾሙ ያደርጋል፤
   2.4. የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት አገልግሎት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ተጠቃሚ መሆኑን ይከታተላል፤
   2.5. የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በስልጣን ክልላቸው የሚሰሩባቸውን የሸሪዓ ህጎች(ኮድ) በመጽሃፍ መልክ ይሰንዳል(የኮዲፊኬሽንሥራ ይሰራል)፤
   2.6. ጥንታዊና ዘመናዊ ኢስላማዊየትምህርትማዕከላት እንዲጠናከሩ ድጋፍ ያደርጋል፣ አዳዲሶች እንዲቋቋሙ ጥረት ያደርጋል፣ለወቅቱ የሚመጥን ዘመናዊ የአሰራር ስርዓት አዘጋጅቶ ይተገብራል፤
   2.7. በመላ ሀገሪቱ በመጅሊስ መዋቅር ስር በተደራጁ ኢስላማዊ የቁርዓትና የትምህርት ማዕከላትወይም የዒልም ቦታዎች አንድ ወጥ የትምህርት ስርዓት እንዲኖር ሀገራዊ ደረጃ(National Standard) አዘጋጅቶ ያስፈጽማል፤
   2.8. ሀገራዊ መስፈርትና ደረጃ(Standard) በማውጣት ለዳዒዎች፣ ለኢስላማዊመምህራን (ሙደሪሶች/ኡስታዞች) እና ለኢማሞች እውቅና ይሰጣል እንዲሁም ለኢስላማዊ የትምህርትና የዒልም ተቋማትእና ለዳዒዎች የማስተማር ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
   2.9. ዳዒዎችና ዑስታዞች መንፈሳዊ ትምህርት ለማስተማር ወይም ለዳዕዋሥራ ሲንቀሳቀሱ በኃላፊነት መንፈስ መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ስህተት ሲኖርም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤
   2.10. ዑለማዎችን በተመለከተ ከመንግስት አካላት፣ ከሌላ እምነት አቻ ተቋማት፣ ከህዝባዊና ከግል ድርጅቶችና ከግለሰቦች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣ በትብብር ይሰራል፤

2.11. የሙፍቲዎች ጉባኤና የኡለማ ጽ/ቤት በስሩ በማዋቀር በሥራቸው የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን ያደራጃል፤

2.12. የዋና ሙፍቲውን ጽ/ቤትንና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎችን ያደራጃል፣ በሥሩ ያሉ ዘርፎችን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ሪፖርታቸውን ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ውሳኔ ያሳልፋል፤

2.13. በውጭ ሀገርኢስላማዊ የትምህርት ተቋማትናዩኒቨርሲቲዎች ተምረው የመጡ ተማሪዎች ለሚያቀርቡት የትምህርት ማስረጃ የእውቅና የምስክርወረቀት ይሰጣል፤

2.14. የሃላል እውቅና ለሚያሻቸው ምርቶችና አገልግሎቶችተገቢውን ክፍያ በማስከፈል የሀላል ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

2.15. በላቀ ሥነ ምግባር እና በሀገር ፍቅር የታነጸዜጋና ትውልድ ለመፍጠር ከሌሎች የሃይማኖት ተቋማትና እና ከመንግስት ጋር በመሆን በጋራ ይሰራል፣ ተማሪዎችን በግብረ-ገብ ያንጻል፤

2.16. የኡለማ ምክር ቤቱ የተቋቋመለትን አላማና ግብ የሚያሳኩ ልዩ ልዩ ህዝባዊ ኮንፈረንሶች፣ የምርምር አውደ ጥናቶች፣ ኤግዚቢሽኖች፣ ሲምፖዚየምና ጉባኤዎችን ያከናውናል፤

2.17. ልዩ ልዩ ጥናቶችን ያደርጋል፣ያስደርጋል፣ ያሰራጫል፤

2.18. የራሱን የሥነ ምግባር እና የአሰራር ሕገ-ደንብ ደንብ ያወጣል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

2.19. ስለ ኢስላማዊ የኪነ ጥበብ ሥራዎች ዝግጅትና ህትመት ፖሊሲና መመሪያ ያወጣል፣ እውቅና ይሰጣል፤

2.20. በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ጥንታዊና ዘመናዊ የትምህርት፣የዒልምና የቁርኣት ማዕከላት መረጃ ያሰባስባል፣ስታቲክስ ያደራጃል፣ ለጥናት አገልግሎት ያውላል፤ የመረጃና የስታቲክስ ውጤቱን በግብአትነት ተጠቅሞ የማጣናከሪያ ሥራዎችን ይሰራል።

2.21. በላቀ-ሥነ-ምግባር የታነጸ ሙስሊም ለመፍጠር የደረጀ የተርቢያ ሥርዓት ይፈጥራል፤

2.22. የኡለማ፣የዱዓትና የኢማሞች ስልጠና ተቋም ያደራጃል፣ የማብቃት ሥራ ይሰራል፤

2.23. የኡለማ የዱዓትና የኢማሞች የገቢ አቅም የሚዳብርበትን ሁናቴ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤

2.24. ድንበር ዘለል ዓለም አቀፍ የኡለማ ግንኙነት በማድረግ የልምድ ልውውጥና የእውቀት ሽግግር እንዲደረግ ይሰራል፤

2.25. የሀገር አቀፍ ኡለማ አጠቃላይ ኮንፈረንስ በማዘጋጀት እውቀትና ክህሎት እንዲዳብር ይሰራል፤ ከመላው ዓለም የተመረጡ ዓሊሞችን ይጋብዛል፤

2.26. ቁርዓንና ኢስላማዊ ድርሳናት ወይም ህትመቶች በሀገር በቀል ቋንቋዎች ተተርጉመው ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

2.27. ከጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## ንዑስ-ምዕራፍ ሁለት
## የሙፍቲዎች ጉባኤ

### አንቀጽ 62
### የሙፍቲዎች ጉባኤ እና የኡለማ ጽ/ቤት አመሰራረት

1. የሙፍቲዎች ጉባኤ ተጠሪነቱ ለኡለማ ምክር ቤት የሆነ የፈትዋና የምርምር ሥራን የሚከውን የሥራ አስፈጻሚ ኡለማ ስብስብ ሲሆን ስብሰባውን በዚህ ሕገ-መጅሊስ ስለ መጅሊስ ሥራአስፈጻሚ ቦርድ በተደነገገው አግባብ ያደርጋል፡፡
2. የኡለማ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለኡለማ ምክር ቤት የሆነ እና የምክር ቤቱ የዕለት ተዕለት መደበኛ ሥራ የሚሰራ አካል ነው፡፡
3. የሙፍቲዎች ጉባኤ ሰባት አባላት ያሉት በዋና ሙፍቲው ሰብሳቢነት የሚመራ ስብስብ ሲሆን በምክር ቤቱ ይመረጣሉ፡፡

### አንቀጽ 63
### የሙፍቲዎች ጉባኤ እና የኡለማ ጽ/ቤት ስልጣን እና ተግባር

ጉባኤው የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራትን ይከውናል፡፡

1. የሙፍቲዎች ጉባኤ እና የኡለማ ጽ/ቤት የኡለማ ምክር ቤትን ስልጣንና ኃላፊነት በሥራላይ ያውላል፤
2. የኡለማ አስተዳደር ጽ/ቤት የምክር ቤቱን አጠቃላይ በጀት በማዘጋጀት ለኡለማ ምክር ቤቱ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡
3. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና የአፈጻጸም ሪፖርት በማቅረብ የኡለማ ምክር ቤቱ ባስቀመጠለት አቅጣጫ ሥራቸውን ይፈጽማል፤
4. የኡለማ ጽ/ቤት በስሩ የተደራጁ የሥራ ክፍሎችን ይመራል፣ያስተባብራል፣ይቆጣጠራል፣በተገቢው የሰው ሃይል ሲፈቀድለት ያደራጃል፤
5. የሙፍቲዎች ጉባኤ ከመላ ሀገሪቱ በኡለማ ሰንሰለትና በተለያዩ የግንኙነት አውታሮች በሚመጡለትና አስፈላጊነታቸውን ባመነባቸው ልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የፈትዋና የኢስላማዊ ምርምር(በህስ) ሥራዎችን በበላይነት ይሰራል፣ለትግበራ ወደ መጅሊስ መዋቅሮች ያወርዳል፣ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፤አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡
6. የሙፍቲዎች ጉባኤ የተለየ ጉዳይ ካጋጠመውና በኡለማ ምክር ቤቱቢታዩይሻላል ብሎ ያመነባቸውን ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በመምረጥ ለምክር ቤቱ ያስተላልፋል፣
7. ሌሎች ከሥራቸው ባህሪ የሚመነጩ ተመሳሳይ ሥራዎችንና ኃላፊነቶችን ይከውናሉ፡፡

## ክፍል ፭ አምስት
## የክልላዊ መጅሊስ መዋቅራዊ አደረጃጀት

### ምዕራፍ አንድ
### የክልል መጅሊስ

#### አንቀጽ 64
#### የክልል መጅሊስ ጠቅላላጉባኤ

1. የክልል መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ ለተቋቋመበት ክልል መጅሊስ ከፍተኛው የስልጣን አካል ነው።
2. የክልል መጅሊስ የሥራ ዘመን ከፌዴራል መጅሊስ የሥራ ዘመን ጋር ተመሳሳይ 5 ዓመት ነው።
3. የክልላዊ ጠቅላላ ጉባኤ አባላትምየሚከተሉት ናቸው፡-
   3.1. የክልሉመጅሊስ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፤
   3.2. የሁሉም የክልሉ ዞኖች መጅሊስሊቀመንበሮች፤ምክትል ሊቀመንበሮች እና ዋና ፀሐፊዎች፤
   3.3. የክልሉ ኡለማ ምክር ቤት አባላት በሙሉ፤
   3.4. ከክልሉ ኢስላማዊ ማህበራት ህብረት(ትስስር()ሁለት አባላት፤
   3.5. ከክልሉ ወጣቶች ሁለት አባላት፤
   3.6. ከክልሉ ሴቶች ማህበራት አራት አባላት፤
   3.7. በክልሉ ከሚገኙከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሙስሊም ተማሪዎች ጀመዓ ትስስር(ኔትዎርክ) ሁለት አባላት፤
   3.8. ከክልሉ ሙስሊም የንግድ ማህበረሰብ ህብረት(ትስስር)ሁለት አባላት፤
   3.9. ከክልሉ ዱዓቶች ማህበራትትስስር(ኔትዎርክ) አራት(4) አባላት፤
   3.10. ከክልሉ ምሁራንትስስር(ኔትዎርክ) ሁለት(2) ምሁራን።

#### አንቀጽ 65 (reedited by Endris)
#### የክልል መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1. የክልል ጠቅላላ ጉባዔ የክልሉ መጅሊስ ከፍተኛው የስልጣን ባለቤት ነው።

የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

የክልሉ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባር ይኖረዋል፡-

1.1. ሉዓላዊ ሙስሊሞች ከፍተኛውን ሃይማኖታዊ ሥልጣናቸውን በእንደራሴዎቻቸው፣ በዓሊሞቻቸው እና በባለድርሻ ሙስሊም አካላቶቻቸው በኩል የሚተገብሩበት የእስልምና ጉዳዮችን በተመለከተ በክልሉ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ህዝበ ሙስሊሙን ለማገልገል ይሰራል። በመሆኑም በክልሉ ሙስሊሙን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ክልላዊ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ውሳኔ ያሳልፋል።

1.2. የክልሉን የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ እና የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴን ከአባላቱ መካከል እንዲሁም የዘካ አስተዳደር ቦርድ አባላትን ደግሞ በዚህ ህገ-መጅሊስ መሰረት ከአባላቱ ውጭ ይሾማል፣ ይቆጣጠራል፣ይሽራል፣ ሪፖርት እየሰማ እና እያጣራ አስፈላጊውን ይወስናል፤

1.3. እንዳስፈላጊነቱ የክልሉን ሕገ-መጅሊስ ላይ በአንቀጽ ….. … እና …. በተደነገገው አኳኋን የማሻሻያ ሀሳብ ያመነጫል፤ ያሻሽላል ይለውጣል፤

1.4. በሀገራዊ ሥራ አመራር ቦርድና በሀገራዊው ዑለማ ምክር ቤት ተረቀው የሚቀርቡለትን የመጅሊስ የምርጫ መመሪያ፣ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች የህገ-መጅሊሱ ማስፈጸሚያ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ያስፈጽማል።

1.5. የዑለማዎች ምክር ቤት በክልሉ መቋቋሙን ያረጋግጣል።

1.6. በሥራ አመራር ቦርድ አቅራቢነት የክልሉን መጅሊስ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል።

1.7. በሥራ አመራር ቦርድ እና በሀገራዊው የዑለማዎች ምክር ቤት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የየተቋማቸውን የበጀት ዓመት የሥራ እቅድ፣የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና ዓመታዊ በጀት ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፣ ያጸድቃል፣ የሥራ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ መመሪያ ይሰጣል፤

1.8. ክልሉን በተመለከተ የውጪ ኦዲትና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሪፖርትን መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል።

1.9. በክልሉ የሥራ አመራር ቦርድ ተጠንተው የሚቀርቡ የተለያዩ የሥራ ፕሮጀክቶችንና የልማት ትልሞችን መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል።

1.10. የተቋሙ ዓላማዎች በተግባር ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

1.11. የኡለማ ምክር ቤት አባላትን ጨምሮ የሥነ-ምግባር ግድፈትና ጥፋት በሚፈጽሙ አባላት ላይ የመጨረሻውን አስተዳደራዊና እስከ ስንብት የሚደርስ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲሁም ለህግ ክፍል እና ለመንፈሳዊ ሸንጎ መቅረብ ያለባቸውን ጉዳዮች በመለየት ተገቢውን ይወስናል፤

1.12. የክልሉ ጠቅላላ ጉባዔ አባል በሞት ወይም በዕድሜ ወይም በመልቀቂያ ወይም በስንብትና በማናቸዉም ምክንያት ጠቅላላ ጉባዔውን ከለቀቀ በተሰናበቱት ምትክ የሥራ ሽግሽግ ደርጋል፤ በተጓደሉ አባላት ቦታ በዚህ ህገ-መጅሊስ በተደነገገው አኳኋን እንዲተኩ ያደርጋል።

1.13. መብትና ጥቅሞቹ የተጠበቁለት አንድ ወጥ አገልግሎት ለማህበረሰቡ ለመስጠት እንዲቻል በክልል መጅሊስ የሚወጡ ስትራቴጂዎች፣ደንቦችና መመሪያዎች የየአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጨምረው በፌዴራል ደረጃ ከወጡ የመጅሊስ ስትራቴጂዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተቃርኖ የሌላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣ በኦዲትና ኢንስፔክሽን የተቃርኖ ሪፖርት ሲቀርብለትም መርምሮ ይወስናል።

1.14. የክልሉ የመጅሊስ መዋቅሮች ደንብና መመሪያዎችን አክብረው ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ስህተቶች እንዲታረሙ ያደርጋል።

1.15. ከሀገራዊው መጅሊስ የምስረታ ዓላማ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል።

1.16. በሀገራዊ ጠቅላላ ጉባዔ የፀደቁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን በክልሉ በተዋረድ ባሉ የመጅሊስ አካላት ተግባራዊ ያደርጋል፣ያስደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

1.17. በክልሉ የሚኖረው ሙስሊም ማህበረሰብ ልጆች የእስልምና ሃይማኖት ትምህርትና ሥነ-ምግባር ተምረው ለማደግ የሚያስችሉ መዋዕለ ህፃናት፣ መድረሳዎችና የቁርኣን ት/ቤቶችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ በተጨማሪም የግል ባለ ሃብቶችና በጎ አድራጊዎች ተመሳሳይ ተቋማትን ለማቋቋም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋል፤

1.18. በክልሉ ውስጥ ያሉ የሌላ እምነት ተከታዮችን መብት ባከበረ መልኩና በህገ መንግስቱ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ የእስልምና ሃይማኖት እንዲስፋፋ የዳዕዋ ሥራዎችን የሚሰሩ ተቋማት ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

1.19. የክልሉ ነዋሪ ሙስሊም ዜጎች በግልም ሆነ በጋራ ሃይማኖታቸውን ለመግለጽና ለመተግበር ያላቸውን ህገመንግስታዊ መብትና ነፃነት በኃይል ወይም በማንኛውም ህገወጥ መንገድ እንዳይገደብ ይከታተላል፣ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ይሰራል፣ ይታገላል፤

1.20. በእስልምና ሃይማኖት እውቅና የተሰጣቸው ዘካ፣ ወቅፍ፣ ሰደቃና የመሳሰሉት ማህበራዊ የመረዳጃ ስርዓቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሰራርና ህብረተሰቡን በሚጠቅም መንገድ እንዲፈጸሙ አግባብ ያላቸው የአስተዳደር ተቋማትን በክልሉ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

1.21. የክልሉመጅሊስ ህብረተሰቡን በሚያገለግልባቸው የትምህርትና የማህበራዊ አገልግሎት ዘርፎች ተመሳሳይ አገልግሎት ከሚሰጡ ሌሎች ህጋዊ ሰውነት ካላቸው አካላት ጋር በትብብር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤

1.22. የክልሉ መጅሊስ በክልሉ የሚገኙ መስጅዶችን ያስተዳድራል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች መስጂዶች በመጅሊሱ በራሱ ወይም በሌሎች በጎ አድራጊዎች ድጋፍ

የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ መስጂዶች ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

1.23. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የክልሉ/የከተማ አስተዳደሩ መጅሊስ በህግ ከተቋቋሙ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት አግባብነት ያላቸውን ህጎች ባከበረ መልኩና በትብብር መንፈስ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤

1.24. የክልሉ መጅሊስ በስሩ በሚቋቋሙ የተለያዩ ዘርፎች መካከል ውጤታማ የሥራ ግንኙነት መኖሩን የሚያረጋግጡ፣ በዝርዝር የሰፈሩ ኃላፊነቶቹን በብቃት ለመወጣት እንዲችል ሙያዊ አገልግሎት የሚሰጡ፣ በእቅድ የተቀመጡ ሥራዎች ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መከናወናቸውን የሚያረጋግጡ የአስተዳደር መዋቅሮችን ያደራጃል፣ ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣ ሥራቸውን ይገመግማል፣ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፤

1.25. የክልሉ መጅሊስ በስሩ ለሚቋቋሙ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ተገቢው ሥራና ኃላፊነት መሰጠቱን ያረጋግጣል፣ ከመጅሊሱ ወቅታዊ የሥራ መርሐ ግብር ጋር ተቀናጅተው ለመሥራት የሚያስችል ፖሊሲና መመሪያ መኖሩን ያረጋግጣል፣ ከሀገራዊ መጅሊስ የማይጣረስ መሆኑን ይቆጣጠራል፤

1.26. የክልሉ ሙስሊም ማህበረሰብ በፌዴራል የእስልምና ጉዳዮች ሀገራዊ መጅሊስ ሚዛናዊ ውክልና ማግኘቱን ያረጋግጣል፤

1.27. ለክልሉ አስተዳደሩ መጅሊስ በየሥራ ዘመኑ የተመደበው በጀት ለትክክለኛ ዓላማ መዋሉን የሚከታተል የኦዲትና የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤

1.28. የክልሉን የዑለማ ምክር ቤትና የክልሉን የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፤

1.29. የሀገራዊውን መጅሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ እንዳስፈላጊነቱ የክልሉን መጅሊስ መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

1.30. የክልሉን መጅሊስ ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት ያፀድቃል፤

## ምዕራፍ ሁለት
## የዞን መጅሊስ

### አንቀጽ 66
### የዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ

1. የዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ በተቋቋመበት ዞን የመጅሊስከፍተኛው የስልጣን አካል ነው::
2. የዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ የሥራ ዘመን የክልሉ መጅሊስ የሥራ ዘመን ነው::
3. የዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት የሚከተሉት ናቸው፡-

3.1. የዞኑ መጅሊስ ሥራ አስኪያጅ፣ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እና ዋና ፀሐፊ፤

3.2. እያንዳንዱን ወረዳ በመወከል ወደ ዞን የሚላኩ አንዳንድ ተመራጮች፤

3.3. የወረዳ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ሊቀመናብርት፤

3.4. የዞኑኡለማ ምክር ቤት አባላት በሙሉ፤

3.5. በዞኑ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ ኢስላማዊ ድርጅቶች መሪዎች፤

3.6. በዞን ደረጃ ያሉ የዱዓቶች፣የሴቶች፣የወጣቶች፣የምሁራን፣የተማሪዎች፣የሙስሊም እድሮች ህብረትና ሌሎች ስብስቦች መሪዎች፤

3.7. በችሎታቸውና በሙያዊ ብቃታቸዉ የታወቁና ለዞኑሥራ አመራር ቦርድ የተሻለ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ በዞኑነዋሪ ከሆኑ ሙስሊሞች መካከል የሚመረጡ አራት(4) ምሁራን።

## አንቀጽ 67
## የዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1. የዞን መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠሪነቱ ለዞኑ ሙስሊም ማህበረሰብ ነው።
2. የዞንመጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

2.1. በክልሉመጅሊስ የፀደቁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና ውሳኔዎች በዞኑ በተዋረድ ባሉ የመጅሊስ አካላት ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

2.2. የዞኑ/የክፍለ ከተማው ሙስሊም ማህበረሰብ ሃይማኖቱን ለማወቅ የሚረዱ የትምህርት ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

2.3. በዞኑ የሚኖረው ሙስሊም ማህበረሰብ ልጆች የእስልምና ሃይማኖትን ትምህርትና ሥነ-ምግባር ተምረው ለማደግ የሚያስችሉ መዋዕለ ህፃናት፣ መድረሳዎችና የቁርኣን ት/ቤቶችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ በተጨማሪም የግል ባለ ሃብቶችና በጎ አድራጊዎች ተመሳሳይ ተቋማትን ለማቋቋም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋል፤

2.4. በዞኑውስጥ ያሉ የሌላ እምነት ተከታዮችን መብት ባከበረ መልኩና በህገ መንግስቱ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ የእልምና ሃይማኖት እንዲስፋፋ የዳዕዋ ሥራዎችን የሚሰሩ ተቋማት ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

2.5. የዞኑ ነዋሪ ሙስሊሞች በግልም ሆነ በጋራ ሃይማኖታቸውን ለመግለጽና ለመተግበር ያላቸውን ህገ መንግስታዊ መብትና ነፃነት በኃይል ወይም በማንኛውም ህገወጥ መንገድ እንዳይገደብ ይከታተላል፣ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ይሰራል፣ ይታገላል፤

2.6. በእስልምና ሃይማኖት እውቅና የተሰጣቸው ዞካ፣ ወቅፍ፣ ሰደቃና የመሳሰሉት ማህበራዊ የመረዳጃ ስርዓቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሰራርና ህብረተሰቡን በሚጠቅም መንገድ እንዲፈጸሙ አግባብ ያላቸው የአስተዳደር ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

2.7. የዞኑመጅሊስ ህብረተሰቡን በሚያገለግልባቸው የትምህርትና የማህበራዊ አገልግሎት ዘርፎች ተመሳሳይ አገልግሎት ከሚሰጡ ሌሎች ህጋዊ ሰውነት ካላቸው አካላት ጋር በትብብር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤

2.8. በዞኑ የሚገኙ መስጅዶችን ያስተዳድራል፣እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች መስጂዶች በመጅሊሱ በራሱ ወይም በሌሎች በጎ አድራጊዎች ድጋፍ የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ መስጂዶች ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ድጋፍ ያደርጋል፤

2.9. በዞኑውስጥ በህግ ከተቋቋሙ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር አግባብነት ያላቸውን ህጎች ባከበረ መልኩና በትብብር መንፈስ የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤

2.10. በዚህ ደንብ የተሰጡትን ኃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት ሙያዊ አገልግሎት የሚሰጡ፣በእቅድ የተያዙ ሥራዎች ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መከናወናቸውን የሚያረጋግጡ የአስተዳደር መዋቅሮችን ያደራጃል፣ ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ያሰናብታል፣ ሥራቸውን ይገመግማል፣ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፤

2.11. የዞኑሙስሊም ማህበረሰብ በክልልመጅሊስ ሚዛናዊ ውክልና ማግኘቱን ያረጋግጣል፤

2.12. በየሥራ ዘመኑ ለዞኑ/ለክፍለ ከተማው መጅሊስ የተመደበው በጀት ለትክክለኛ ዓላማ መዋሉን የሚከታተል የኦዲትና የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤

2.13. የዞኑንየዑለማ ምክር ቤትና የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፤

2.14. የዞኑንመጅሊስ ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት ያፀድቃል፤

2.15. ከላይ የተጠቀሱትን ኃላፊነቶቹን ለመወጣት ይችል ዘንድ ከክልሉ/ከከተማ አስተዳደሩ መጅሊስና ከዞኑ/ከክፍለ ከተማው ሙስሊሞች የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ምዕራፍ ሶስት
## የወረዳ መጅሊስ

### አንቀጽ 68
### የወረዳ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ

1. የወረዳ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ በተቋቋመበት ወረዳ የመጅሊስ ከፍተኛው የስልጣን አካል ው።
2. የወረዳ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ከስድስት ወር ነው።
3. የወረዳ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚከተሉት ናቸው፦
   3.1. የወረዳው መጅሊስ ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር እና ዋና ፀሐፊ፤
   3.2. በወረዳው ያሉ የመስጂድ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፤
   3.3. የወረዳውየኡለማ ምክር ቤት አባላት በሙሉ፤
   3.4. በወረዳ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ ኢስላማዊ ድርጅቶች ተወካዮች፤

3.5. በወረዳው ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ የወጣቶች፣የዱዓቶች፣ የሴቶች፣የሙስሊም ሙሁራን፣ የሙስሊም እድሮች እና ሌሎች ስብስቦች መሪዎች፤

3.6. በችሎታቸውና በሙያዊ ብቃታቸዉ የታወቁና ለወረዳው የሥራ አመራር ቦርድ የተሻለ አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ በወረዳው ነዋሪ ከሆኑ ሙስሊሞች መካከል የሚመረጡ አራት(4) ምሁራን፤

## አንቀጽ 69
## የወረዳው መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳው መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ ተጠሪነቱ ለወረዳው ሙስሊም ማህበረሰብ ነው።
2. የወረዳው መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

2.1. በክልሉመጅሊስ ፀድቀው በዞኑ መጅሊስ አማካይነት የተላኩለትን ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎች፣ ደንቦች፣መመሪያዎችና ውሳኔዎች በወረዳው በተዋረድ ባሉ የመጅሊስ አካላት ተግባራዊ ያስደርጋል፣ ይከታተላል፤

2.2. በወረዳው የሚኖረው ሙስሊም ማህበረሰብ ልጆች የእስልምና ሃይማኖት ትምህርትና ሥነ-ምግባር ተምረው ለማደግ የሚያስችሉ መዋዕለ ህፃናት፣ መድረሳዎችና የቁርኣን ት/ቤቶችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ በተጨማሪም የግል ባለ ሃብቶችና በጎ አድራጊዎች ተመሳሳይ ተቋማትን ለማቋቋም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋል፤

2.3. በወረዳው ውስጥ ያሉ የሌላ እምነት ተከታዮችን መብት ባከበረ መልኩና በህገ መንግስቱ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ የእስልምና ሃይማኖት እንዲስፋፋ የዳዕዋ ሥራዎችን የሚሰሩ ተቋማት ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

2.4. በወረዳው የሚኖሩ ሙስሊሞች በግልም ሆነ በጋራ ሃይማኖታቸውን ለመግለጽና ለመተግበር ያላቸው ሕገ-መንግስታዊ መብትና ነፃነት በኃይል ወይም በማንኛውም ህገወጥ መንገድ እንዳይገደብ ይከታተላል፣የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ይሰራል፣ ይታገላል፤

2.5. በእስልምና ሃይማኖት እውቅና የተሰጣቸውን ዘካ፣ ወቅፍ፣ ሰደቃና የመሳሰሉት ማህበራዊ የመረዳጃ ስርዓቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሰራርና ህብረተሰቡን በሚጠቅም መንገድ እንዲፈጸሙ አግባብ ያላቸው የአስተዳደር ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

2.6. የወረዳው ሙስሊም ማህበረሰብ ሃይማኖቱን ለማወቅ የሚረዱ የትምህርት ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

2.7. በወረዳው ያሉ መስጅዶችን ያስተዳድራል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች መስጂዶች በመጅሊሱ በራሱ ወይም በሌሎች በጎ አድራጊዎች ድጋፍ የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ መስጂዶች ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ድጋፍ ያደርጋል፤

2.8. በወረዳው ውስጥ በህግ ከተቋቋሙ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር አግባብነት ያላቸውን ህጎች ባከበረ መልኩና በትብብር መንፈስ የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤

2.9. በስሩ የአስተዳደር ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣ ሥራቸውን ይገመግማል፣ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፤

2.10. የወረዳው ሙስሊም ማህበረሰብ በዞንመጅሊስ ሚዛናዊ ውክልና ማግኘቱን ያረጋግጣል፤

2.11. በየሥራ ዘመኑ ለወረዳው መጅሊስ የተመደበው በጀት ለትክክለኛ ዓላማ መዋሉን የሚከታተል የኦዲትና የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤

2.12. የወረዳውን የኡለማ ምክር ቤት እና የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፤

2.13. የወረዳውን መጅሊስ ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት ያፀድቃል፤

2.14. ከላይ የተጠቀሱትን ኃላፊነቶቹን ለመወጣት ይችል ዘንድ ከዞኑመጅሊስና ከወረዳው ሙስሊሞች የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

# ምዕራፍ አራት
# የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ

## ንዑስ ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

### አንቀጽ 70
### የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ አመሰራረት

1. "የመስጅድ አካባቢ ነዋሪ ሙስሊሞች ምክር ቤት(መጅሊስ)"የአካባቢውንምዕመናንንበመላያቀፈ የመጨረሻው ማህበረሰባዊ የታችኛው የመጅሊስ እርከን ሆኖ በዚህሕገ-መጅሊስየተደራጀሲሆን ህዝበ ሙስሊሙ ሉዓላዊ ስልጣኑን በቀጥታ የሚተገብርበት መዋቅር ነው።
2. በአንቀጽ 2(9) የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ በመላሀገሪቱየሚገኙማናቸውምመስጅድየእርከኑ መጅሊስ ይቋቋምባቸዋል።
3. ለምዕመኑምንምአይነትመስጅድየሌለባቸውአካባቢዎችበአንቀጽ … በተደነገገው አኳኋን "የመስጅድ አልባ ሙስሊም ነዋሪዎች ምክር ቤት(መጅሊስ)" በተመሳሳይ አደረጃጀትና ስልጣን የአካባቢያቸውን ወይም የቀጠናቸውን ስያሜ በመጠሪያነት ተጠቅመው ይመሰርታሉ።

### አንቀጽ 71
### የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ አቋም(መዋቅር)

የአካባቢ መጅሊስ የሚከተለው አቋም ይኖረዋል፡-

1. የመስጅዱን አካባቢ መላ ምዕመናንን ያቀፈ የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ፤
   1.1. የጠቅላላ ጉባኤ አፈ-ሹራ(ሰብሳቢ)
   1.2. የጠቅላላ ጉባኤ ምክትል አፈ-ሹራ(ሰብሳቢ) እና
   1.3. የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ አባል ምዕመናን
2. የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ቋሚ ጉባኤ

2.1. የቋሚ ጉባኤው አፈሹራ(የጠቅላላ ጉባኤው አፈ-ሹራና የመስጅድ ኮሚቴ ሰብሳቢ)

2.2. የቋሚ ጉባኤው ቋሚ ኮሚቴዎች(በሥራ ክፍሎች ልክ የሚደራጁ ተቆጣጣሪ ኮሚቴዎች)

3. የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ፤

3.1. የኮሚቴ ሰብሳቢ፤

3.2. ሙአዚን፤

3.3. ጸሃፊ፤

3.4. የፋይናንስ አስተዳደር ተጠሪ(የሂሳብ ሹም፣ገንዘብ ያዥ፣የንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት) ተጠሪ፤

3.5. የጸጥታ እና ሥነ-ሥርዓት ተጠሪ፤

3.6. የመስጅድ ልማትና እንክብካቤ ተጠሪ፤

3.7. የወጣቶችና የሙያ አደረጃጀት ተጠሪ፤

3.8. የሴቶች አደረጃጀት ተጠሪ፤

3.9. የማህበራዊ ልማት፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትና የአባልነት(Membership) ጉዳይ አስተባባሪ፤

3.10. የደስታና ሀዘን ህብረተሰባዊ ጉዳዮች(የጋብቻና ሰርግ፤ የለቅሶ፣ቀብርና ሰደቃ ጉዳዮች)አስተባባሪ፤

3.11. የገቢ ማበልጸጊያ ሥራዎች ተጠሪ፤

3.12. የታሪክ፣ ቅርስና አካባቢያዊ ሙዚየም ተጠሪ፤

4. የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ንዑስ የኡለማ ጽ/ቤት

4.1. የኢማምና ሙአዚን ቢሮ፤

4.2. ዳዕዋና ተርቢያ ክፍል፤

4.3. የቁርኣትና ሃለቃ ክፍል፤

4.4. የትምህርትና መድረሳ አስተዳደር፤

4.5. ኢስላማዊ ኪነጥበብ፤

4.6. የበዓላት፣የኮንፈረንሶችና የልዩ መርሃግብሮች ማስተባበሪያ፤

4.7. የዲን ኻዲሞች(ኡለማ/አቅሪ/ኡስታዝ/ሙደሪስ፣ኢማም፣ሙአዚን፣ዱዓት/ሰባኪ) ድጋፍ አስተባባሪ፤

## አንቀጽ 72
## የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ሥልጣንና ተግባር

የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

1. በዚህ ሕገ መጅሊስ የተደነገገውን መስፈርት ያሟሉ ሁሉንም የመስጅዱ አካባቢ ሙስሊሞችን በአባልነት በማቀፍ ጠቅላላ ጉባኤ መስርቶ ምዕመናን ዋነኛ የስልጣን ባለቤትነታቸውን ኢስላማዊ መርህን እና ይህንን ሕገ-መጅሊስ አክብረው እንዲተገብሩ ያደርጋል፡፡
2. ከበላይ የመጅሊስ እርከኖችበሚላኩአጀንዳዎችናአባላቱበሚያነሷቸውኢስለማዊናምዕመን-ተኮርርዕሰ-ጉዳዮችላይበመምከርውሳኔያሳልፋል፤ በመዋቅሮቹ በኩል ይተገብራል፡፡

3. በመስጅዳቸውና በአካባቢው መንፈሳዊ፣ልማታዊናአስተዳደራዊተግባሮች በማከናውን የምዕመናንን ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፡፡
4. ሽሪዓዊ በደነገገው አኳኋን ኢስላምንና ሙስሊሞችን ይጠብቃል፤ የዲኑን ሥርዓት ቀኖና እና ኢስላማዊና ምዕመናዊ ደጋግ ትውፊቶችን ያከብራል፤ ያስከብራል፡፡
5. በመስጅዱና በአካባቢው የሚገኙ ሁለገብ ኢስላማዊ እና ሙስሊማዊ ቅርሶችን ከበላይ የመጅሊስ እርከን ጋር በመሆንና አቅጣጫን በመቀበል ይጠብቃል፤
6. ሀገራዊ፣ ኢስላማዊ እና ሙስሊም ተኮር ታሪኮችን ያስተምራል፤ የሀገር እና የዲን ፍቅር በአካባቢው ምዕመናን እንዲዳብር ኢስላማዊ ይሰራል፤
7. ለተማሪዎች መንፈሳዊ የግብረ-ገብ ትምህርቶች በትርፍ ጊዜያቸው እንዲያገኙ ያደርጋል፤
8. ኢስላማዊ ኃብቻዎችን ያበረታታል፣ ያስፈጽማል፤ ትዳር ነክ መንፈሳዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
9. ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ውጭ በሆኑ ሀገራዊ የበጎ ፈቃድ ዘመቻዎችና የእናት ሀገር ጥሪዎች ላይ ከበላይ የመጅሊስ አካላት ጋር በመቀናጀት የምዕመናን ተሳትፎን ያስተባብራል፣ መሰል ሃሳብን የማመንጨት ተነሳሽነት ወስዶ ከባለድርሻ አካላት ጋር በምክክር ይፈጽማል፤
10. የተለያዩ የምዕመናን አደረጃጀቶችን በመዘርጋት ወጣቶች፣ሴቶች፣ታዳጊዎች፣ ሙያተኞች፣ አማተርና ፕሮፌሽናል የኪነ-ጥበብ ሰዎች፣ልዩ ልዩ በጎ ፈቃደኞች፣የአረንጓዴ ልማት አርበኞችና ሌሎችን በዘርፋቸው በማሰባሰብ ለማህበረሰቡ የተቀናጀ የመንፈሳዊና የቁሳዊ ልማት ሥራ እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡
11. ለምዕመናን እስልምናን ማስተማርና ትምህርቱን ማስፋፋት፤
12. ሪሳላው ላልደረሳቸው ህዝቦች እስልምናን ማድረስና የስርጭቱን አድማስ ማስፋት፤
13. የኩፍር ተጋላጮች እንዳይኖሩ መሥራትና የዘካ ፈላጊዎችን በመለየት ለወረዳው መጅሊስ ማሳወቅ፤
14. የእርከኑን መጅሊስ በሚመለከት ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ይከሰሳል፣ ንብረት ያፈራል፣ የገቢ ማስገኛ እና የሃብት ማበልጸጊያ ሥራዎችን ከወረዳው መጅሊስ ጋር ይሰራል፤ ሌሎች በህግ ውጤት የሚያስገኙ ድርጊቶችን ይፈጽማል፡፡
15. ሌሎች ከእርከኑ መጅሊስ የሥራ ባህሪ የሚመነጩ ተዛማጅ ስልጣንና ተግባራትን ይፈጽማል፡፡

## አንቀጽ 73
## የአባልነት መዋጮ

1. እያንዳንዱ ሙስሊም አባወራ ወይም እማወራ ወይም የሙስሊም ቤተሰብ ተጠሪ በአንድ መኖሪያ ቤት የሚኖሩና ትዳር መስርተው ራሳቸውን ባልቻሉ ወይም እድሜያቸው ለአቅመ አዳም ደርሶ ተገቢ ሥራ ወይም በቂ ገቢ በሌላቸው የቤተሰቡን አባላት በመላ በመወከል በሀገራዊ መጅሊስ በሚወሰነው መጠንና የጊዜ ልዩነት ነጠላ ወቅታዊ የአባልነት መዋጮ መክፈል አለበት፡፡

2. በየወቅቱ አባላት የሚሰበሰበው መዋጮ ወደፊት በሚወሰን ምጣኔ (Ratio) ከመስጅዱ የአስተዳደርና የሥራ ማስኬጃ ወጭ የሚተርፈው ለበላይ የበመጅሊስ እርከኖች በጀት መደጎሚያ ይሆን ዘንድ ከወረዳው መጅሊስ መላክ ይኖርበታል፡፡

## ንዑስ ምዕራፍ ሁለት
## የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ

### አንቀጽ 74
### የጠቅላላ ጉባኤው አመሰራረት

1. የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ በተቋቋመበት መስጅድ የመጅሊስ ከፍተኛው የስልጣን አካል ነው፡፡
2. የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ የመስጅዱን አካባቢ ነዋሪ(ጀመዓ) ምእመናን፣ የመስጅዱንኢማሞች፣ሙአዚኖችና ሌሎች ቋሚ ሰራተኞች(Staff members) (በሌላ መስጅድ ካልተመዘገቡ በስተቀር) አባል ለመሆን ፈቅደው መመዝገባቸውና ወቅታዊ መዋጮን መክፈላቸው ሲረጋገጥ የእርከኑ ጠቅላላ ጉባኤ አባል የሚሆኑ ሲሆን የሚከተለውን ዝርዝር መስፈርት ሳይነጣጠል ያሳንዳች ቅድመሁኔታ ማሟላት አለባቸው፡-
   2.1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሙስሊም፤
   2.2. እድሜው 18 አመትና ከዚያ በላይ የሆነ፤
   2.3. በየወቅቱየሚከፈለውንመዋጮ የከፈለ ወይም (አዲስ ገቢ ከሆነ) ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነና ስምምነቱን በጽሁፍ ያረጋገጠ፤
3. መስፈርቱን ማሟላታቸው የተረጋገጠላቸው አባል ምእመናን የአባልነት መዋጮና ተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ከፈጸሙ በኂላ መታወቂያ ከመሰጠቱ ሁለት ሳምንት በፊት ተቃራኒ የሕዝብ አስተያየት ካለመጠበቅ ስም ዝርዝራቸው በግልጽ በሚታይ የመስጅዱ ቅጥር ጊቢመለጠፍ ያለበት ሲሆን መታወቂያ ከመሰጠቱ በፊትም ሆነ በኂላ የተሳሳተ መረጃ የሰጠን ወይም መስፈርቱን ያላሟላ ሆኖ የተገኘን ተመዝጋቢ በጽሁፍ በሚሰጥ መግለጫ ወዲያውኑ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡
4. ዕድሜያቸው ለአስገዳጅ ዕለታዊ ሶላቶች የደረሱ ወይም 15 ዓመት የሞላቸው ወይም 10 ክፍል እና ከዚያ በላይ የሆኑ ታዳጊ ወጣት ሙስሊሞች እድሚያቸው 18 እስኪሞላ ድረስ የመዋጮ ግዴታ ሳይኖርባቸውና ድምጽ የመስጠትና ሃሳብ የመሰንዘር መብትን ብቻ በማስቀረት ለልምድ ልውውጥና ለማብቃት እንዲረዳ በታዳጊ አባልነት ማሳተፍ ይቻላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት እና አራት የተደነገገው ቢኖርም በ1992 በወጣው በተሻሻለው የሪፐብሊኩ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 7(2)፣310፣311፣312 እና 313 በተደነገገው አኳኋን ዕድሚያቸው 14 እና ከዚያ በላይ ሆኗቸው ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ እንዲወጡ ውሳኔ የተሰጠባቸው ወይም ዕድሚያቸው ቢያንስ 16 ሆኗቸው ጋብቻ የፈጸሙ ለአካለ መጠን

እንደደረሱ የሚቆጠሩ በመሆኑ በዚህ ሕገ-መጅሊስ ስለ 18 ዓመት ዕድሜ የተደነገገው ሁሉ ለእንዲህ ዓይነቶቹ ያገለግላል፡፡

## አንቀጽ 75
## የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. የመስጅድ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለመላው አባል ምዕመናን ሆኖ አባላት የመኖሪያ አድራሻ ሲቀይሩ መልቀቃቸውና አዳዲስ አባላት በማናቸውም ጊዜ መግባታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጉባኤው የሥራ ዘመን ገደብ አልባና ያልተወሰነ ሲሆን አፈጉራውና አመራሮቹ የሥራ ዘመን ግን አምስት ኣመት ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው በወረዳ መጅሊስ የሚወጡ እቅዶችና ትዕዛዞችን በመስጅዳቸው ተፈጻሚ ከማድረግ በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራትን ያከናውናሉ፡-
   - 2.1. በዚህ ሕገ -መጅሊስ ለእርከኑ መጅሊስ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ይፈጽማል፤
   - 2.2. የበላይ የመጅሊስ እርከኖች በስልጣን ክልላቸው ለእርከኑ መጅሊስ የሚስተላልፉት ትዕዛዝና መመሪያ መፈጸሙን ይቆጣጠራል፤
   - 2.3. የሥራ ክፍሎችን ዕቅድና በጀት በቋሚ ጉባኤው ሲቀርብለት ገምግሞ ያተድቃል ውሳኔ ሳልፋል፤
   - 2.4. የሥራ ክፍሎችን የዕቅድና የጀት አፈጻጸም በቋሚ ጉባኤው ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል ሪፖርት እየሰማ ይገመግማል፣ ተገቢውን ውሳኔያሳልፋል፡፡
   - 2.5. የበላይ መጅሊስ መመሪያዎችን ባልጣሰ መልኩ በመስጅዱ አስተዳደር ኮሚቴ ምርጫ፣ በኢማም አሿሿምና በሙአዚን ምደባ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ሰጭ አካላት ናቸው፡፡
   - 2.6. ቋሚ ጉባኤው በውክልናና በቀጥታ ስልጣኑ የተገበራቸውን ውሳኔዎችንና አፈጻጸሞችን በመገምገም ያጸድቃል፣ይሽራል ወይም ያሻሽላል፡፡
   - 2.7. የቋሚ ጉባኤ አባላትን ይመርጣል፡፡
   - 2.8. በቋሚ ጉባኤው ተመርጠው ወደ በየትኛውም የበላይ የመጅሊስ እርከን በደረሱ እንደራሴዎችላይእምነትሲያጣበዚህሕገመጅሊስበተደነገገውሥነሥርዓትመሰረትውክልናቸውንያነሳል፤ቋሚ ጉባኤው ሌላ እንዲተካም ያስደርጋል፡፡
   - 2.9. በቋሚ ጉባኤው የታገደን ኢማምና ሌላ አመራር ጉዳይ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
   - 2.10. ሌሎች ከሥራው ባህሪ የሚመነጩ ስልጣንና ተግባራትን ያከናውናል፡፡
3. በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጠው አፈ-ጉራ የእርከኑ መጅሊስ ሰብሳቢ ሲሆን የቋሚ ጉባኤውና የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ መሪ ነው፡፡

## አንቀጽ 76
## የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች

1. መደበኛ የመስጅድ ጠቅላላ ጉባኤ በየዓመቱ አንዴ በወርሃ ….. ይሰበሰባል፡፡
2. እጅግ ቢዘገይ ከአራት ወር በላይ መዋጮ ያላቋረጡ የጉባኤው አባላት ዝርዝር ውስጥ ቢያንስ ግማሹ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

3. የስብሰባ አጀንዳዎች በቋሚ ጉባኤው ቀድመው የሚዘጋጁ ሲሆን የተመረጠ እንደራሴን ለመመለስ (Recall) ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡
4. የተመረጠ እንደራሴን ለመመለስ (Recall) የሚደረግ ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ የሚሆነው እጅግ ቢዘገይ ከአራት ወር በላይ መዋጮ ያላቋረጡ የጉባኤው አባላት ዝርዝር ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሶስተኛው በስብሰባው ከተገኙ ሆኖ በሶስት አራተኛ ድምጽ ካልተደገፈ በስተቀር የሚጸና ውሳኔ ማሳለፍ አይቻልም፡፡
5. በማናቸውም ስብሰባዎች እኩል ድምጽ ሲያጋጥም የአፈ-ጉባኤው ድምጽ መለያ(መቁረጫ) ይሆናል፡፡
6. ስለሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤ ድንገተኛ ስብሰባ ምክንያቶች የተደነገጉት እንደ አስፈላጊነቱ ለመስጅድ ጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያገለግሉ ሆኖ ድንገተኛ ስብሰባው እንዲጠራ በቋሚ ጉባኤው በኩል ማቅረብ የሚችሉት ፡-
   6.1. ጥያቄው በቀረበበት ወቅት መዋጮን ያላቋረጡ አንድ አስረኛ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት፤ ወይም
   6.2. ጥያቄው በቀረበበት ወቅት መዋጮን ያላቋረጡ አንድ ሶስተኛ የቋሚ ጉባኤ አባላት፤
   6.3. ቋሚ ጉባኤው በመደበኛ ወይም በድንገተኛ ስብሰባው በአብላጫ ድምጽ ሲወስን፤
   6.4. የመስጅድ ኮሚቴ በአብላጫ ድምጽ ሲወስን በኢማሙ በኩል ወይም በኡለማ ንዑስ ጽ/ቤት ዋና ዓሊም በኩል በቀጥታ ቋሚ ጉባኤውን ማስፈቀድ ሳያስፈልግ ስብሰባውን ይጠራል፡፡

## አንቀጽ 77
## እምነት የታጣበትን እንደራሴ የመመለስ (Recall) ልዩ ሥነ ሥርዓት

1. በየትኛውም የመጅሊስ እርከን በምርጫ ሰንሰለት የደረሰን ተመራጭ እንደራሴን ከመመለስና እምነት ታጥቶበታል ከማለት ጋር በተያያዘ ውሳኔ ለማሳለፍ የመጣበትንጀመዓየመስጅድ ጠቅላላጉባኤውሳኔየሚያስፈልግ ሲሆንጉዳዩንየስብሰባአጀንዳአድርጎ በአንቀጽ 74 መሰረት ውሳኔ ለማሳለፍ፡-
   1.1. የቋሚ ጉባኤውሲሶአባላትለአጀንዳውየድጋፍፊርማለአፈ-ጉባኤው በጽሁፍ ሲያቀርቡ ወይም
   1.2. ጥያቄው ሲቀርብ መዋጮ ያላቋረጡ የጠቅላላ ጉባኤው አንድ ሶስተኛ አባላት በጽሁፍ ሲጠይቁ ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አቤቱታየቀረበባቸውእንደራሴበምዕመኑዝርዝርየጽሁፍቅሬታዎችላይተገቢውንአስተያየተትናምላሽእን ዲሰጡመደረግ አለበት፡፡

## ንዑስ-ምዕራፍ ሶስት
## የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ቋሚ ጉባኤ

## አንቀጽ 78
## የቋሚ ጉባኤው አመሰራረት

1. የመስጅድ አካባቢ መጅሊስ ቋሚ የጉባኤ አባላት ምርጫ የማያስፈልጋቸውን ተሰያሚ ኢማሞችን፣ የኡለማ ንዑስ ጽ/ቤት አባላትንና ኮሚቴውን ጨምሮ በመስጅዱ ጠቅላላ ጉባኤ

አባላት ብዛት ላይ የተመሰረተ ሆኖ በጠቅላላ ጉባኤው በአብላጫ ድምጽ የሚመረጡ ቢያንስ ሰላሳ ሶስት(33) ቢበዛ ሀምሳ አምስት(55) አባላት ያቀፈ ስብስብ ነው።

2. በቀጥታ ከሚሳተፉት ውጭ ለመስጅድ ቋሚ ጉባኤ አባልነት የሚመረጠው የሚከተለውን መስፈርት ማሟላት አለበት፡-
   2.1. የእርከኑ ጠቅላላ ጉባኤ የሆነ ኢትዮጵያዊሙስሊም፤
   2.2. እድሜውከ18 ዓመትያላነሰ እናከ65 ያልበለጠ፤
   2.3. ዘወትርበመስጅድዒባዳየሚገኝናለምርጫየቀረበበትንየሥራቋንቋየሚረዳ፤
   2.4. ለኢስላምናለሙስሊሞችታማኝየሆነና ለሙስሊሞች አንድነት ሊሠራ ፈቃደኛ የሆነ፤
   2.5. በህዝበሙስሊሙዘንድበስነምግባሩናማህበረሰቡንበማገልገልጥሩስምያለው፤
   2.6. በሚመረጥበትየምርጫክልል(የመስጅድ አካባቢ) ላለፉትስድስትወራት ያለማቋረጥነዋሪየሆነ (ለትምህርትናለመጅሊስሥራአካባቢያቸውንየለቀቁትን ከዕጩነት አያስወግድም)፤
   2.7. ተገቢውንየአባልነትመዋጮ ያለማቋረጥ የከፈለ፤
   2.8. ጤነኛናየተሟላአካላዊብቃትያለውሆኖበሁለንተናዊእውቀት፣ አቅምናክህሎትየዳበረናቢያንስማንበብናመፃፍየሚችል፤
   2.9. ከኢስላማዊግለሰባዊምሁራዊምርምሮች(ኢጅቲሀድ) በሚመነጩጤናማየአስተሳሰብልዩነቶች (ኺላፎች) ላይከመቻቻልመርሆተቃራኒበሆኑድርጊቶችያልተሳተፈ፤
   2.10. ከብዙኃኑምእመናንመስጅድናጀመዓያለተገቢምክንያትያልተነጠለናበተክፊር/በተሽሪክያልተሳተፈ፤
   2.11. ህግናሥርዓትየሚያከብርናለሀገሪቱብሄራዊጥቅሞችናለዜጎችሁለንተናዊደህንነትየሚቆረቆር፤
   2.12. በየትኛውምመንግስታዊእርከን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካተሹዋሚያልሆነ ወይም ሹመቱን ለመልቀቅ የወሰነ፤
   2.13. ኡማውንበቅንነት በነጻ ለማገልገልፈቃደኛየሆነናቃለመሃላየሚገባ።
   2.14. የጠቅላላጉባኤውአባላትውስጥቢያንስየአስርበመቶአባልምእመናንየእጩነትየድጋፍፊርማያገኘወይ ምየጉባኤውአባላትበአብላጫድምፅለእጩነትየመለመሉትመሆንአለበት።

## አንቀጽ 79
## የቋሚ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. የቋሚ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር እንዲሁም ከጠቅላላ ጉባኤው ጋር ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት በዚህ ሕገ-መጅሊስ ለሀገራዊው የሥራ አመራር ቦርድ የተደነገጉት የቁጥጥር ሥራዎች እንደ አግባብነቱ የሚያገለግሉ ሆኖ የሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤው በሥራ አመራር ቦርዱ ላይ ያለው ስልጣንና ግኙኙነት እንደ አግባብነቱ ለቋሚ ጉባኤውም ያገለግላል።
2. በንዑስ አንቀጽ አንድ እና በሌሎች የዚሕ ሕገ-መጅሊስ ድንጋጌዎች ለቋሚ ጉባኤው የተሰጡት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት በተለይ ይኖሩታል፡-
   2.1. የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴዎችንና የኡለማ ንዑስ ጽ/ቤቱን ሥራ ይገመግማል፣ይቆጣጠራል፤
   2.2. የዘካ ተቀባዮችን ዝርዝር በማውጣት ለወረዳ መጅሊስ ይልካል፤

2.3. በመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ የሥራ ክፍሎች የብዛት መጠን ልክ በቋሚ ኮሚቴ በመደራጀት የየተቋቋሙበትን የሥራ ዘርፍ ይቆጣጠራሉ፤

2.4. የሥራአፈጻጸሙን ሪፖርት ለጠቅላላው ጉባኤያቀርባል፤

2.5. ከኢማም እና በመስጊዱ ከሚያቀሩ ኡለማ ውጭ የሆኑትን የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ አባላትን ተገቢ ምክንያት ሲኖረው በሙሉ ወይም በከፊል በማንሳት በሌላ ተክቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል፤

2.6. በኢማሞችና በመስጊዱ ከሚያቀሩ ዑለማ ላይ አቤቱታና ቅሬታ በጽሁፍ በተገቢው ሥነሥርዓት ሲቀርብለትና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው አግዶ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

2.7. እምነት የታጣበትን እንደራሴ በሚመለከት ተገቢውን ሥነሥርዓት ተከትሎ የግምገማ ሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳብ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፤

2.8. በአካባቢያዊናሀገራዊኢስላማዊጉዳዮችናምዕመኑንበሚመለከተአጀንዳዎችላይበመምከርምልከታቸውንናአቋማቸውን ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል፤ለበላይመጅሊስ ይልካል፤

2.9. የመስጅዱን ጀመዓ ወይም ምዕመንወክሎ ወደ ወረዳ መጅሊስ የሚላከውንእንደራሴመርጦ በመላክ ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያደርጋል፤

2.10. በመስጅድአስተዳደርኮሚቴዎችን፣ኢማሞችናሙአዚኖችንላይ ቅሬታይሰማል፤

2.11. በመስጅዳቸው አካባቢ የተሰሩ ዲናዊ ሥራዎችንይገመግማል፣ይከታተላል፣እርምጃይወስዳል፤

2.12. በመስጅዱዙሪያያሉትንልማቶችናየገቢማስገኛፕሮጀክቶችከበላይየመጅሊስአርከኖችጋርበመቀናጀት መመሪያይሰጣል፣ንብረቶችንናመስጅዱንአስተዳደርይመረምራል፤

2.13. የጠቅላላ ጉባኤውን ድንገተኛ ስብሰባ ያስተባብራል በመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ በኩል ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤ ተሰብሳቢ አባላትን ይጠራል፤

2.14. በጠቅላላ ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ስልጣንና ተግባራት ይከውናል።

## አንቀጽ 80
## የቋሚ ጉባኤው ስብሰባ

1. የቋሚ ጉባኤው የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ነው።
2. ቋሚ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባውን በየሩብ ዓመቱ(በየሶስት ወሩ) ያደርጋል።
3. በመስጅድ ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ አምስት በመቶ አባላት ፊርማ የተደገፈ አጀንዳ ለመስጅድ ኮሚቴው ከስብሰባው በፊት ሲቀርብ ቀጥሎ በሚደረገው መደበኛ የቋሚ ጉባኤው የመወያያ አጀንዳ ይሆናል።
4. በሌሎች ድንጋጌዎች ስለመደበኛ የስብሰባ ሥርዓቶች የተገለጹት ለቋሚ ጉባኤውም ያገለግላሉ።

## ንዑስ-ምዕራፍ አራት
## የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴና የኡለማ ንዑስ ጽ/ቤት

## አንቀጽ 81
## የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ

1. የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴ የመስጂድ አካባቢ መጅሊስ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሲሆን ተጠሪነታቸው ለመስጅዱ አካባቢ ሙስሊም ማህበረሰብ ወይም ለጠቅላላ ጉባኤው ነው፡፡
2. የአካባቢ መስጂድ ኮሚቴ አባላት ስብጥር የተለያየ ሲሆን መስጂዱ ካለበት አካባቢ ከሚኖሩ ሙስሊሞች የሚመረጡ ሰባት አባላት የሚኖሩት ሆኖ ከመካከላቸው ሰብሳቢ(የጉባኤው አፈ-ሹራ)፣ ፀሐፊ፣ የተለያዩ የሥራ ክፍል ተጠሪዎችን የሚመርጡ ሲሆን የመስጂዱ ዒማምና ሙአዚን ያለምርጫ የኮሚቴው አባል ይሆናሉ፡፡
3. የአካባቢ መስጂድ አስተዳደር ኮሚቴ በአንቀጽ 70(3) ስር የተዘረዘሩትን ለሥራው የሚረዱ የሥራ ዘርፎችን ያቋቁማል፤ በቋሚ ጉባኤው ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፤ እንዲሁም
   3.1. በክልሉ መጅሊስ ፀድቀው በዞንና በወረዳው መጅሊስ አማካይነት የተላኩለትን እቅዶች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች በኮሚቴውና በአካባቢው ሙስሊም ማህበረሰብ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤
   3.2. የአካባቢው ሙስሊም ማህበረሰብ ልጆች የእስልምና ሃይማኖት ትምህርትና ሥነ-ምግባር የሚማሩባቸው መዋዕለ ህፃናት፣ መድረሳዎችና የቁርኣን ት/ቤቶች እንዲጠናከሩ ጥረት ያደርጋል፤
   3.3. በበአካባቢው የሚኖሩ ሙስሊሞች በግልም ሆነ በጋራ ሃይማኖታቸውን ለመግለጽና ለመተግበር ያላቸው ህገ መንግስታዊ መብትና ነፃነት በኃይል ወይም በማንኛውም ህገወጥ መንገድ እንዳይገደብ ይከታተላል፣ ይታገላል፤
   3.4. በእስልምና ሃይማኖት እውቅና የተሰጣቸው ዘካ፣ ወቅፍ፣ ሰደቃና የመሳሰሉት ማህበራዊ የመረዳጃ ስርዓቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሰራር ለአካባቢው ሙስሊሞች በሚጠቅም መንገድ እንዲፈጸሙ ያደርጋል፤
   3.5. መስጅዶችን ያስተዳድራሉ፣ያስተባብራሉ፣ቋሚ ሰራተኞችን ይቀጥራሉ፣ያስተዳድራሉ፣ ያሰናብታሉ፤
   3.6. በአካባቢው መስጂድ የዳዕዋ ሥራ እንዲስፋፋ ጥረት ያደርጋሉ፣ ያስተባብራሉ፤
   3.7. ለአካባቢው ሙስሊሞች መታወቂያ ይሰጣሉ፣ የትብብርና የድጋፍ ደብዳቤዎችን ይጽፋሉ፤
   3.8. የመቃብር ስፍራ አያያዝና አጠቃቀምን ይከታተላሉ፣ እንክብካቤ ያደርጋሉ፣ ያስተዳድራሉ፤
   3.9. ከአካባቢው ሙስሊሞችና ከበጎ አድራጊዎች መዋጮና ድጋፍ ያሰባስባሉ፤
   3.10. የአካባቢው ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል፣ ሃይማኖታዊ በዓላት በአካባቢው ሙስሊሞች በጋራ እንዲከበሩ ያስተባብራሉ፤
   3.11. በአካባቢው ያሉ ኢስላማዊ ቅርሶችና ባህል እንዲጠበቁ ጥረት ያደርጋሉ፤
   3.12. ከወረዳው መጅሊስና ከአካባቢው ሙስሊሞች የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡
   3.13. እስካሁን በግለሰብና በድርጅቶች የተሰሩና የሚተዳደሩ እንዲሁም ወደፊት በግለሰብ በሚቋቋሙ በወቅፍነትና በግለሰብ የተያዙ መስጊዶች በአስተዳደራቸው በኩል ይቀጥላሉ፤ የአካባቢው ማህበረሰብ

ከመስጊድ ማግኘት ያለበትን አገልግሎት ከናዚሮቹና ከመጅሊሱ ጋር በመተባበር አስፈላጊው አቅጣጫ ይወሰዳል፡፡

## አንቀጽ 82
## የመስጅድ ኡለማ ንዑስ ጽህፈት ቤት

1. በመስጅድ ደረጃ የሀገራዊው ኡለማ ምክር ቤት ሰንሰለት አካል የሆነ በዋና ዓሊም የሚመራ የኡለማ ንዑስ ጽ/ቤት በመስጅዱ ኢማምና የዒልም አስተማሪዎች የሚደራጅ ሆኖ በአንቀጽ68(4) በተደነገገው አኳኋን በስሩ በስሩ የሚከተሉትን የሥራ ክፍሎች ያደራጃል፡-
   1.1. የኢማምና ሙአዚን ቢሮ፤
   1.2. ዳዕዋና ተርቢያ ክፍል፤
   1.3. የቁርዓትና ሃለቃ ክፍል፤
   1.4. የትምህርትና መድረሳ አስተዳደር፤
   1.5. ኢስላማዊ ኪነጥበብ፤
   1.6. የበዓላት፣የኮንፈረንሶችና የልዩ መርሃግብሮች ማስተባበሪያ፤
   1.7. የዲን ኻዲሞች(ኡለማ/አቅሪ/ኡስታዝ/ሙደሪስ፣ኢማም፣ሙአዚን፣ዱዓት/ሰባኪ) ድጋፍ አስተባባሪ፤
2. የጠቅላላ እና የቋሚ ጉባኤዎች ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ንዑስ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ሕገ-መጅሊስ ለመስጅድ አካባቢ መጅሊስ የተሰጡ ዒልምና ኡለማ ነክ ስልጣንና ተግባራትን በተለይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ በተዘረዘሩት የሥራ ክፍሎች ውስጥ የሚካተቱትን በመለየት የሚፈጽም ሲሆን በጠቅላላና በቋሚ ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትንም ያከናውናል፡፡
3. በዚሕ ሕገ-መጅሊስ ስለ ኡለማ ጽ/ቤቶች የተደነገጉት ሌሎች ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለንዑስ ኡለማ ጽ/ቤቱም ያገለግላሉ፡፡
4. የመስጅዱን አካባቢ በመወከል ወደ ወረዳ ኡለማ ምክር ቤት የሚላኩትን ዓሊሞች የሚወስነው ጠቅላላ ጉባኤው ወደራሱ ካልወሰደው በስተቀር የቋሚ ጉባኤው ስልጣን ነው፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## የኡለማ እና የዳዕዋ ክልላዊ መዋቅር

## አንቀጽ 83
## የኡለማ ምክር ቤት መዋቅር

1. ዋና ሙፍቲውን በአባልነት በያዘው በሀገራዊው የዑለማ ምክር ቤት ስር በክልላዊ ተዋረድ የሚከቱለትን የዑለማ ምክር ቤት መዋቅሮች አሉ፡-
   1.1. በሙፍቲ የሚመራ የክልል ኡለማ ምክር ቤት፤
   1.2. በኡለማ ሊቀመንበር የሚመራ የዞን ኡለማ ማዕከል፤
   1.3. በኡለማ ሰብሳቢ የሚመራ የወረዳ የዑለማ ጽ/ቤት፤
   1.4. በዋና ዓሊም የሚመራ የመስጅድድ ኡለማ ንዑስ ጽ/ቤትጽ/ቤት፤

2. በእየእርከኑ የሚገኝ የኡለማ ተቋም የውስጥ ነጻነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የተዋረድ የሥራ ግንኙነት ይኖራቸዋል፡፡ ከላይ ወደ ታች በመዋቅራቸው ስፋት ልክ የስልጣን እርከኑም ይገደባል፡፡

## አንቀጽ 84
## የኡለማ ምክር ቤት አስፈጻሚ ተቋማት

1. በሀገራዊው ኡለማ ምክር ቤት በዋና ሙፍቲው የሚመራ የሙፍቲዎችጉባኤ የያዛቸውን ስልጣኖች በክልል ደረጃ በየመዋቅሩ የሚተገብርና የሀገራዊውን ፈትዋዎችና ውሳኔዎች የሚያስፈጽም ተቋም በሁሉም እርከን ይዋቀራል፡፡
2. የሚከተሉት የኡለማ ጽ/ቤት አደረጃጀቶች ተዋቅረዋል፡-
   2.1. በክልል ደረጃ በሙፍቲ የሚመራ የሙፍቲ ጽ/ቤት፤
   2.2. በዞን ደረጃ በዑለማ ሊቀመንበር የሚመራ የኡለማ ማዕከል፤
   2.3. በወረዳ ደረጃ በዑለማ ሰብሳቢ የሚመራ ጽ/ቤት፤
   2.4. በመስጅድ ደረጃበዋና ዓሊም የሚመራ የመስጅድ ኡለማ ንዑስ ጽ/ቤትይደራጃል፡፡

# ክፍል ፮ ስድስት
# የመጅሊስ ሥርዓተ-ምርጫ

## አንቀጽ 85
## የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ

1. የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከመስጅድ እስከ ሀገራዊው መጅሊስ ድረስ በተዋረድ በተዋቀረው የዑለማ ምክር ቤት አቅራቢነት በየእርከኑ ባሉት ጠቅላላ ጉባኤዎች አጽዳቂነት ይሰየማል፡፡
2. በሁሉም የመጅሊስ እርከን በመስጅድ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልልና በሀገራዊ ደረጃ የሚቋቋመው የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የላቀ ስነምግባር ካላቸው የተለያዩ አካላት የሚሰባጠር ሆኖ ከወጣት፣ ከሽማግሌ፣ከምሁራንና ከዓሊሞች የተውጣጣ ሰባት አባላት ያሉት ሆኖ ከእነዚህ ውስጥ ሶስቱ ሴቶች መሆን አለባቸው፡፡
3. በመስጊድ ደረጃ ለሚደረግ ምርጫ የምርጫ አስፈጻሚዎችን የመስጊዱ ኢማም፣ በመስጊዱ የሚያቀሩ አንድ ዓሊም፣በመስጊዱ የገንዘብ መዋጮ በማድረግ የሚታወቁ አንድ ግለሰብ፣ ከመስጂዱ ጀመዓ አንድ ሽማግሌና አንድ ወጣት በአጠቃላይ አምስቱ በኢማሙ መሪነት በጋራ ተማክረው ሕዝቡ ዘንድ ተቀባነት ያገኛሉ የሚሏቸውን ፩፬ ሰዎችን እጩ አድርገው ለመስጅዱ ጀመዓ በማቅረብ በድምጽ ብልጫ ሰባት አባላትን ያስመርጣሉ፡፡
4. የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የመንግስት ሹመኛ መሆን የለባቸውም፡፡

5. የምርጫ አስፈጻሚ አባላት  ሀላፊነታቸውን ለአላህ፣ለህሊናቸውና ለህዝባቸው ታማኝ ሆነው ከወገንተኝነት ነጻ ሆነው በገለልተኝነት ተግባራቸውን የመወጣት ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

### አንቀጽ 86
### የምርጫ ጣቢያዎች/ማዕከሎች

1. የምርጫ ማዕከሎች ወይም ጣቢያዎች መስጅዶች ሲሆኑ  በወረዳው መስጅድ ከሌለ በቀር ሁልጊዜ ምርጫ የሚደረገው በመስጊድ ቅጥር ግቢ በሚዘጋጅ ቦታ ዉስጥ ብቻ ነው፡፡
2. መስጅድ በሌለበት ወረዳ ከምርጫው በፊት ጉዳዩን ከህዝበ ሙስሊሙና ከመንግሥት አካል ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት መሞከር ያለበት ሲሆን ከምርጫ በፊት የመስጊድ ስፍራ ከተገኘና በስፍራው ላይ ድንኳን አልያም ጊዜያዊ ዳስ በመሥራት የአካባቢው ሙስሊም ነዋሪዎች በወረዳው የነዋሪነት መታወቂያቸው እየተመዘገቡ ምርጫ ይደረጋል፡፡
3. ምንም መስጅድ በሌለበት ወረዳ ከምርጫው በፊት የመስጊድ ስፍራ ማግኘት ካልተቻለ ለአንድ የምርጫ ጊዜ ብቻ እንዲያገለግል በወረዳው ባለ የቁርኣን ት/ቤት፣ዛውያ ወይም መድረሳ ወይም ኢስላማዊ ተቋም ይደረጋል፡፡
4. በወረዳው የቁርኣን ት/ቤት ወይም መድረሳ ወይንም ሌላ ኢስላማዊ ተቋም ከሌለ የዚያ ወረዳ ምርጫ እንዲዘገይ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ምርጫው ከተደረገ በኋላ የሚመረጡት የዞኑ፣ የክልልና የፌደራል መጅሊስ አመራሮች ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመነጋገር ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ በወረዳው መስጊድ ስፍራ እንዲኖር በማድረግ ምርጫ የሚደረግ ሲሆን ይህ የማይሳከበት ሁኔታ ከተፈጠረ የአከባቢው ሙስሊሞች ቀድሞ በተመረጠና ይፋ በተደረገ በአውላላ ሜዳ፣በዛፍ ስር አልያም በተመረጠ ሌላ አመች ሥፍራ ይደረጋል፡፡

### አንቀጽ 87
### የመራጭነት መስፈርት

1. ማንኛውም 18 ዓመት የሞላው ወይም የሞላት ሙስሊም በአባልነት በተመዘገበት መስጅድ ምርጫ የመሳተፍ መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሙስሊም በመኖሪያው አካባቢ በሚገኝና በአባልነት ተመዝግቦ መታወቂያ ባወጣበትና መዋጮ ያለማቋረጥ በከፈለበትመስጅድ የመምረጥና መስፈርቱን አሟልቶየመመረጥ መብት አለው፡፡
3. የመኖሪያ አከባቢውን የሚቀይር ግለሰብ አካባቢውን በቀየረ በሁለት ወር ዉስጥ ከቀድሞ መስጂዱ የወሰደውን መታወቂያ ካርድ በመመለስ ከአዲሱ ሰፈር መስጂድ የአባልነት መታወቂያ መውሰድ ይገባዋል፡፡
4. በማንኛውም መስጊድ መስገድና በኢስላማዊ ሂደት መሳተፍ መብት ቢሆንም ከአንድ በላይ በሆነ መስጂድ በአባልነት መመዝገብ፣የመታወቂያ ካርድ ማውጣት፣በምርጫ በመራጭነትም ሆነ በመተመራጭነት መሳተፍ ፈጽሞ አይቻልም፡፡
5. መዋጮ የመክፈል አቅም እንደሌለው አሳማኝ ምክንያት ያቀረበ ሙስሊም በመዋጮ አለመክፈል ብቻ በምርጫ የመሳተፍ መብቱን አይነፈግም፡፡

## አንቀጽ 88
## የእጩዎች ምዝገባ

1. የእጩዎች ምዝገባ ከምርጫው እለት አንድ ወር ቀደም ብሎ ይጀመራል። ከምርጫ ቀን ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ ይጠናቀቃል።
2. አንድ ሰው ራሱን አልያም መስፈርቱን የሚያሟላ ሌላን ሰው በእጩነት ማስመዝገብ ይችላል።
3. አንድ ሰው እጩ ሆኖ ሲመዘገብ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎችን ስለማሟላቱ የማጣራት ሀላፊነት የመዝጋቢዎቹ ሀላፊነት ነው።
4. አንድ ሰው ራሱን አልያም ሌላን ሰው እጩ ሆኖ አድርጎ ማቅረብ የሚችለው ቢያንስ ከመስጊዱ የተመዘገቡ የጀመዓ አባላት የሠላሳ ሰዎችን የድጋፍ ፊርሚያ ሲያቀርብ ነው።
5. በእጩነት የተመዘገው ሰው ስሙ በጥቁር መዝገብ ስለመመዝገቡ የምርጫው አስፈጻሚ ኮሚቴዎች አጣርተው ከምርጫ አንድ ሳምንት በፊት ይፋ ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 89
## የእጩዎች መስፈርት

1. ለመስጅድ ቋሚ ጉባኤ አባልነት የሚወዳደረውበአንቀጽ 77(2) የተደነገገውን ያሟላ ብቻ ነው።
2. ለመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴነት በሚቀርቡ ዕጩዎች መሟላት ያለባቸው አስገዳጅ መስፈርቶች፡-
   2.1. በመስጊዱ አከባቢ የሚኖርና ቢያንስ በመስጊዱ በጀመዓነት ለአንድ ዓመት የቆየ፤
   2.2. በሃይማኖታዊ አልያም መደበኛ የትምህርት ዝግጅት በከተሞች ቢያንስ 10ኛ ክፍል የጨረሰ። በገጠር አከባቢ ደግሞ መገኘት እስከቻለ ድረስ ቢያንስ አንደኛ ደረጃ ት/ት የተማረና ሀይማኖቱን የሚተገብር፤
   2.3. በበጎ ፈቃደኝነት ለማገልገል ዝግጁ እና የራሱ የሆነ የገቢ ምንጭ ያለዉ፤
   2.4. በየትኛዉም የፖለቲካ ፓርቲ ባለ ስልጣን ያልሆነ ወይም መንግስታዊ የፖለቲካ ሹመት የሌለው፤
   2.5. እድሜው 25 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፤
   2.6. ያለማቋረጥ የአባልነት መዋጮ የከፈለ፤
   2.7. ኢስላማዊ ስነምግባር ያለው።
3. ለወረዳ መጅሊስ መሪነት በእጩነት በሚቀርቡት ዕጩዎች መሟላት ያለባቸው አስገዳጅ መስፈርቶች፡-
   3.1. በወረዳው ዉስጥ ያለ መስጂድ አባልነት ያለዉ፤
   3.2. ዕድሜው 25 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፤
   3.3. በየትኛዉም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም መንግስታዊ የፖለቲካ ሹመኛ ያልሆነ፤
   3.4. በሃይማኖታዊ አልያም በመደበኛ ትምህርት ቢያንስ ዲፕሎማ ወይም ተመጣጣኝ የት/ት ደረጃ ያለዉ፤
   3.5. የጀመዓሰላት ከሚሰግድበት መስጊድ ወይም በአከባቢው ካሉ ሁለት ታወቂ ዓሊሞች የዕጩነት የድጋፍ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፤

3.6. በመንግስት፣በሃይማኖታዊ አልያም በግል ተቋም ስለማገልገሉ ቢያንስ የአንድ ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

3.7. የወረዳውን የሥራ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ የሚችል፡፡

4. ለዞን መጅሊስ አመራርነት እጩ ሆኖ በሚቀርቡት ዕጩዎች መሟላት ያለባቸው አስገዳጅ መስፈርቶች፡-

4.1. በዞኑ በቋሚነት ነዋሪ የሆነ፤

4.2. የዕጩነት ከሁለት መስጊዶች፣ ከሁለት ታወቂ ዓሊሞች አልያም ከሁለት ኢስላማዊ ድርጅቶች ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፤

4.3. በየትኛዉም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም መንግስታዊ የፖለቲካ ሹመኛ ያልሆነ፤

4.4. እድሜው 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነው፤

4.5. የትምህርት ዝግጅቱ በሃይማኖታዊ አልያም በመደበኛ ትምህርት ቢያንስ ዲፕሎማ ወይም ተመጣጣኝ ያለው፤

4.6. በመንግስታዊ፣በሃይማኖታዊ አልያም በግል ድርጅት በሃላፊነት ለ 2ዓመት አልያም በሠራተኝነት ለ4 ዓመት የሠራና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

4.7. በዞኑ የሥራ ቋንቋ ቢያንስ መናገር ከተቻለም ማንበብና መጻፍ የሚችል፡፡

5. ለክልል መጅሊስ በእጩነት በሚቀርቡት ዕጩዎች ማሟላት ያለባቸው አስገዳጅ መስፈርቶች፡-

5.1. በክልሉነዋሪ የሆነ፤

5.2. የዕጩነት ከሁለት መስጊዶች ወይም ከሁለት ታወቂ ዓሊሞች አልያም ከሁለት ኢስላማዊ ድርጅቶች ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፤

5.3. ዕድሜው 35 እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

5.4. በሃይማኖታዊ አልያም በመደበኛ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ ያለውና በሀላፊነት ለሦስት አልያም ከሀላፊነት ዉጭ ለአምስት ዓመት የሰራ አልያም የማስተርስ ዲግሪ ያለውና የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

5.5. የክልሉን የሥራ ቋንቋ መናገር፣ መጻፍና ማንበብ የሚችል፡፡

**አንቀጽ 90**
**ከዕጩነት የሚያቅቡምክንያቶች**

1. ሙስሊም ያልሆነ ወይም እስልምናን የተወ፤
2. የምርጫ አስፈጻሚ ቦርድ አባልነት የተመረጠ፤፡
3. ምርጫው በሚደረግበት መስጊድ በጀመዓ አባልነት ተመዝግቦ የአባልነት ካርድ ያልወሰደና ተገቢውን መዋጮ ያልከፈለ፤
4. በስነምግባር ጉድለት ከየትኛውም የመጅሊስ እርከን በማስረጃ ተረጋግጦበት የተባረረና የመጨረሻውን ዉሳኔ ያገኘ ግለሰብ ቢያንስ ለሁለት የምርጫ ጊዜያት እጩ ሆኖ መቅረብ አይችልም፤
5. በፍርድ ቤት በሕዝባዊ ምርጫዎች እንዳይሳተፍ እግድ የተላለፈበት፤

6. የምርጫ ሂደትን በማወክ ጥፋተኛ ሆኖ ስሙ በጥቁር መዝገብ ያረፈና የቅጣት ጊዜውንያልጨረሰ።

## አንቀጽ 91
## የምርጫ ቅስቀሳ

1. ማንኛውም ሰው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው በማናቸውም ሁናቴ በመስጊድ ዉስጥ የምረጡኝ ቅስቀሳ ማድረግ የተከለከለ ነው።
2. የመጅሊስ አመራር አባላት፣ የመስጊድ ኢማሞች፣ዓሊሞች፣ዳኢዎች፣ ሙአዚኖች፣የመስጊድ ኮሚቴዎች አልያም ሌላ በማንኛውም ሀላፊነት ያለ ሰው ከቀረቡት እጩዎች መካከል የትኛውንም እጩ እንዲመርጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መናገር፣ለይቶ ለብቻ ማስተዋወቅ ወይም ይህን የመሰለ በመራጮች ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ማናቸውምነገር ማድረግ አይፈቀድም።
3. ሕዝቡ እጩ ተመራጮችን ለይቶ እንዲያውቅ ስለማንነታቸው የተዘጋጀው ጽሑፍ በምርጫ አስፈጻሚ አካላት በምርጫው ቀናት በፊትና በምርጫው እለት ከምርጫው በፊት በመስጊድ ዉስጥ ይነበባል እንዲሁም ይለጠፋል።
4. ስለተመራጩቹ ማንነት የሚያስተዋዉቀውን በመስጊዱ ዉስጥ ሕዝቡ በሚረዳው ቋንቋ ይለጠፋል። ምርጫው እስኪጠናቀቅ ወረቀቱን ማንሳት፣መቅደድና ከላዩ ምንም ጽሑፍ መሰረዝ ክልክል ነው።
5. ምርጫው አንድ ሳምንት ሲቀረው እጩዎች ማንነት በምርጫው እለት የመስጊዱ ጀመዓ አባላት ተገኝተው እንዲመርጡ በሚታይ መልኩ በመስጊዱ ዉስጥ ይለጠፋል።

## አንቀጽ93
## የምርጫ አተገባበር

1. የየእርከኑ ምርጫ ከአቅም በላይ የሆነ ከባድ ችግር ተከስቶእንዲዘገይ ካልተደረገ በስተቀር በመላ ሀገሪቱ ምርጫ በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት ይደረጋል።
2. ምርጫ በምስጢር በካርድ ከተካሄደ በኋላ ዉጤቱን በታዛቢዎች ፊት ይቆጠራል። ታዛቢዎችም ከሌላ ወረዳ ወይም ዞን ከተለያየ ጉልህ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚመለሙና አምስት አባላት ያሉት ይሆናል።
3. በምርጫ ጊዜ እያንዳንዱ መራጭ ምርጫ በሚደረግበት መስጊድ የመስጊዱ ጀመዓ አባልነቱን የሚያሳይና መዋጮዉን እስከ ምርጫው መዋጮ የከፈለ መሆኑ የመታወቂያ ካርዱን እያሳየ ወደ መስጊዱ እንዲገባ ይደረጋል።
4. የመስጊድ አስተዳደሮችን በየመስጊዱ በጀመዓ አባልነት የተመዘገቡ ሰጋጆች ብቻ ይመረጣሉ።
5. እያንዳንዱ መስጊድ በቋሚ ጀመዓነት በመስጊዱ ለሚሰግዱ ሙስሊሞች የመታወቂያ ካርድ የማዘጋጀት፣መታወቂያ የተሰጣቸውን እለትና ስለየአባልነት ክፍያው የአባላት መመዝገቢያነት በተዘጋጀ መዝገብና አቅም በፈቀደ መጠን በኮምፒዩተር የመመዝገብ ግዴታ አለበት።
6. በምርጫ ጊዜ እያንዳንዱ የመስጊዱ አባል ወደ መስጊዱ ወይም ወደ ምርጫ ጣቢያው የሚገባው የአባልነቱ መታወቂያ እያሳየና እየተረጋገጠ ይሆናል።

7. ምርጫ የሚደረግበት ወር በቋሚነት መታወቅ ያለበት ሲሆን ቀድሞ የሚታወቀው ወር ከረመዳን ወር ጋር ከተገናኘ የምርጫው ጊዜ የረመዳን ወር በወጣ በሠላሳ ቀናት ዉስጥ መደረግ አለበት። የምርጫው ጊዜና እለቱ ሦስት ወራት ቀደም ብሎ ይፋ ይደረጋል።
8. የመጀመሪያው የመስጊድ አስተዳደር ኮሚቴ ምርጫ ይጠናቀቃል። ቀጥሎ መስጊዱን በመወከል ለወረዳው መጅሊስ መሪነት እንዲወዳደሩ የሚላኩ እጩዎች ይመረጣሉ።
9. በእያንዳንዱ መስጊድ አንዳንድ ሰዎች መስጊዱን በመወከል በመስጊዱ ጀመዓ ሕዝብ ተመርጠው ለወረዳ መጅሊስ ይላካሉ።
10. ከመስጂድ ተመርጠው ወደ ወረዳ የተላኩት የወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ አባል የሚሆኑ ሲሆንከመካከላቸው የወረዳ መጅሊስ ሥራ አስፈጻሚዎችና ወረዳዉን ወክሎ ወደ ዞን የሚላክ አንድ ሰው ይመርጣሉ።
11. ወረዳን ወክለው ወደዞን የተላኩት የዞኑ ጠቅላላ ጉባኤ አባል የሚሆኑ ሲሆንከመካካላቸው የዞን አመራሮችንይመርጣሉ።
12. የዞንሊቀመንበሮች፣ምክትሎችና ዋና ጸሓፊዎች የክልሉ መጅሊስ ጠቅላለ ጉባኤ አባል ይሆናሉ።
13. የፌደራል መጅሊስን ጠቅላላ ጉባኤ የሚመሰርቱት የክልሉ መጅሊስ ሊቀመንበር፣ምክትልና ዋና ጸሓፊዎች እንዲሁም በህዝብ ብዛታቸው ቀመር ለየክልሉ የሚጨመር ኮታ እንዲሁም በህዝብ የማይመረጡ የማህበራት ተወካዮች ናቸው።
14. ሁሉም ዓይነት የምርጫ ሥርዓቶችና ክንውኖች በተንቀሳቃሽ ምስልና በአስፈጻሚዎቹ በተፈረመ ቃለ ጉባኤ መቀመጥ አለበት።

## አንቀጽ 93
## የቅሬታ አቀራረብ

1. በመስጅድ ምርጫ ላይ ቅሬታ የሚቀርበው ሕዝቡ ምርጫዉን አጠናቶ ምርጫው ከተደረገበት መስጅድ ወይም የምርጫ ጣቢያ ከመበተኑ በፊት ነው።
2. በመስጅድ ደረጃ በሚገኝ ምርጫ የሚቀርብ ቅሬታ በዚያው በምርጫው ጊዜ ሕዝቡ ከመስጅድ ሳይበተን እጅ በማውጣት ሲፈቀድ ቅሬታውን አግባብነት ባለው መልኩ በማስረዳት ይሆናል።
3. ማናቸውም ምርጫ ነክ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ከቀረቡ በተዋረድ ያለው የዑለማ ምክር ቤት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ አቤቱታውን ያያል።
4. የኡለማ ምክር ቤት ቅሬታ ሰሚ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ይግባኙን በሰባት ቀናት ውስጥ በቀጣዩ እርከን ለሚገኝ የኡለማ ምክር ቤት ቅሬታ ሰሚ ያቀርባል።

## አንቀጽ 94
## የምርጫ ዉጤት ስረዛና የዳግም ምርጫ

በየትኛውም የመጅሊስ እርከን ምርጫ ላይ የቀረበ ቅሬታበምርጫ አስፈሚው ቦርድና በዑለማ ምክር ቤት ተገቢ ሆኖከተረጋገጠ አቤቱታ የቀረበበት ምርጫ ዉጤት ተሰርዞ ምርጫው ሊደገም ይችላል።

## አንቀጽ 95
## ምርጫ ነክ ቅጣቶችና እርምጃዎች

1. ከአንድ በላይ በሆነ መስጅድ በአባልነት ተመዝግቦ የተገኘ መራጭ ወይም እጩ ከምርጫው ይሰረዛል፤በተጨማሪም ስሙ በጥቁር መዝገብ አርፎ ለአንድ የምርጫ ዘመን ከመምረጥና ከመመረጥ ይታገዳል፡፡
2. የምርጫ ሂደትን በመጮህ፣ አልያም በሌላ ማንኛውም መንገድ ማወክና ማጭበርበር ወይም ለማወክና ለማጭበርበር መሞከር፣ ያለመታወቂያ ለመምረጥ ወይም ለመመረጥ የሞከረ ስሙበጥቁር መዝገብ ተይዞ ከእለቱ ምርጫና ከአምስት ዓመት በኋላ ከሚደረገው ምርጫ ይታገዳል፡፡
3. በምርጫ ሰዓት ምርጫ በሚካሄድበት መስጊድ ጀመዓ አባል ስለመሆኑ የሚገልጽ የመታወቂያ ካርድ ሳይይዝ ወደ መስጊድ ካልገባሁ ብሎ ንትርክ የፈጠረ፣የተከራከረ ወይም በሌላ መንገድ ለመግባት የሞከረ ሰው ስሙ በጥቁር መዝገብ ተይዞ በእለቱ ምርጫና ከአምስት ዓመት በኋላ ጭምር ከሚደረገው አንድ ምርጫ ይታገዳል፡፡
4. በሕዝብ ፍላጎት በአብላጫ ድምጽ የተመረጠን ተመራጭ ዉጤት በሚገለጽበት ጊዜ ተቃውሞን የሚገልጽ ማንኛውንም ጩኸት ማሰማት ወይም አንዳች የተቃውሞ ድምጽን ያሰማ ሰው ስሙ በጥቁር መዝገብ ተይዞ ለሁለት ተከታታይ ምርጫዎች ከመሳተፍና ከመመረጥ ይታገዳል፡፡
5. ስማቸው በጥቁር መዝገብ የተመዘገቡ ሰዎች ዝርዝር የሚቀጥለው ምርጫ ከመደረጉ በፊት በምርጫ እንደማይሳተፉ ለማሳወቅ ዓለማ ብቻ ስማቸው በወረዳዎቹ ዉስጥ ባሉ መስጊዶች ለሚዋቀሩ አስመራጮች ይላካል፡፡
6. ስማቸው በጥቁር መዝገብ የተመዘገቡ ሰዎች ጥፋታቸውን አምነውና በጽሑፍ በወረዳው ላለ የዑለማ ምክር ቤት ይቅርታ ከጠየቁ የዑለማ ምክር ቤት ጸጸታቸውን ተቀብሎ በምርጫው በመራጭነት የመሳተፍ እግዳቸውን ሊያነሳላቸው ይችላል፡፡ ይህንኑ ዉሳኔውን የዑለማ ምክር ቤት ከምርጫው አንድ ወር በፊት በጽሑፍ ግለሰቡ ለታገደበት መስጅድ ይልካል፡፡

## አንቀጽ 96
## የምርጫ ዉጤት አገላለጽ ሥርዓት

1. የምርጫው አስፈጻሚ አካላት የምርጫውን ዉጤት ለሕዝብ ይፋ ያደርጋሉ፡፡
2. የመስጊድ የአስተዳደር ምርጫና መስጊዱን በመወከል ለወረዳ የሚላኩ ተመራጮች ዉጤት የሚገለጸው በምርጫው ጣቢያነት ባገለገለው መስጊድ ዉስጥ በይፋ ይነገራል፡፡ በተጨማሪም በግልጽ በሚታይ ሁኔታ እያንዳንዱ እጩ ያገኘው ዉጤትና ያሸነፉት ተለይቶ በሚታወቅ መልኩ ይለጠፋል፡፡

3. ለወረዳ መጅሊስ አመራርነትና ወረዳውን ወክሎ ወደ ዞን የሚላኩ ተመራጭ ማንነት ተለይቶ ካገኙት ድምጽ ጋር በወረዳ ዉስጥ በሚገኙ መስጊዶች ዉስጥ ይነበባል። በይፋ በሚታይ መልኩም ይለጠፋል።
4. ለዞን መጅሊስ በመሪነት የተመረጡ ግለሰቦች ማንነት በዞኑ ዉስጥ ባሉ የወረዳ መጅሊሶች አማካኝነት በዞኑ መስጂዶች ለህዝብ ይፋ ይደረጋል።በተጨማሪም በዞኑ ክልል በሚሰራጩ ራዲዮ ጣቢያዎችም ይገለጻል።
5. በክልል ደረጃ በመጅሊስ መሪነት የሚመረጡ ግለሰቦችን ማንነት ቢያንስ በክልሉ በሚሰራጩ ብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል።
6. የቦርዱ አባላት የምርጫዉን ዉጤት በይፋ ለህዝቡ ተገቢ በሆኑ መንገዶች ይፋ ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 97
## የምርጫ ዉጤትን በጸጋ ስለመቀበል

1. የምርጫ ዉጤት በአብላጫ ድምጽ ሲሆን በድምጽ ብልጫ የተሸነፈ እጩ ተመራጭና መራጩ ህዝብ ዉጤቱን በጸጋ መቀበልና ለዉጤቱ መገዛት አለበት።
2. በህዝብ የተመረጠ ተመራጭ በማንኛውም ምክንያት የህዝብን ፍላጎት ተቃርኖ ዉድቅ ሊደረግ አይችልም።

## አንቀጽ 98
## የኢማም ምርጫ ልዩ ሁኔታ

1. የመስጊድ ኢማም በመስጅዱ ጀመዓ አባላት ቢያንስ ከግማሽ በላይ በሚሆኑት የጠቅላላ ጉባኤ እንዲለወጥ ቅሬታ ካልተነሳበት በስተቀር ወይንም የዑለሞች የአንድነትና የትብብርን ሰነድ በመጣስ ተከሶ ሊታረም ፈቃደኛ ካልሆነ በስተቀር አልያም በጤና  ችግር ምክንያት ሀላፊነቱን መወጣት በማይችልበት ደረጃ ካልደረሰ  በቀር ምርጫውና ሃላፊነቱ  በጊዜ የተገደበ አይደለም።
2. በአቤቱታ ምክንት የኢማም ስንብት የሚደረገው ከመስጅዱ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ከሃምሳ በመቶ በላይ ምዕመናን አባላት በጽሁፍ በፊርሚያ የተደገፈ ቅሬታ ካቀረቡና አቤቱታ አቅራቢዎች ማንነት ከመዛግብት ተረጋግጦና የቅሬታ አቅራቢዎች በግንባር ቀርበው በስብሰባ ለቀረበው ሰነድ ይሁንታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የኢማሙ መነሳት በቋሚ ጉባኤው በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲደገፍ ለህዝብ ተደራሽ በሆነ መንገድ ይፋ ያደርጋል። በግልጽ በሚታይ ቦታ በጽሁፍ ያሳውቃል።
3. ለማንኛውም አዲስ ወይም ነባር መሰጅድ አዲስ ኢማም ወይም ምክትሉን ወይም በማናቸውም ምክንያት በለቀቀ ወይም በተሰናበተኢማም ወይም ምክትል ቦታ ሌላ መምረጥ ወይም መተካት የሚቻለው በመስጅድ ቋሚ ጉባኤ መልማይነትና አቅራቢነት አምስት ዕጩዎች ለወረዳው ኡለማ ምክር ቤት ቀርበው የኢማምነት መመዘኛ ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ቋሚ ጉባኤው ከጸደቁት ዕጩዎች መካከል ዋና እና ምክትሉን መርጦ ይሾማል።

## ክፍል 7 ሰባት
## የሕገ-መጅሊስ ማሻሻያ ሥርዓት

### ምዕራፍ አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌ

#### አንቀጽ 99
#### የሕገ-መጅሊስ ማሻሻያን ስለማመንጨት

1. የሕገ-መጅሊሱማናቸውም ድንጋጌ የማሻሻል ሀሳብ የሚመነጨው በሚከተሉት አካላት ብቻ ነው፡-
   1.1. የሀገራዊ ጠቅላላ ጉባኤ አንድ ሶስተና አባላት በላይ የማሻሻያ ሀሳቡ ተደግፎ ጥያቄው ሲቀርብ፤
   1.2. በሀገራዊ የኡለማ ምክር ቤትየማሻሻያ ሀሳቡ በአብላጫ ድምጽ ተደግፎ ጥያቄው ሲቀርብ፤
   1.3. በሥራ አመራር ቦርዱ የማሻሻያ ሀሳቡ በአብላጫ ድምጽ ተደግፎ ጥያቄው ሲቀርብ
   1.4. በማናቸውም ክልል ጠቅላላ ጉባኤ የማሻሻያ ሀሳቡ በአብላጫ ድምጽ ተደግፎ ጥያቄው ሲቀርብ
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሱት አካላት አንዱ የማሻሻያ ሃሳቡን በማመንጨት ለጠቅላላ ጉባኤ ጽ/ቤት ሲያቀርቡ አጀንዳው ለውይይት ይቀርባል።

### ምዕራፍ ሁለት
### መደበኛ የማሻሻያ ሥርዓት

#### አንቀጽ 100
#### መደበኛ ማሻሻያን ስለማጽደቅ

1. በዚህ የሕገ-መጅሊስ ክፍል በምዕራፍ ሁለት ከተደነገጉት ልዩ የማሻሻያ ሥርዓት ከሚፈልጉት ጥብቅ ጉዳዮችን በሚመለከት ከተደነገጉት ውጭ የሆኑ መደበኛ የሕገ-መጅሊሱ ድንጋጌዎችን የማሻሻል ስልጣን የሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤው ነው።
2. ሀገራዊው ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ማሻሻያዎችን የሚያጸድቀው በተገኙት አባላት ቢያንስ በ2/3ኛ አባላቱ ከተደገፈ ብቻ ነው።

### ምዕራፍ ሁለት
### ልዩ የማሻሻያ ሥርዓት

#### አንቀጽ101
#### ልዩ የማሻሻያ ሥርዓት የሚሹ ጥብቅ ድንጋጌዎች

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተዘረዘሩትን ጥብቅ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ጥብቅ ድንጋጌዎች በዚህ ምዕራፍ በተደነገጉት ልዩ የማሻሻያ ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር አይሻሻሉም።
2. የዚህ ሕገ-መጅሊስ ድንጋጌዎች ልዩ የማሻሻያ ሥርኣት የሚፈልጉ ጥብቅ ድንጋጌዎች ናቸው የሚባሉት ከሚከተሉት ጉዳዮች ቢያንስ አንዱን የሚመለከት ከሆነ ብቻ ነው፡-
   2.1. በመስጂድ የኢማምና የአስተዳደር ጉዳይ ላይ የመወሰን መብቱ በመስጊዱ የሚሰግደው የተመዘገበው ምዕመን ብቻ መሆን፤
   2.2. በየትኛውም እርከን ያለን የእስልምና ጉዳይን ተመራጭ ከስልጣን የማንሳት መብቱ በቀጥታ የመረጠው አካል ብቻ መሆኑ፤

2.3. በሕዝብ የተመረጠ የትኛውም የእስልምና ጉዳይ አካል ሕዝቡ አመኔታውን ባነሳበት ጊዜ ከስልጣኑ የመልቀቅ ግዴታ ያለበት መሆኑና ይህን የሚቃረን መተዳደሪያ ደንብ፣ትዕዛዝና መመሪያ ማውጣት የማይቻል ሆኖ አንድ እርከን ከተመረጠ በኋላ በተዋረድ ካሉ ቀጣይ የመጅሊስ እርከኖች አመኔታ አግኝቶ የተመረጠ አካል በመጀመሪያው እርከን አመኔታ በማጣቱ ብቻ በተዋረድ እምነት ያሳደሩበት አካላት አመኔታቸውን ካላነሱ በቀር ከስልጣኑ የማይለቅ መሆኑ፤

2.4. ማንኛውም ሙስሊም የምርጫውን መስፈርት እስካሟላ ድረስ በሚከተለው የዲን አመለካከቱ ምክንያት በመጅሊስ ምርጫ እጩ ሆኖ እንዲያቀርብ ማድረግ አለመቻሉ፤

2.5. ከመስጂድ እስከ ሀገር አቀፍ መጅሊስ ድረስ በሁሉም እርከኖች የዱዓቶች፣የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የሙሁራን፣ እና የሙስሊም ሞያተኞች ማህበራት ይደራጃሉ:: ተጠሪነታቸው በተዋረድ ላለው ጠቅላላ ጉባኤ መሆኑ፤

2.6. ከመስጂድ የአስተዳደር ኮሚቴ እስከ ሀገር አቀፍ መጅሊስ ያሉት በየአምስት ዓመቱ ምርጫ ያደርጋሉ:: በማንኛውም ምክንያት የምርጫ ጊዜን ማራዘም ሆኖነገር ግን በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ መከሰቱን የፌደራል መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ካጸደቀው ብቻ ለአንድ ጊዜ ብቻ እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ድረስ ብቻ የመርጫ ዘመንን ማራዘም ስለመቻሉ፤

2.7. በየትኛውም እርከን ያለ የእስልምና ጉዳይ መዋቅር አንድን ሙስሊም በሃይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ አቋሙ አልያም ሌላ ምክንያት አገልግሎት እንዳያገኝ መከልከል አለመቻሉ፤

2.8. በየትኛውም የመጅሊስ አካል የህዝበ ሙስሊሙን አንድነት የሚሸራርፍ ወይንም አንድን ጀመዓ ወይም መዝሀብ ተከታይን የሚያገልወይም የሚያጠቃ መመሪያ ዉድቅ መሆኑ፤

2.9. የየትኛውም መስጊድ አስተዳደር በመስጂዱ ለሚሰግድና የአካባቢው ነዋሪ ለሆነ ሰው የመስጂዱ ጀመዓ አባል መሆኑን የሚገልጽ የመታወቂያ ካርድ የመስጠት ግዴታ አለበት:: በማንኛውም አቋሙና ማንነቱ ምክንያት መታወቂያ መከልከል አለመቻሉ፤

2.10. በሁሉም እርከኖች ያሉ የመጅሊስ መሪዎች የመጅሊሱ ዋናው ዓላማ ኢስላምን መጠበቅ፣ ማስፋፋትና የሙስሊሞችን መብትና ጥቅሞችን መጠበቅ መሆኑን በመረዳት የቆመውና ወገንተኛነቱ ለኢስላምና ለሙስሊሞች መሆኑን በተግባር ማሳየት ግዴታ ስለመሆኑ፤

2.11. ከወረዳ እስከ ፌደራል ያሉ የመጅሊስ አመራሮች በአካባቢያቸው ያሉ ሙስሊሞች ህጉ በሚፈቅደው መንገድ ሁሉ በመደራጅት ህብረተሰባቸውን እንዲያገለግሉ ማገዝ ግዴታቸው መሆኑና የተደራጁትንም አቅም በፈቀደው ሁሉ እንዲጠናከሩ ማገዝ እንዲሁም የሚጠናከሩበትን መንገድ መፈለግ ግዴታቸው ስለመሆኑ፤

2.12. መጅሊስ የህዝበ ሙስሊሙ ጥላና ወካይ ድርጅት በመሆኑ ማንኛውንም በኢስላምና በሙስሊሞች ስም የተደራጁትንን ስብስቦችን ሁሉ ያለምንም ልዩነት የማቀፍ፣የማገዝ መብትና ነጻነታቸው እንዳይሸራረፍ ከጎናቸው መቆም ያለበት ስለመሆኑ፤

2.13. በሁሉም የእስልምና ጉዳዮች እርከኖች ዉሳኔዎች የሚወሰኑት በአብላጫ ድምጽ ሲሆን በድምጽ ብልጫ ሀሳቡና አቋሙ ዉድቅ የሆነበት ሁሉ የፈትዋ ጉዳይ እስካልሆነ ድረስ ለዉሳኔው ተገዢ የመሆን ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፤

2.14. የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤቱ የታችኛው የመጨረሻ እርከኑ የመስጊድ ምክር ቤት ሲሆን ምርጫ ሁልጊዜ የሚደረገው በመስጂድ ቅጥር ግቢ ብቻ ስለመሆኑ፤

2.15. ማንኛውም ሙስሊም በየትኛውም መስጊድ የመስገድ፣ ትምህርቶችን የመከታተል መብቱን ማንም ሊገድበው አለመቻሉና ምርጫ መሳተፍ የሚችለው ግን በመኖሪያ ቤቱ አከባቢ ባለ መስጊድ ብቻ ስለ መሆኑ የሚያወሱ ድንጋጌዎች ጥብቅ ናቸው፡፡

## አንቀጽ102
## የልዩ ማሻሻያ ሥርዓት ጥብቅ ዓላማዎች

1. የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት ጥብቅ ዓላማዎች አኳያ መተርጎም አለባቸው፡፡
2. የዚህ ምዕራፍ ልዩ የማሻሻያ ሥርዓት መጅሊሳዊ ጥብቅ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

2.1. የኢስላምን ዲንንና የሙስሊሞችን ጥቅሞች መጠበቅ፤

2.2. የሙስሊሞችን አንድነትና ሕብረት መጠበቅ፤

2.3. በሰላማዊ መንገድ ኢስላምን በሀገሪቱ ማስፋፋት፤

2.4. ሙስሊሞች ከልጅነት ጊዜጀምሮ ኢስላምን በጥልቀት የሚረዱና የሚተገብሩ እንዲሆኑ ማስቻል፤

2.5. ሙስሊሞች ኢስላማዊና የሀገሪቱ ሕጎች በሚፈቅዱት መንገድ በፈለጉት መንገድ በግልም ሆነ በተደራጀ መልኩ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ሁሉ ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ማስቻል፤

2.6. ሁሉንም ሙስሊሞች በተለይም የሙስሊሙ ቁጥር አናሳ በሆነበት አከባቢዎች ሕዝበ ሙስሊሙን በተለያዩ መንገዶች ሃይማኖቱን ለማስለቀቅከሚንቀሳቀሱ ማናቸውም አካላት በመከላከል ጽኑ ኢስላምን የተረዱና የሚተገብሩ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

## አንቀጽ103
## ልዩ የማሻሻያ ሥነ ሥርዓት

በዚህ በምዕራፍ የተደነገጉት ልዩ የማሻሻያ ሥርዓት የሚፈልጉት ጥብቅ ጉዳዮችን የያዙ ጥብቅ ድንጋጌዎች የማሻሻያ ሃሳቦቹ በአንቀጽ 85 መሰረት ቀርበው አጀንዳው በሀገራዊው ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ሶስተኛ(2/3ኛ) ድምጽ ከተደገፈ በኋላ የሁሉም ክልል መጅሊስ ጠቅላላ ጉባኤ በተናጠል በሚያደርጉት ስብሰባ እያንዳንዳቸው በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲያጸድቁት ብቻ ነው፡፡ የኡለማ አንድነትና መግባቢያ ሰነድ ግን በመግባቢያ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው ደንብ መሰረት ብቻ ነው ሊሻሻል የሚችለው፡፡

## ክፍል ፰ ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ104
### የገቢ ምንጭ

የመጅሊስ የገቢ ምንጭ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ከአባላት መዋጮ፣
2. ከውጪና ከሀገር ውስጥ በጎ አድራጊዎች የሚገኝ እርዳታና ስጦታ፣
3. ከገንዘብ ማሰባሰቢያ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች፣
4. ከሐጅና ዑምራ ጉዞ መስተንግዶ የሚገኝ የአገልግሎት ክፍያ፣
5. ከወቅፍና ከፕሮጀክት ዝግጅት ፕሮፖዛል ፈንድ ከሚገኝ ገቢ፣
6. ዓላማውን ለማስፈጸም በሚስችል ሁኔታ ከሚኖር የንግድና የህንጻ ኪራይ
7. መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ ድጎማ፣

### አንቀጽ 105
### የሽግግር ጊዜ ድንጋጌ

### አንቀጽ107
### በክብር ስለሚሰናበቱ የኡለማና የአስተዳደር ከፍተኛ አመራሮች ልዩ ጥቅም

በክብር ስለሚሰናበቱ የኡለማና የአስተዳደር ከፍተኛ አመራሮች ልዩ ጥቅምን በተመለከተ ጠቅላላ ጉባኤው ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያወጣል፡፡

### አንቀጽ 106
### ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ

ይህ ሕገ-መጅሊስ በ………………. ከጸደቀበት እንደ ሀገራችን አቆጣጠር ከዛሬ------ ቀን 2011 ጀምሮ የፀና ነው፡፡

**ክቡር ተቀዳሚ ሙፍቲ**
**ሐጂ ዑመር ኢድሪስ**
**የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ ሰብሳቢ**